# የተሳሳተው ማን ነው?

አዘጋጅ፥ አረብ ሙሐመድ ጊንር

4 ኛ እትም   4th Edition   2022

E-mail:-  akkasuma568@gmail.com

## ማውጫ


| ርእስት | ገጽ |
|---|---|
| መቅድም | 1 |
| ጌታ የተባሉት ብዙ ናቸው | 4 |
| እውን ኢየሱስ ሚስት አለው? | 7 |
| እውን ኢየሱስ ኃጢአት አልሰራም? | 11 |
| እውን አምላክ ልጅ አለው? | 16 |
| ኢየሱስ ሙታንን ያስነሳው በራሱ ፍቃድ ነው? | 22 |
| እውን ገነትና ገሃነም የሉም? | 26 |
| አርባ ቀንና ለሊት ብፆምስ? | 28 |
| እነዚህ የአምላክ ባህሪያት ናቸው? | 30 |
| ኢየሱስ ነብይ ነው | 39 |
| ኢየሱስ ሙስሊም ነው | 41 |
| ዘካ | 42 |
| ፆም | 42 |
| ኡድሂያ (መስዋእት) ማቅረብ | 43 |
| ኢየሱስ ይሰግድ ነበር | 45 |
| ሙከራብ በ 1949 መጽኃፍ ቅዱስ መስጊድ ነው | 48 |
| ሙከራብ ሚህራብ ነው | 50 |
| ፂም ማሳደግ | 51 |

ከአንድ በላይ ማግባት........................................................................................... 52

በዘመድ መጋባት...................................................................................................... 54

የወንድምህን ሚስት እርሱ ከሞተ ማግባት...................................... 56

እግዚአብሔርን በውሸት ማምለክ.................................................... 58

ነቢዩ ሙሐመድ (ዐ.ሰ.ወ) በቁርዓንና በመጽኃፍ ቅዱስ......59

# መቅድም

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡
መጽኃፌን ከማንበባችሁ በፊት እኛ የተወያየንባቸው መጽኃፍ ቅዱሶች ከነአትማቸው ማወቅ ያስፈልጋል፡

1. ቅዱስ ቁርዓን አማርኛ ትርጉም ነው፡፡
2. በ 1949 መጽኃፍ ቅዱስ ትርጉም ነው፡ በውስጡ የተጻፉት ቃላቶች የኮምፒዩተር ሳይሆን የእጅ ፅሁፎች ይመስላሉ፡ እርሱ የሚለየው በዚህ ነው፡፡
3. በ 1954 መጽኃፍ ቅዱስ ትርጉም በውስጡ ተጠቅመው የጻፉት የግእዝ ቁጥር (፩፣፴፣፵፣፶…) ነው፡፡
4. በ 1980 ቀለል ባለ አማርኛ መጽኃፍ ቅዱስ ትርጉም ነው፡ በውስጡ ተጠቅመው የፃፉት እኛ በሀገራችን ትምህርት ቤት የምንማርበት ቁጥር (1፣2፣3…) ነው፡፡
5. ዘዳቬንቺ ኮድ ዳንብራን ባዘጋጀው የአማርኛ ትርጉም፡፡
6. New king James version
7. ድሮ በሀገራችን ውስጥ ፕሮቴስታንቶች ሙስሊሞችን አናስገባም አናስወጣም እያሉ ለማስመሰል፡ አንዳንድ የቁርዓን አንቀጾችን እየቆራረጡ በተለያዩ መጽኃፍቶችንና በካሴት ሙስሊሞችን ሲያሳስቱ ቆይተዋል፡ የሀገራችን ህገ መንግስት አንቀጽ 27 ንኡስ አንቀፅ 1-5 እና አንቀጽ 90 ንኡስ አንቀጽ 2 እንዳለ ሆኖ እነዚህ ሁለቱ አንቀጾች ማንም ሰው የፈለገውን ኃይማኖት የመማር እና ማስተማር መብት አለው የፈለገውንም ኃይማኖት የመከተል መብት አለው ስለሚል ማንም ሰው መከልከል አይችልም፡ አሁን ግን የሀገራችን ኦርቶዶክሶች በተለይ የኦርቶዶክስ ማህበረ ቅዱሳን መሪ የሆኑት በሚጽፉትና በየጉባኤው የሚያስተምሩት የቁርዓን አንቀጽ ሆኖዋል፡ ለምሳሌ ያህል እነርሱ የሚጠቀሙትን እንመልከት፡፡
8. በሱረቱል ማኢዳ 5÷116 አላህም የመርየም ልጅ ኢሳ ሆይ አንተ ለሰዎቹ እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን… የሚለውን የቁርዓን አንቀጽ ከቁርኣን ይዘዉ፡ “እኛ ማርያምን አናመልካትም! ቁርዓን የፈጣሪ ቃል ከሆነ ለምን እንዲህ ይላል? ማርያም ታመልደናለች እንጂ አናመልካትም” አሉ፡ በመጀመሪያ እነርሱን የምንጠይቃቸዉ፡ ስንት የክርስትና ክፍፍል አለ? ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ በ 2006 በታተመው ላይ የክርስትና <u>ክፍፍል *33 ሺህ*</u> (encyclopedia Britannica 2006/ultimate reference

suite DVD / electronics version) እንደደረሰ ያሳያል፡፡ ኦርቶዶክስ ከነዚህ ውስጥ አንዱ ነው፡ ታዲያ ኦርቶዶክሶች እነዚህን ሁሉ ወክሎ ለመናገር የነዚህን ሁሉ አካሄድ ማወቅ ነበረባቸው፡ ኦርቶዶክሶች ባይሉ እንኳ የሚሉ አሉ፡ ዘ ኒው ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ (1988) ጥራዝ 16 ገጽ 326 እና 327 እንዲህ ይላል፡- "ለአምላክ እናት አምልኮ አካል ክብር መስጠት ይበልጥ የተስፋፋው… አረማዊ አምልኮ ይከተሉ የነበሩ ሰዎች ወደ ቤተክረስቲያን በጎረፉበት ወቅት ነው፡፡… ‹ወደ ክርስትና የተለወጡት አረማውያን እንዲህ ያለውን› የአምልኮ ቅንዓትንና ሃይማኖተኝነትን ያዳበሩት <u>ለሺህ ዓመታት'ታላቋ' **እናትና ድንግል አምላክ** የተባለችውን ሴት አምላክ ብለው ያመልኩት</u> በነበረበት ወቅት ነው፡፡" ስለዚህ ማርያምንም አምላክ  አድርገው የሚገዙ አሉ፤ እንጂ ቁርዓን አልተሳሳተም፤ ሆን ብለው የሰው ልጅ እስልምናን እንዲጠላ እያደረጉ ነው፡ ታማልዳለች የምልስ የት አለ?

9. <u>አህዛብ ለምን ያግሩመርማል?</u> የሚል (CD) ሲዲ አዘጋጁ ባህሪይሁን ወንድወሰን ነው፡ እዚያ ሲዲ ላይ አህዛብ ብለው ሲጠራ የነበረው ሙስሊሞችን ነው፡ ነገር ግን እኛ ሙስሊሞች አህዛብ አይደለንም፡ በሱረቱል አህዛብ 33÷20 እና 22 ላይ አህዛቦች የነቢያችን ጠላቶች ና ሙሽሪኮች ናቸዉ።

   ከመጽኃፍ ቅዱስም ኦሪት ዘ ዳግም 6÷13 ላይ አህዛብ ማለት  ብዙ ጣዖታትን የሚያመልኩ ናቸው፡ እኛ ሙስሊሞችን  አህዛብ ብሎ መጥራቱ ግን እኛን መስደቡ ነው፡፡መጽኃፍ  ቅዱስን እንኳ ቢያውቅ ኖሮ እኛን አይሰድበንም ነበር፡  በ(CD)ሲዲው ላይ "ኢትዮጵያ …መስጂዶች ለምን ይሰራሉ?
   የታለ ብዛት የ ተገነቡ መስጊዶች በዶዋቸዉን ቀረተዋል፡
   ሙስሊሞች እንግዶች ናቸው፤ከመጡበት መመለስ አለባቸው፤ እኛ ከመጽኃፍ ቅዱስ ና ከቁርዓን የጀመርነውን ነገር እንቀጥልበታለን" … እያለ ይናገራል፡ እኛ ሙስሊሞች ግን  እስከአሁን ላወጣችሁት  ራሱ በቂ መልስ አለን እንላቸዋለን፡ ከማህበረ ቅዱሳኖች ትምህርት ወስደናል የሚሉ ከኔ ጋር ሲወያዩ ነበር፡ እነዚህ ግን ተማሪዎች ናቸው፡ የእነርሱ አስተማሪዎች ቢመጡም በአደባባይ ከእነርሱ ጋር ለመወያየት ዝግጁ ነን፡ የያዙት ነገር ሃቅ መሆኑን ካመኑ፡ በአደባባይ ከእኛ ጋር ይወያዩ፡አይ አንፈልግም የሚሉ ከሆኑ፡ የሚያስተምሩት ነገር ትክክል አይደለም፡፡

10. የቁርአንን አንቀጽ እየቆራረጡ  በየጉባኤዉ ሙስሊሞችን

ለማክፈር ይጠቀማሉ።

*ፀኃፊ ነኢማ ኢብራሂም*

**መልካም ንባብ**

ጌታ የተባሉ ብዙ ናቸው፡፡

ሙስሊም እና ክርስቲያን ዉይይት ቀኑ ደረሰ ከጧቱ **3፡00** ሰዓት ሲሆን የሰው ብዛት በጣም ያስደስታል፡፡

አረብ፡-በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡ በሱረቱል ኢምራን **3÷85** ከእስልምና ውጪ ለሚፈልግ ሰው፡ፈጽሞ ከእርሱ ተቀባይነት የለውም፡እርሱ በመጨረሻው ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው፡፡ በሱረቱል አንከቡት **29÷41** እነዚያ ከአላህ ውጭ ሌላ አማልክትን አማልክት አድርገው የያዙ ሰዎች ምሳሌያቸው ልክ ብዙ ቤቶችን እንደምትሰራ ሸረሪት ብጤ ነው፡ ከቤቶች ሁሉ በጣም ደካማው የሸረሪትቤትነው፡ብያውቁኖሮ(አማልክት፡ አድርገው አይገዟቸውም ነበር፡፡

ከህዝብ ውስጥ፡- አንድ ሰዉ እጁን አወጣና እኔ ክርስቲያን ነኝ፡ ባመንኩት አምላኬ አላፍርም፡ አምላክ ስለመሆኑም አልጠራጠርም፡ ፕሮቴስታንት ኃይማኖት ተከታይ ነኝ፡ <u>እየሱስ ጌታ</u> ነው፡ ከአንተ ጋር ለመወያየት ተዘጋጅቼ መጥቻለሁ፡፡

አረብ፡-ደስታዬን አልችልምና ና ወደ መድረክ ዉጣ!

መስፍን፡-እኔ መስፍን እባላለሁ ወንጌልን ለዓለም ከሚያሰራጩት ወገን ውስጥ አንዱ ነኝ ኃሌሉያ!

አረብ፡-የውይይታችን ርእስ በዚህ አንተ በጀመርከው ላይይሁን?

መስፍን፡-አዎ!ከዚህ ርእስ ውጪ ለሌላ ርእስ ፍቃደኛ አይደለሁም፡፡ የሃንስ ወንጌል **13÷13** እናንተ <u>መምህርና ጌታ</u> ትሉኛላችሁ እንዲሁም ነኝና…በመጽኃፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ቦታ ላይም ኢየሱስ ጌታ ተብሎዋል፣ እናንተ ሙስሊሞች አምላክነቱን የማትቀበሉበት ምክንያት ምንድን ነው?

አረብ፡-ጌታ ነኝ መባሉ ብቻ ለአምላክነት አያበቃውም፡ ምክንያቱም ጌታ የተባሉ ብዙ ናቸውና፡፡

መስፍን፡- ከኢየሱስ ውጪ ጌታ ተብሎ የተጠራ ማንም የለም!

አረብ፡-የለም ሳይሆን አላየሁም በል፡ አንተ ራስህ ይዘህ በመጣህው መጽኃፍ ቅዱስ በ **1980** የተተረጎመ ቀለል ባለ አማርኛ

መጽሃፍ ቅዱስ ትርጉም ነው፡ በአሪት ዘሁልቅ 11÷28
ድምጽህን ከፍ አድርገህ አንብብ!

**መስፍን**፡-ከጎልማሳነቱ ጀምሮ የሙሴ ረዳት የነበረው የነዌ ልጅ እያሱ "ጌታዬ ሙሴ ሆይ! ከልክላቸው" አለው፡፡

**አረብ**፡-1ኛ ጴጥሮስ መልእክት 3÷6 አንብብ!

**መስፍን**፡- የታዘዙትን ሳራ አብረሃምን "ጌታዬ" እያለች ትታዘዝለት እንደነበረው አይነት …

**አረብ**፡-1ኛ መጽኃፈ ነገስት 18÷7-8 አንብብ!

**መስፍን**፡-ዖባዲያ በሚሄድበት መንገድ ላይ ሳለ በድንገት ኤልያስን አገኘው፡ ኤልያስ መሆኑንም ስላወቀ፡ በግንባሩ ወደ መሬት ለጥ ብሎ እጅ ከነሳው በኋላ "**ጌታዬ**" ኤልያስ በእውነት አንተ ነህን? ኤልያስም አዎ እኔ ነኝ እዚህ መሆኔን ሄደህ "**ለጌታህ**" ንገረው፡፡ ብሎ መለሰለት፡፡

**አረብ**፡- ሰዎች ሁላችሁም ልብ በሉ፡ ኤልያስ ጌታዬ ተብሏል፡እንደ መስፍን አባባል ከሆነ ኤልያስም አምላክ መሆኑ ነው አይደል? ኤልያስም ለዖባድያ አዎ እኔ ነኝ እዚህ መሆኔን ሄደህ "ለጌታህ" ንገረው አለው፡ ስለዚህ ዖባዲያ ሁለተኛ ጌታ አለው ማለት ነው፡፡ ጌታ የሚል ቃል አምላክ የሚለውን ሙሉ ትርጉም አይሰጠንም ጌታ ማለት አለቃ ማለት ነው፡፡

አሁንም 2ኛ መጽኃፈ ነገስት 6÷15 አንብብ!

**መስፍን**፡-በመንግስቱም ማለዳ የኤልሳ አገልጋይ ከመኝታው ተነስቶ ከቤት ሲወጣ በፈረሶችና በሰረገላዎች የታጀቡ የሶርያ ወታደሮች ከተሚቱን መክበባቸውን አየ ወደ ኤልያስም ተመልሶ ድምጹን ከፍ በማድረግ ነበር"**ጌታዬ** እነሆ ልንጠፋ ነው ምን ማድረግ ይሻለናል?"ሲል ጠየቀው፡፡

**አረብ**፡-አሁንም በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 21 ያለውን አንብብ፡፡

**መስፍን**፡-የእስራኤልም ንጉስ ሶርያውያንን ባያቸው ጊዜ "**ጌታዬ** ሆይ! ልግደላቸውን?" ሲል ኤልያስን ጠየቀው፡፡

**አረብ**፡-ስለዚህ ኤልያስም አምላክ ነው፡፡ እየሱስን አምላክ ለማድረግ ጌታ መባሉ ለአምላክነት ያበቃል የምትሉ ከሆነ በጣም ያሳዝናል!

**ከተመልካች፡**-ውስጥ አንዱ ተከቢር!

**ሙስሊሞች፡**-በሙሉ አላሁ አክበር!

**መስፍን**፡-መንፈስ ቅዱስ ከአንተ ጋር እንዳልከራከር ከልክሎኛል እኔን በቃኝ፡ ከዚህ በላይ መከራከር ኃጢዓት ነው፡፡

**አረብ**፡- ይህ የክርክር ሳይሆን የውይይት መድረክ ነው፡ መንፈስ ቅዱስ ከአንተ ጋር እንዳልከራከር ከለከለኝ ላልከው፡ ያአንተ መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ ቢሆን ኖሮ፡ ወደ መድረክ ከመምጣትህ በፊት በከለከለህ ነበር፡ ይህ እውነቱን ላለመቀበል የሚታደርጉት ደካማ የሆነ ፍልስፍና ነው፡፡ ማንም ሙስሊም አይሰማህ …

***መስፍን***፡-የውይይቱን ርእስ እንቀይር!

**አረብ**፡- በጣም ትገርማለህ! መጀመሪያ ለሌላ ርእስ ፍቃደኛ እንዳልሆንክ ስትናገር ነበር፡ መድረኩን ትለቃለህ እንጂ የጀመርኩትን ርእስ ሳልጨርስ አዲስ ርእስ አልጀምርም; 2 ኛ መጽኃፈ ነገስት 2÷25 አንብብ፡፡

***መስፍን***፡-እኔ አላነብም!

**አረብ**፡-አንተ ካለነበብክ እኔ አነባለሁ; (ጌሃዚ) ወደ ቤት ተመልሶ ገባ ኤልያስም "እስከ አሁን የት ነበርክ"? ሲል ጠየቀው፡፡ ጌሃዚም "**<u>ጌታዬ</u>**! ኧረ እኔ የትም አልሄድኩም!" ሲል መለሰ፡፡ በተጨማሪም 1ኛ መጽኃፈ ሳሙኤል 25÷27 ዳዊትም ጌታ ተብሏል፡፡ **<u>ጌታዬ</u>** ሆይ! እባክህ ይህን እኔ ያመጣሁልን ስጦታ ተቀብለህ ለተከታዮችህ አድላቸው፡፡ **<u>ጌታዬ</u>** ስላደረግኩትም በደል ይቅር በለኝ፡፡ እግዚአብሔር ዘሮችህን ያነግሳል፡፡ ምክንያቱም አንተ የእግዝኣብሔርን ጦርነት እየተዋጋህ ነው**…** በዚሁ ምእራፍ ቁጥር 31 ምንም ፀፀት ወይም የህሊና ወቀሳ አይድረስብህ ምክንያቱም **<u>ጌታዬ</u>** ሆይ! ያለ ምክንያት ወይም የበቀል እርምጃ ለመውሰድ ብለህ የገደልከው ሰው የለም፡፡ ስለዚህ ***<u>ጌታዬ ሆይ</u>***! እግዚአብሔር በሚባርክህ ጊዜ እኔንም አትርሳኝ፡፡

1. አብረሃም ጌታ ተብሏል
2. ሙሴ ጌታ ተብሏል
3. ኤልሳእ ጌታ ተብሏል
4. ኤሊ ጌታ ተብሏል
5. ዳዊት ጌታ ተብሏል፡ እስከ አሁን ባነበብናቸው ጥቅሶች ዉስጥ ሁሉም አማልክት ናቸው ማለትህ ነውን?

***መስፍን***፡-መድረኩን ለቆ ሄደ

**አረብ**፡-በሱረቱል አህቃፍ 46÷32 የአላህን ጥሪ የማይቀበል ሰው በምድር ውስጥ የሚያመልጥ አይደለም ከአላህ ሌላ ለእርሱ ረዳቶች የሉትም እነዚያ (አለህን እንቢ ያሉ) በግልጽ ስህተት ውስጥ ናቸው፡፡ ኢየሱስን **<u>ጌታዬ</u>** ብላ

ስትጠራው የነበረችው የታሪክ ፀኃፊያን ዘ ዳቬንቺ ኮድ
ዳን ብራውን ባዘጋጀው መጽኃፍ የኢየሱስ እናት ሳትሆን
የኢየሱስ ሚስት እንደሆነች ነው የሚነግሩን፡፡

**አለማየሁ**፡-እጅ አወጣ ከቅድም ጀምረን እየተከታተልንህ ነው፡
ነገር ግን አሁን ገና የማይሆን ነገር አመጣህ; ወደ
መድረክ ሁለት ጓደኞቹን ይዞ መጣ; እየሱስ ሚስት የለውም!

## <u>እውን ኢየሱስ ሚስት አለውን?</u>

**አረብ፡-** ኢሳ(ዐ.ሠ) ቢያገባም ባያገባም እኛ ሙስሊሞችን አያስደንቀንም; ምክንያቱም በሱረቱል ረዓድ 13÷38 (ሙሐመድ ሆይ!) ከአንተ በፊት መልእክተኞችን በእርግጥ ልከናል፡ ለእነርሱም <u>**ሚስቶችንና ልጆችንም**</u> አድርገናል ለማንኛውም መልእክተኛ በአላህ ፍቃድ እንጂ ተአምር ሊያመጣ አይገባውም ለጊዜው ሁሉ ፅሁፍ አለው፡፡ ትዳር ነቢያዊ ፈለክ ነው፡ ያማለቴ ደግሞ ኢሳ ሚስት አግብቷል ማለቴ አይደለም፡ ነገር ግን ቢያገባም አይደንቀንም ነው እያልኩ ያለሁት፡፡

**አለማየሁ፡-**ኢየሱስ ከወንጀል ንፁህ ነው! እንዴት ሚስት ያገባል? የመጣው እኛን ለማስተማር ነው እንጂ ኃጢአት ለመስራት አልመጣም፡ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢየሱስ አንድ ቦታ እንኳ ሃጢአት ሰርቷል የሚል የለም አረብ እየተነናገረ ያለው ነገር ስህተት ነው፡፡

**አረብ፡-**ኃጢአት አልሰራም የሚልስ አለ?

**አለማየሁ**፡-አልሰራም ብየሃለዉ አልሰራም ፡ ምናልባት ስለበላና
ስለጠጣ ይህንን እንደወንጀል ከቆጠርክ አላውቅም፡፡

**አረብ፡-**አንተ ማግባትንም እንደ ወንጀል እያየህ ነው፡ በክርስትና
ኢየሱስ ሰው ሆኖ ሰውን ለማስተማር ወደ ዓለም መጣ
የሚል ትምህርት ከሁሉም ክርስቲያን ድርጅት ይሰጣል፡
ታዲያ የሰው ልጅ ይበላል፣ ይጠጣል፣ ይተኛል፣ ይሄዳል፣
እንዲሁም ሚስት ያገባል፡... ታዲያ ኢየሱስ የሰውን
ባህሪ ሁሉ ተላበሰ ከተባለ ቢያገባ ምን ይገርመሃል?

**አለማየሁ፡-**ዝም!

**አረብ፡-**ዘ ዳቬንቺ ኮድ ዳን ብራውን ባዘጋጀው መጽኃፍ ገጽ 170
1ኛው መስመር ላይ ያለውን፡ ከሁሉም በተለየ መልኩ
ደግሞ ከእየሱስ ክርስቶስ ጋር ትዳር መመስረቷ ነው፡፡ ገጽ

173 መስመር ሁለት ከዚህም በተጨማሪም ኢየሱስ
ማግባቱን መገመቱ እንደተለመደ የመጽኃፍ ቅዱስ
አቀራረብ እየሱስን ወንደላጤ አድርጎ ከመገመቱ በበለጠ
ስሜት ይሰጣል፡ መስመር 7 ደግሞም በዚህ ጊዜ የነበረው
ማህበረሰብ ልማድ በእርግጥ ኢየሱስን ላጤ እንዳይሆን
ያግደዋል፡10 ኛው መስመር ኢየሱስ ባያገባ ኖሮ ቢያንስ
ከመጽኃፍ ቅዱስ ወንጌላውያን መካከል አንዱ ይህንን
ሊገልጽና ያልተለመደው የላጤነት ህይወቱን በተመለከተ
ጥቂት ማብራሪያ ሊሰጡ የግድ ነበር፡፡

**አለማየሁ፡**-ጣልቃ ገባና ከታሪክ መጽኃፍ ከምታነብ ከመጽኃፍ
ቅዱስ አንድ ጥቅስ እንኳ ለምን አታመጣም?

**አረብ፡**-በመጽኃፍ ቅዱስም ከክርስቶስ እናት ከማሪያም ስር ሁሌ
የማትቀር አንዲት ሴት ነበረች ስሟም ማሪያም ነበር፡
አንደኛዋ እናቱ ከሆነች ሁለተኛዋ ታዲያ ምኑ ነበረች?
በማቴዎስ ወንጌል 28÷1 እንከ አንተው አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡**-ሰንበት ካለፈ በኋላ እሁድ ጠዋት በማለዳ መቅደላዊ
***ማሪያም እና ሌላይቱ ማሪያም*** መቃብሩን ሊያዩ ሄዱ… እና
እዚህ ላይ ሚስቱ ናት የሚል የታለ?

**አረብ፡**-1 ኛዋ እናቱ ከሆነች 2 ኛዋ ምኑ ነበረች? አልኩህ እንጂ
ሚስቱ ናት አላልኩህም፡ ምኑ እንደሆነች መልሱን አንተው
ፈልግ፡

**አለማየሁ፡**-ምኑ እንደሆነች እኔ አላውቅም፡ የፈለገ ሰው ሚስቱ
ናት ቢል እንኳ እኔ ሚስቱ ናት አልልም፡፡

**አረብ፡**-በዮሃንስ ወንጌል ምእራፍ 20÷14-15 አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡**-ይህንን ብላ ወደ ኋላ ዞር ስትል እየሱስን ቆሞ አየችው; ኢየሱስ መሆኑን
ግን አላወቀችም ኢየሱስ"አንቺ ሴት ስለምን ታለቅሻለሽ ማንንስ
ትፈልግያለሽ"? አላት

**አረብ፡**-እውን አዚህ ጋር ኢየሱስ አንቺ ሴት ብሎ የጠራት
ማሪያም እናቱ ናትን?

1. እናቱ ብትሆን እየሱስ እናቱን አንቺ ሴት ብሎ ይጠራልን?
2. ኢየሱስ የመጣው ክብርንም ጭምር ለማስተማር ነው ተብሏል፡ ታድያ እናቱን አንቺ ሴት ብሎ የሚጠራት ከሆነ የእርሱ ትምህርት ምን አይነት ትምህርት ነው፡ ወይስ ያቺ ሴት እናቱ አልነበረችም? ታድያ እናቱ ካልሆነች ምኑ ናት?

**አለማየሁ፡**-ሌላ ሴት ትሆናለች እንጂ እናቱን አንቺ ሴት ብሎ

አይጠራትም፡፡

**አረብ፡-**ታዲያ ከዚያ ሁሉ ህዝብ ውስጥ፡ መቃብሩን ለማየት የምትመጣ ሴት ምኑ ብትሆን ነዉ?

**አለማየሁ፡-**እ.እ.. አልሰማህም!

**ሙስሊሞች**፡-አላሁ አክበር ፡፡

**ከአለማየሁ ጓደኞች፡-** አንዱ እኔ ብሩክ እባላለሁ የአዳማ ልጅ ነኝ፤ ኢየሱስ እዝህ ጋር አንቺ ሴት ብሎ ሲጠራት የነበረዉ እናቱን ነዉ፤ አይሁዶች እናታቸውን አንቺ ሴት ብሎ ነው የሚጠሩት፡ ለዚህም ነው ኢየሱስም እናቱን አንቺ ሴት ብሎ የጠራት፡፡

**አረብ፡-**ማስረጃህ ምንድን ነው? እናቱ ከሆነች ኢየሱስ እናቱን <u>አንቺ ሴት</u> ብሎ መጥራቱ የእናቶችን ክብር ማዋረድ አይሆንምን?

**ሁሉም :-**ዝም!

**ከተመልካቾች ውስጥ:-**አንዱ እጁን አወጣና እኔ ስሜን መናገር አልፈልግም፡ ነገር ግን ክርስቲያን ነኝ፤ ከአስርቱ ትእዛዛት ዉስጥ የሁለተኛዋ <u>እናትህ ና አባትህን አከብር</u> ነዉ። አይደለም ክርስቶስ እኔ እንኳ እናቴን አንቺ ሴት ብዬ አልጠርትም፤ ሀይማኖታችን የሚያስተምረው ክብርንም ነው፤ስለዚህ የብሩክ ስህት የጎላ ሆኖ ይታየኛል፡ ለመከራከር ከቻሉ ማስረጃ ማቅረብ ነው፡ ካልቻሉ ግን በክርስትና ላይ ቀዳዳን እንዲፈጥሩ አልፈልግም፡፡

**አረብ፡-**እሺ ጥሩ ነው፡ ለመወያየት በቂ እውቀት አለን ብለው ወደ መድረክ የወጡ ራሳቸው ናቸው፡ ለማወቅ ፍላጎት ካላቸው ደግሞ ፍላጎታቸውን እኔ አልከለክላቸውም፡ ትልቁ የሙስሊሞች አላማ እውነቱን ለህዝቡ ማሳወቅ ነውና፡ አንተም ኢስላም ትክክለኛ ኃይማኖት አይደለም የምትል ከሆንክ መድረኩ ክፍት ነው፡፡

**ከተመልካች**;-ውስጥ እጁን ያወጣው ኣይ እኔ ለመከራከር አልፈልግም።

**አረብ፡-**እሺ! አንድ ሰው በየግብዣ ቤቶች የሚዞረው ከምኑ ጋር ነው?

**ኢብራሂም፡-**ከህዝቡ ውስጥ እጁን አወጣና አንድ ሰው ሁሌ ከወንድ ጋር የሚሄድ ከሆነ ያ ከርሱ ጋር የሚሄደው ጓደኛው መሆን አለበት፡ አንድ ወንድ ሁሌ ከሴት ጋር የሚዞር ከሆነ እጮኛው ትሆናለች፡ ይህ የኔ ግምት ነው፡፡

**አረብ፡-**የኔም ግምት ይህ ነው፡ እናንተስ ትቀበላላችሁ?
**እነ አለማየሁ፡-**እኛ አንቀበልም፡፡
**ህዝብ**፡-በአንድ አፍ እንቀበላለን፡፡

**አረብ፡-**አሁንም በዮሃንስ ወንጌል ምእራፍ 2÷4 ኢየሱስ እናቱን አንቺ ሴት ብሎ ሲጠራት እንደነበር ተፅፏል፡ በግብዣ ቤት ህዝብ ፊትለፊት አንቺ ሴት ብሎ እናቱን መጥራቱ የወለደችውን እናት መስደብ ነው እንጂ እናቱን ማክበር አይደለም፡ ግን የቁርአኑ ኢሳ ነሱረቱል መርየም 19፡32 ለእናቱ ታዛዥ እና ትእቢተኛ እንዳል ነበር አሏህ ያስተምረናል፡፡ ዳን ብራውን ወዳ ዘጋጀው መጽኃፍ እንመለስ ገጽ 173 26 ኛ መስመር የመድኃኒዓለም ደንገጡር (ሚስት) ማለት ነው መቅደላዊ ማሪያም ናት፡ እርሱም ከሁሉ ደቀመዛሙርት በላይ ያፈቅራታል፡ ብዙም ጊዜ አፉዋ ላይ ይስማትማል፡፡የተቀሩት ደቀመዛሙርቱም በዚህ ቅር ይሰኛሉ…፡፡ ዘ ዳቬንቺ ኮድ የሚል አንድ ሆሊውድ(holy wood)ውስጥ በተሰራው ፊልም ላይ እየሱስ ሚስት እንዳለው ፊልሙ በግልጽ ያሳያል፡ ፊልሙ እውነተኛ ታሪክ ላይ ተንተርሶ ነው የወጣው፡ ታሪኩ ውሸት ቢሆን ኖሮ መላው የአለም ክርስቲያን ጮሖ ፊልሙን ከዓለም ላይ ባጠፉት ነበር፡ ፊልሙንም ያወጡት ክርስቲያኖች ራሳቸው ናቸው፡ እዛ ፊልም ላይ አንዷት የፊልም (አክተረስ) ለክርስቶስ ሚስት ሆና ነው የምትሰራው፤ የዛኔ እድሜዋ ገና ወጣት ነበር; ፊልሙን ያወጡት ሙስሊሞች ቢሆኑ ኖሮ በሙስሊም ላይ ይጮህ ነበር፡ ነገር ግን ፊልሙን ያወጡት የናንተው ክርስቲያኖች ናቸው; የምታውቁት ነገር ስላለ ነው እጂ ዝም ያላችሁት; ዝም አትሉም ነበር፡ ገጽ 174 9 ኛው መስመር ፊልሙ ከአንዷት መቅደላዊት ማሪያም ከተባለች ሴት ጋር ኢየሱስ ፍቅር መስራቱን እንደሚገልጽ ያሳያል፡ ገጽ 176 10 ኛው መስመር ከዚህ የበለጠ የፈሩት የሷን የንጉሳውያን ደም ካለው ክርስቶስ ጋር መጋባቱ ነው፡ መስመር 29 እየሱስ ክርስቶስ ሚስት ከማግባቱም በተጨማሪም ልጅም ወልዶ ነበር ይላል፡ እኛ ሙስሊሞች ኢሳ ሚስት አግብቶ ልጅንም ቢወልድ አይደንቀንም ምክንያቱም መውለድ የነብያት ፈለክ ነውና በሱረቱል ረዕድ 13÷38 ላይ ተጽፏልና፡፡ ሙስሊም ወንድሞቼ ሁላችሁም ልብ እንድትሉ የምፈልገው ነገር እኔ ኢሳ ሚስት

አለው ማለቴ አይደለም፡ ነገር ግን ቢያገባም አይደነንቀንም
ነው እያልኩ ያለሁት፡ አሁን ወደ ምርጫህ ልመለስና ታዲያ
የሙስሊሞች ስህተት ምንድን ?

**ሁሉም**:- ዝም!

## **<u>እውን ኢየሱስ ኃጢአት አልሰራምን</u>**?

**አለማየሁ፡**-ከመጽሃፍ ቅዱስም ሆነ ከቁርዓን አንድም ቦታ ኢየሱስ ኃጢዓት ሰርቷል የሚል አላየሁም፡፡

**አረብ፡**- ማሻአላህ ቁርዓንንም ቀርተሃል(አንብበሃል)?

**አለማየሁ፡**-ኣይ አልቀራሁም (አላነበብኩም) <u>ማህበረ ቅዱሳኖች</u> ሲያስተምሩን አንዳንድ ጥቅሶችን ይገፍ ነው፡፡

**አረብ፡**- እናንተስ ብሩክ?

**ብሩክ፡**-እኛም እንደርሱው ነን፡፡

**አረብ፡**-ሉቃስ ወንጌል ምእራፍ 19÷27 አንዳችሁ አንብቡት፡፡

**አለማየሁ፡**-እነዚያ በላያቸው ላይ ልነግስ ያልወደዱትን ጠላቶቼን ወደዚህ አምጡዋቸው **<u>በፊቴም እረዱዋቸው፡፡</u>** ይህ የኛ መጽኃፍ ቅዱስ አይደለም፡፡

**ብሩክ፡**-መጽኃፍ ቅዱስማ የኛ ነው; ነገር ግን ትርጉም አለው፡፡

**አረብ፡**ህዝብ ሁሉ እንዲሰማ ከፍ አድርጋችሁተርጉሙልን፤ አማርኛው ግን ግልጽ አማርኛ ይመስለኛል፡የህንን ብሎ ማዘዙ ወንጀል አይደለምን?

እነብሩክ፤ ለመተርጎም ፈሩ

**አረብ፡**-ትርጉሙ ግልጽ ነው እባካችሁ ራሳችሁን አትሸውዱ፡፡

**ካሳሁን፡**-እኔ የአለማየሁ ጓደኛ ነኝ፡ አማርኛው ግልጽ ነው፡ካልሆነ ህዝቡ ይመስክር፡ እኔ ይህችን ጥቅስ ያየሁት ገና ዛሬነው፡፡ እንደኔ ያላዩ ክርስቲያኖች ብዙ ናቸው ብዬ እገምታለሁ ሌላም ካለ ጨምርልን፡ ትርጉሙን አባቶቻችንን እንጠይቃለን፡፡

**አረብ፡**-ንግግርህ በጣም ያስደስታል! ሰው ማለት እንደዚህ ነው; አሁንም ማቴዎስ 10÷34 አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡**-አላነብም

**ከሳሁን፡**-እኔ አነባለሁ፡፡…<u>**በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ ሰይፍን እንጂ…**</u>

**አረብ፡**-አንድ ሰው እንዲህ አይነት ቃል ከአፉ ሲወጣ ፖሊሶች ቢሰሙት ይህን ሰው ምን ነበር የሚያደርጉት? ለሚለው መልሱ ግልጽ ነው፡ መጽሃፍት ምሳሌ ምእራፍ 23÷31 ወይን ጠጅ አይደለም መጠጣት በአይን ማየት እንኳ የተከለከለ ነው፡ ነገር ግን ኢየሱስ የወይን ጠጅን ይጠጣ ነበር፡ ማቴዎስ 11÷18-19 አንብብ፡፡

**ካሳሁን፡**-እንዲሁም አጥማቂ ዮኃንስ እህል ሳይበላና የወይን ጠጅ ሳይጠጣ ቢመጣ ይህስ ጋኔን አለበት አሉት፡ የሰው ልጅ (ኢየሱስ) ደግሞ <u>እየበላና የወይን ጠጅ …</u>፡፡

**አለማየሁ፡**-እዝህ ጋር የወይን ጠጅ የተባለው አስካሪው አይደለም፡፡

**አረብ፡**-እንደዚያ የሚል የትአለ?

**አለማየሁ፡**-ዝም!

**አረብ፡**-የተከለከለው አጠቃላይ የወይን ጠጅ ነው; መጽሃፍ ቅዱስ ከከለከለ ኢየሱስ ራሱ ለምን ይጠጣል? ወንጀል አይደለም?

**ሁሉም፡**- ዝም!

**አረብ ፡**-አሁንም ማቴዎስ 26÷29 ንብብ

**አለማየሁ፡**-በአባቴ መንግስት አዲሱን <u>የወይን ፍሬ ጭማቂ ከናንተ ጋር እስከምጠጣበት ቀ</u>ን ድረስ ከእንግዲህ ከዚህ የወይን ፍሬ ጭማቂ ዳግመኛ አልጠጣም እለችኋለሁ፡፡

**አረብ፡**-አንድ ማህበራችሁ; ማህበረ ቅዱሳን ባዘጋጀዉ መጽኃፍ ሀመረተዋህዶ 2000 ልዩ እትም በሚለው ላይ፡ እንዴት ቁርዓን ነገ በገነት ውስጥ መጠጥ ይኖራል ይላል፤በማለት ብዙ ነገሮችን ጽፏል; ነገር ግን ኢየሱስ ራሱ በአንደበቱ

በገነት በአባቱ ዘንድ መጠጥ እንዳለ መልስ ሰጥቷል;

መጽኃፍ ቅዱሳችሁን እንኳ በትክክል ብታውቁ ኖሮ ይህ በናንተ ላይ ጥያቄ ሆኖ ሙስሊሞችን አትተቹም ነበር; ነገር ግን፡ እናንተ እንደዛ ብላችሁ መጽኃፋችሁ፤አለማወቃችሁን ለሙስሊሙ ማህበረሰብ እያሳወቃችሁ ነው፡ በመጽኃፉ ውስጥ የተካተቱ በዙ ነገሮች አሉ፡ ተከታታይ መልሶች አላህ ካለ ከሰሞኑ ይለቀቃሉ፡፡

**አለማየሁ፡**-እኛ ከዚህ በላይ ከአንተ ጋር መወያየት አንፈልግም ሀይማኖታችንን ኣትስደብ ብሎ መድረኩን ለቀቀ፡፡

**አረብ፡**-የምን ስድብ? አንድ የስድብ ቃል የተናገረ ሰዉ የለም።

**ኢብራሂም፡**-እያነበባችሁ ያላችሁት እናንተው ራሳችሁ ናችሁ፡

ሌላ ጊዜ የተለያየ መጽኃፍ ከመጽኃፍ ቅዱስና ከቁርዓን እየቀነጨባችሁ ኢስላምን ትተቻላችሁ;በእርግጥ አንዳንድ ክርስቲያኖች ሙስሊሞች ሰደቡን እያሉ በየምክር ቤቶች እየዞሩ ያወራሉ፤ ክርስትያን ኦርቶዶክሶች በ ኢስላም <u>ልይ</u> ብዙ መጽሃፍቶችን ጽፏል

**ለምሳሌ**

1. ኢስልምናና አፍሪካ (1941) አከባቢ የተጻፈ።
2. ለምን ኣልሰለምሁም?
3. በኢትዮጵያ የሃይማኖት መቻቻል ኣለን?
4. ክስቶስና ቁረኣን ምን ኣገናኘዉ?
5. እንድረስላቸዉ።
6. የ እግዚኣብሄርን ክብር ለሙስሊሞች ማካፈል።
7. ኤልሸዳ.............ወዘተ....... ብዙ መጽሃፍቶች ሙስሊምን ለማክፈር ጽፏል
8. ተወዳጁ ወንድማችን <u>ሙሐመድ ከድር</u> <u>አስመሳዮችን ማጋለጫ</u> በሚለው ቪሲዲው(VCD) ላይ ብዙ ኦርቶዶክሶች ከ 20 እና ከ 30 ዓመት በፊት የጻፉት እንኳ ሳይቀሩ በግልጽ ያሳያል፡ ምናልባት ከዚህ ግቢ እንደወጣችሁ ማየት ለምትፈልጉት በየኢስላማዊ ከሴት መደብር ቪሲዲውን

ታገኙታላችሁ፡ አለምየሁ በአደባባይ እንወያይ ተብላችሁ ስትጠሩ ደግሞ ትሸሻላችሁ; አንድ ለዶክተር ዛኪር መልስ ሰጥቻለሁ ሲል የነበረው ምህረተአብ መልስ ከሰጠ ለሙሉ (VCD) ቪሲዲ ነበር መልስ መስጠት የነበረበት፡የዶክተር ዛክርን ንግግር እየቆራረጠ መልስ ሰጥቻለዉ ብሎ አንድ (VCD) ለቀቀ ፡ ይህ ለዶክተር ዛኪር መልስ ሰጥቻለሁ ማለቱ ስም ፍለጋ ነው እንጂ ሃቅን ፍለጋ አይደለም፡፡

9. ሲዲውን ሲተረጉሙት ተርጓሚዎች ተሳስተው ነው እንጂ ዶክተር ዛኪር አልተሳሳተም፡ እሱንም እንድታውቁ እንፈልጋለን፤ ለታላቁ ፍጥጫ ድንቅ መልስ የሚል ተወዳጁ ወንድማችን ሳዲቅ ሙሐመድ ክርስቲያን ኦርቶዶክሶች ለዶክተር ዛኪር መልስ ሰጥተናል ባሉት ላይ ድጋሜ መልስ ሰጥቶበታል; እዚያ ላይ ሳዲቅ ወንድማችን እንደሚለን ምህረተአብ ስልክ ተደውሎለት ለውይይት ፍቃደኛ እንዳልሆነ ነበር የገለጸው፡፡ ምህረተአብ የሰጠው መልስ ትክክለኛ ቢሆን ኖሮ ከሳዲቅ ጋር መየወያየትን ባልፈራ ነበር; ውይይት መፍራቱ ራሱ የሰጠው መልስ ትክክለኛ ኣለመሆኑን ያሳያል፡፡ ምህረተአብና መሰል ሰባኪያን ለሚጽፉት ነገር እውነተኛ መሆኑን ካመኑ ከዛሬ ቀን በኋላ እኛ ለውይይት መድረኩን የምናዘጋጀው ሰው ሁሉ መምጣ በሚችልበት ውይይቱ ይካሄዳል; እናንተም ያውቃሉ የምትሉትን የሃይማኖታችሁን መሪዎች አምጡና ውይይቱ በአደባባይ ይውጣ፡ እነ **ቀመር ሁሴን፣ ሳዲቅ ሙሐመድ፤ ሙሐመድ ከዲር፣ አረብ** ወንድማችንም መላው የኢትዮጵያ መስሊሞች ኢንሻአሏህ ሃቋ ግልጽ እንድትወጣ ዝግጁ ነን;ጣልቃ በመግባቴ ይቅርታ አድርጉልኝ፡፡

**አረብ፡**-ምንም ችግር የለም ሰው የፈለገውን መከተል መብት

አለው; ድንጋይንም ዳቦ ብሎ የሚያስተምር ኖሮ ሰው ከተቀበለው መብቱ ነው;ፕሮቴስታንቶችም በየመንገዱ ቆመዉ ሰበካቸውን እንደቀጠሉ ነው; የሀገራችን ህገ መንግስት ለሁሉም መብት ሰጥቷል; አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1-5 እና አንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ያለው እንደተጠበቀው ሆኖ ማስተማር ይችላሉ፡ ለሁሉም እኩል መብት ሰጥቷል; ወደ ርእሳችን እንመለስና አለማየሁ እና ብሩክ ጥለውን ሄዱ፡መጀመሪያም ወደ መድረክ የወጡትም በፍላጎታቸው ነው ማንም ሰው እንዳይናገራቸው፡፡

ካሳሁን ከኔ ጋር ውይይቱን ቀጠለ፡ ዮሃንስ ወንጌል 2÷3 አንብብ

**ካሳሁን፡**-በሰርጉ ግብዣ ላይ የወይን ጠጅ ባለቀ ጊዜ የኢየሱስ እናት <u>የወይን ጠጅ የላቸውም እኮ!</u> አለችው… እስከ ተራ ቁጥር 12 አነበበው፡፡

**አረብ፡**-ኢየሱስ ወይን ጠጅ ሲያዘጋጅ ነበር; ኢየሱስ የመጣው ለማስተማር ነው ተብሏል; ስለዚህ አስካሪ መጠጥንም ሰዎች እንዴት እንደሚያዘጋጁት አስተምሯል ማለት ነው፡፡ አምላክ ቢሆን ክፉ ነገር ለሰው ያስተምራልን? ራሱም እየጠጣ አምላክነቱ ምኑ ጋር ነው? አምላክ አስካሪ መጠጥን ይጠጣልን?

**አንድ ሰዉ፡**-እጁን አወጣ ዶክተር ዛኪርና ዊሊያም ካምቤል በተከራከሩበት ቪሲዲ(VCD) ላይ ማርቆስ ወንጌል 16÷18-20 አማኞች መርዝ ቢጠጡ እንኳ እንደማይጎዱ ነው የተናገሩት፡

1. በመጽኃፍት ምሳሌ 31÷6 አስካሪ መጠጥ ጠጥታችሁ ደህነታችሁን እረሱ (ስከሩም) ከተፈቀደ
2. መርዝም ከተፈቀደ

3. መሪዎቻችን ይደበቁናል እንጂ ጋንጃ(አሺሽ) ራሱ ሳቡ የሚል አይጠፋም፤ ስለኔ ማወቅ ከፈለግክ ………

**አረብ፡**-እባካችሁ አትረብሹ፡ የመጣነው ሃቁን ለመማማር ነው እንጂ ለመሳቅ አልመጣንም ለመሳቅ የምትፈልጉ ካላችሁ መድረኩ የሳቅ አይደለም፤ እባካችሁ ፀጥታ፤ መጠመቅ የሚያስፈልገው ለምንድንነው?

**ካሳሁን፡**- ከወንጀል ለመዳን ነው፡፡

**አረብ፡**-ማቴዎስ 3÷15 አንብብ

**ካሳሁን፡**-ኢየሱስ ግን የጽድቅን ነገር ሁሉ መፈፀም ስለሚገባን አሁንስ ተው እንዲህ ይሁን ሲል መለሰለት; የሃንስ በነገሩ ተስማምቶ ኢየሱስን **<u>አጠመቀው፡፡</u>** እዚህ ጋር እኮ እየሱስ የተጠመቀው እኛን ለማስተማር ነው፡፡

**አረብ፡**-ጥምቀት ከኢየሱስ በፊት የተጀመረው በአጥማቂው የሃንስ ነው; ክርስቶስንም ያጠመቀው እርሱ ነው; አንዳንድ የክርስቲያን ሰባኪዎች በሱረቱል ሙሐመድ 47÷ 19 አንቀጽን በመጥቀስ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ኃጢዓት ሰርቷል ክርስቶስ ግን ኃጢአት አልሰራም እያሉ ከእስልምና ብዙም እውቀት የሌላቸውን ለማደናገር ይሞክራሉ; ነቢያችን (ዐ.ሰ.ወ) እንዳስተማሩን የአደም ልጅ ሁሉ ይሳሳታል ከስህተተኞቹ በላጮቹ ግን በመፀፀት ወደ አላህ ተመላሾቹ ናቸው፡፡ ኢየሱስም ቢሆን የአዳም ልጅ ነው; የአዳም ልጅ ባይሆን ኖሮ የአዳምን ልጆች ስጋ ባልለበሰ ነበር፡፡

## <u>እውን አምላክ ልጅ አለውን?</u>

**ካሳሁን፡**-ኢየሱስማ የእግዚአብሔር ልጅ ነው!በዮሃንስ ወንጌልምእራፍ 3÷16 እግዚአብሔር አለምን እጅግ

ስለወደደ <u>አንድ ልጁን(ኢየሱስን)</u> ሰጠ ይላል፡፡

**አረብ፡**-ከናንተ ከክርስቲያኖች በፊትም <u>አምላክ ልጅ አለው</u> ተብሏል፡ በሱረቱል ተውባ 9÷30 አይሁድ <u>ኡዘይር የአላህ ልጅ</u> ነው አለች፡ ክርስቲያኖችም <u>አልመሲህ(ኢሳ) የአላህ ልጅ</u> ነው አሉ ይህ በአፎቻቸው (የሚናገሩት) ቃላቸው ነው የነዚያ ከነርሱ በፊት የካዱትንም ሰዎች ቃል ያመሳስላሉ አላህ ያጥፋቸው(ከእውነት) እንዴት ይመለሳሉ፡፡ ልጅ የሚለው በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ <u>አገልጋይ</u> ማለት ነው፡ ይህ እናንተ የሚታዩት New king James versions አለም አቀፍ መጽሃፍ ቅዱስ ነው፡ ACTS 3÷13 ጀምሮ ያለውን እንካ አንብብ፡፡

**ካሳሁን፡**-The god of Abraham, Isaac and Jacob, the god our fathers glorified his ***<u>servant Jesus</u>*** whom you delivered up and denied in the presence of Pilate when he was determined to let him go.

**አረብ፡**-ACTS 4÷26 አንብብ፡፡

**ካሳሁን፡**-To you first god having raised up his *<u>servant Jesus</u>* sent him to bless you…

**አረብ**፡-አሁን ባነበብካቸው በሁለቱም ጥቅሶች እየሱስን <u>his</u> ***<u>servant Jesus</u>*** (የእግዚአብሔር አገልጋይ ወይም ባሪያ ተብሏል፡) ግን በሀገራችን በ 1954 እና በ 1980 የተተረጎሙት ክርስቶስን የብላቴና ልጅ በማለት ጽፈዋል; መጽኃፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው ከተባለ እኘዚህን ጥቅሶች መቀየሩ ራሱ ለምን አስፈለገ ? New king James versions እንዳስቀመጠው በሱረቱል መሪያም 19÷30 ላይ ክርስቶስ እኔ **<u>የአላህ ባሪያ</u>** <u>ነኝ</u> መጽኃፋንም ሰጥቶኛል ነብይም አድርጎኛል፡፡ ታዲያ ቁርዓን የአላህ ባሪያ ብሎ መስክሮ መጽኃፍ ቅዱስም <u>አገልጋይ</u> መሆኑን መስክሮ <u>አገልጋይ</u> መሆኑን የማታምኑበት ምክንያት ምንድን ነው ? ፈጣሪ ልጅ አለው ለምትሉት አላህዬን ጥራት ተገባው፡፡ በሱረቱል

በቀራ 2÷116 **አላህ ልጅ** አለው አሉ (ከምሉት) ጥራት ተገባው አይደለም በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የእርሱ ነው ሁሉም ለእርሱ ታዛዥ ናቸው። ሰማያትንና ምድርን ያለ ብጤ ፈጣሪ ነው ነገርንም (ማስገኘት ወይም መፍጠር) በሻ ጊዜ ለእርሱ የሚለው ሁን ነው ወዲያውም ይሆናል።

አሁንም በሱረቱል ኢስራእ 17÷112 ምስጋና ለአላህ ለዚያ **ልጅን ላልያዘው** ለእርሱም ለንግስናው ታጋሪ ለሌለው ከውርደት ረዳት ለሌለው ይገባው በልም ማክበርንም

አክብረው። በሱረቱል ጅን 72÷3 እነሆ የጌታችን ክብር ላቀ (አላህ) ሚስትንም **ልጅንም አልያዘም።** አይሁዶች የፈጣሪ ልጅ እዝራእ ነው ይላሉ እናንተም የእግዚአብሔር ልጅ እዝራእ ሳይሆን እየሱስ ነው ትላላችሁ። ሙስሊሞቹን ከመጥራታችሁ በፊት በመጀመሪያ እናንተው ተስማሙ ከዚያ በኋላ ነው ሙስሊሞችን መጥራት የምትችሉት; እናንተ መስማማት ካልቻላችሁ ሁለታችሁም ትዋሻላችሁ። በኦሪት

ዘፀዓት 4÷22 አንብብ

**ካሳሁን፡-**አንተ ጫና እየፈጠርክብን ነው፡ ስትናገር ብዙ ሰዓት ትጠቀማለህ; ለእኔና ለሌሎቹም ትንሽ ሰዓት ብቻ ትሰጠናለህ; ጥቅሱን አላነብም!

**አረብ፡-አትዋሽ የፈለከዉን ያህል ለመናገር መብት አለህ፡ ከርእሱ**

**ግን አትዉጣ**፤ደግሞ ለማንበብ? እኔ አነባለሁ; በዚያን ጊዜ እኔ እግዚአብሔር ለፈርዖን የምለውን እንዲህ ብለህ ትነግረዋለህ እስራኤል(ያቆብ) **የበኩር ልጄ** ነው። እናንተም ክርስትያኖች የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ ።

**ካሳውን፡-**እኛ እማ የእግዚአብሔርን ልጅነት ያገኘነው በልጁ በማመናችን ነው፡ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት የእግዚአብሔር ልጅ የተባለ ማንም የለም።

**አረብ፡-**አሁን ያነበብኩልህ ጥቅስ እኮ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት በብሉይኪዳን ነው፡ ያን ጊዜ ክርስቶስ ራሱ አልተወለደም

እንዲሁም ክረስቶስ ከመምጣቱ በፊት ኦሪት ዘዳግም 14÷1 ላይ አማኞች የእግዚአብሔር ልጆች ተብሏል እንካ አንብብ።

**ካሳሁን፡-**እኔ አላነብም አልኩህ አይደል፡ ለምን ትጨቀጭቀኛለህ?

**አረብ፡-**ሌላ ጊዜ ሙስሊሞችን አናስገባም አናስወጣም የምትሉት እናንተ ናችሁ፤ ከእስልምና ብዙ እውቀት የሌላቸው

ሙስሊሞችን ታሳስታላችሁ፤ አንተ ካላነበብክ አሁንም እኔ አነባለሁ፡ እኔ አንብብ የምልህ እኮ በኋላ ጥቅሱን በስህተት አነበበ እንዳትለኝ ነው፡ አላህም አስነብቡ አለን እንጂ አንብቡላቸው አላለንም፡ ጥቅሱ እንድህ ይላል፡- እናንተ የአምላካችሁ **<u>የእግዚአብሔር ልጆች</u>** ናችሁ፡ አሁን ወደ

ቁርዓን ልመለስና በሱረቱል ፉርቃን ምዕራፍ 25÷2 (እርሱ አላህ) የሰማያትና የምድር ንግስና የእርሱ ብቻ የሆነ <u>ልጅንም ያልያዘ</u> በንግስናውም ታጋሪ የሌለው ነገሩንም ሁሉ የፈጠረ እና በትክክልም ያዘጋጀ ነው፡፡

**ካሳሁን፡-**ለእናንተ ለሙስሊሞች ያልገባችሁ ነገር አለ; እግዚአብሔር ልጅን ወለደ ማለታችን እኮ ከሴት ጋር ተገናኝቶ ወለደ ማለታችን አይደለም፡ የወለደው እኮ በመንፈስ ነው፡፡

**ኢብራሂም፡-**መጽኃፍ ቅዱስ አንብብ ስትባል እንቢ ትላለህ; ለመከራከር ለምን ከራስህ ትናገራለህ? እኛ የምንፈልገው ከአንተ ሳይሆን ከመጽኃፉ ነውና ከመጽኃፉ አንብብልን፡፡

**አረብ፡-**በመጀመሪያ ራሱ ሰውም ሆነ ሌላ ፍጡር የሚወልደው አምሳያውን ነው;ኢየሱስና አብ አንድ አምሳያ አላቸው ማለትህ ነውን?

**ካሳሁን፡-**አይደለም፡ እግዚአብሔርማ መንፈስ ነው፤ ኢየሱስ ግን አካል አለው፡፡

**አረብ**፡-እኛ ቁርዓናችን እንደሚያስተምረን ከሆነ ኢሳ በሱረቱል መርየም 19÷19-37 አላህ ለመርየም ያለ አባት ልጅ እንደሰጣት በማያሻማ ሁኔታ ያስተምረናል ይህን የሚጠራጠር ሙስሊም የለም;አላህ ሰማያትንና ምድርን፡ ህይወት ያለዉና ህይወት የሌለዉን መፍጠር; እንዲሁም አዳምን ያለ አባትና ያለ እናት ያስገኘው; ሄዋንንም ከአዳም ከወንድ ያስገኘውን ጌታ፡ ኢሳን ያለ አባት ከእናት ብቻ ማስገኘቱ ምን ይከብደዋል?

**ካሳሁን፡-**ዝም!

**አረብ፡-**ወንድሜ መጽኃፍ ቅዱስ ኢየሱስ በተዓምር መወለዱን ራሱ በሰው ውስጥ ብዥታን ይፈጥራል፡፡

**ካሳሁን፡-**ምንም ብዥታን አይፈጥርም; ምክንያቱም በሉቃስ ወንጌል 1÷31 ጀምሮ ድንግል እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅን ትወልጃለሽ **...** ፡፡ እዚህ ላይ ያለ አባት መወለዱን ያሳያል;ታድያ አንተ የምትለው ምኑ ጋር ነው?

**አረብ፡-**በእርግጥ አንተ ያነበብከውን እኔ ሳላይ ቀርቼ አይደለም፡ በማቴዎስ ወንጌል 1÷18 ማሪያም ለዮሴፍ ከታጩች በኋላ ፀነሰች ይላል፡ ከመታጨቷ በፊት ብትፀንስ እንኳ፡ ተዓምር ይመስል ነበር፡፡ ነገር ግን ከታጨች በኋላ ፀነሰች ቢባል መቼም ለእርሱ ከታጨች በኋላ ሚስቱ ናትና ያፀነሰችዉ ከዮሴፍ ይመስላል፡፡ በሉቃስ ወንጌል 2÷41-49 ባለው ላይም ማሪያም ክርስቶስን እኔ ና **አባትህ** ዮሴፍ ስንፈልግህ ነበር ብላለች፡ ታድያ አሁን ልጁ የማን ይመስላል?

**ህዝብ**፡-በአንድ አፍ የዮሴፍ ይመስላል!

**አረብ፡-**እነ አለማየሁ ተመልሰው መጡ፡ የሰውም ብዛት በጣም እየጨመረ ነው፡ መጽኃፍ ቅዱስ ለናንተም አልገባችሁም ቢገባችሁ ኖሮ ከሙስሊሞች ጋር ለመወያየትም ሆነ ለማስተማር ባልፈራችሁ ነበር፡ በሱረቱል ዩኑስ 10÷66 ንቁ በሰማያት ያሉትና በምድርም ያሉት ሁሉ በእርግጥ የአላህ (ፍጡር) ነው እነዚያ ከአላህ ሌላ ታጋሪዎችን የሚጠሩ ምንን ይከተላሉ? ጥርጣሬን እንጂ ሌላን አይከተሉም እነርሱም የሚዋሹ እንጂ አይደሉም፡፡ አላህ በሱረቱል መሪየም 19 ÷ 88-93

88. (አላህ) አልረህማን ልጅን ያዘ (ወለደ) አሉ
89. ከባድ መጥፎን ነገር በእርግጥ አመጣችሁ
90. ከእርሱ (ከንግግራቸው) ሰማያት ሊቀደዱ ምድርም ልትሰነጠቅ ጋራዎቹም ተንደው ሊወድቁ ይቃረባሉ፡፡
91. ለአልረህማን ልጅ አለው ስላሉ፡፡
92. ለአልረህማን ልጅ መያዝ አይገባውም፡፡
93. በሰማያትና በምድርም ያለ ሁሉ በትንሳኤ(በቂያማ) ቀን ለአልረህማን ባሪያ ሆነው የሚመጡ እንጂ ሌላ አይደሉም፡፡ ፈጣሪ ልጅ አለው የምትሉ ሁላችሁም አላህን እየሰደባችሁ ነው፡፡

**አለማየሁ፡-እንደ መጣ ጠልቃ ገባ** በዮሃንስ ወንጌል 8÷53-58 … "አንተ ገና 50 ዓመት አልሞላህም ታድያ እንዴት አብረሃምን ኣየሁት ትላለህ"፡፡ ኢየሱስም "እውነት እውነት እላችኋለሁ አብረሃም ሳይወለድ እኔ ኣለሁ" ኣላቸው፡፡ ስለዚህም አይሁዳውያን ሊወግሩት ድንጋይ አነሱ; ኢየሱስ ግን ተሰወረባቸው ከቤተመቅደስም ወጥቶ ሄደ፡ ኢየሱስ የአምላክ ልጅ ባይሆን ኖሮ አብረሃም ከመወለዱ በፊት ባልኖረ ነበር፡ **የመጡት ክርስቲኖች** ሁሉም ስሜታዊ መሆን ጀመሩ፡፡

**አረብ፡-**መጽኃፍ ቅዱስ እንደሚለው ከሆነማ አብረሃም ከመወለዱ በፊት አንተም ነበርክ፡ አንተም የአምላክ ልጅ ነሃ?

መጽኃፍት መክብብ 3÷14 አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡-**እግዚአብሔር ያደረገው ሁሉ ለዘለዓለም እንዲኖር አወቅከሁ ሊጨምርበት ወይም ከእርሱ ሊጎድል አይቻልም እግዚአብሔር ከበፊቱ ይፈሩ ዘንድ አደረገ **<u>አሁን ያለው በፊት ነበር የሚሆነው በፊት ሆኖ ነበር</u>** እግዚአብሔር ያለፈውን መልሶ ይሻዋል፡፡

**አረብ፡-**ከመወለዳችን በፊት በእግዚአብሔር ዘንድ ሁላችንም ተፈጥረን ነበር፡ ስለዚህ አብረሀም ከመወለዱ በፊት አንተም ነበርክ፤ታድያ ለማስረጃ ብለህ ያቀረብከው ይህ ብቻ ነው?

**አለማየሁ፡-**በዮሃንስ ወንጌል 8÷12 ደግሞም ኢየሱስ እኔ **<u>የዓለም ብርሃን ነኝ</u>** የሚከተለኝ የህይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገረ፡፡ በሱረቱል ኑር 24÷35 ፈጣሪ ብርሃን ነውና የዓለም ብርሃን መባሉ ራሱ ብቸኛ የአምላክ ልጅ ያደረገዋል ፡፡

**አረብ፡-**በተዓምር አያበቃውም ምክንያቱም የዓለም ብርሃን የተባሉ ብዙ ናቸውና፡ ማቴዎስ 5÷14 አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡-**እናንተ **<u>የዓለም ብርሃን</u>** ናችሁ፡፡ በተራራ ላይ ያሉት.....

**አረብ፡-** እዚህ ጋር ኢየሱስ የዓለም ብርሃን ናችሁ ያላቸው 12 ቱ ሀዋሪያቶች ናቸው፡፡ እንደ አንተ አባባል ከሆነ 12 ቱም ሀዋሪያቶችም የአምላክ ልጆች ናቸው ማለት ነው፡፡ እንዲሁም በሱረቱል አህዛብ 33÷46 (ሙሐመድ ሆይ! ) ወደ አላህም በፍቃዱ ጠሪ **<u>ብርሃንን</u>** (አድርገን ላከንህ)፡፡ እንደ አለማየሁ አካሄድ ከሆነ ነቢዩ ሙሐመድም (ኢ.ሰ.ወ) የአምላክ ልጅ ናቸው ማለት ነው፡፡ ብርሃን የተባለ ሁሉ የአምላክ ልጅ ከተባለ ትልቅ ስህተት ነዉ በሱረቱል አንቢያእ 21÷48 ለሙሳና ለሃሩን እውነትንና ውሸት የሚለይን **<u>ብርሃንንም</u>** ለጥንቁቆችም መገሰጫን በእርግጥ ሰጠናቸው፡፡ ለነሙሳ የተሰጠው መጽኃፍም **<u>ብርሃን</u>** ተብሏል፡፡ በቁርዓን ውስጥ ከአላህ ዘንድ የተላኩ ነብያቶችና እንዲሁም የወረዱት መጽሃፍቶች **<u>ብርሃን</u>** ተብለው

ተጠርተዋል፡፡ በሱረቱል አንዓም 6÷104 ከጌታችሁ ዘንድ **<u>ብርሃኖች</u>** በእርግጥ መጠላችሁ የተመለከተም ሰው (ጥቅሙ) ለነፍሱ ብቻ ነው፤ የታወረም ሰው (ጉዳቱ) በራሱ ላይ ብቻ ነው፤ እኔም በናንተ ላይ ጠባቂ አይደለሁም (በላቸው)፡፡ አንተ ከመጽኃፍ ቅዱስ ብርሃን የሚለውን ኢየሱስ የአምላክ ልጅ እንደ ሆነ ለማሳየት ሞክረሃል፡ ሌሎች ብርሃን የተባሉትስ ምን ሊሆኑ ነው?

## <u>ኢየሱስ ሙታንን ያስነሳው በራሱ ፍቃድ ነውን?</u>

**አለማየሁ፡**-በዮሃንስ ወንጌል 11÷39 ላይ ክርስቶስ አላዛርን ከሞታ በኋላ አስነስቷል ትደብቃላችሁም እንጂ በቁርዓናችሁም በሱረቱል ኢምራን 3÷49 ላይ ተጽፏል፡፡ በቁርዓን ላይም ሙታንን ያስነሳው በራሱ ፍቃድ ነው ፡፡

**አረብ፡**- አይደለም በቁርዓን በመጽኃፍ ቅዱስም ኢየሱስ ሙታንን ያስነሳው <u>በራሱ ፍቃድ አይደለም</u>; ነው የምትል ከሆንክ መጽኃፍ ቅዱስም ቁርዓንም ይኀው፡ ራስህ የሃንስ ወንጌል 11÷39-41 አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡**-ኢየሱስ ደግሞ ድንጋዩን አንሱ አለ የሞተውም እህት ማርታ ጌታ ሆይ ከሞተ አራት ቀን ሆኖታልና አሁን ይሸታል አለችው፡፡ ኢየሱስ ብታምኚ የእግዚአብሔር ክብር እንድታይ አልነገርኩሽምን? ኣላት ድንጋዩን አነሱት ኢ**<u>የሱስም አይኖቹን ወደ ሰማይ አንስቶ አባት ሆይ ስለሰማህኝ አመሰግለሃለሁ</u>**፡፡ ሁል ጊዜ <u>እንድትሰማኝ</u> አወቅኩ… ነገር ግን አንተ እንደላከከኝም ያምኑ ዘንድ በዚህ <u>ዙሪያ</u> ስለ ቆሙት ህዝብ ተናገርሁ አለ፡፡ ይህ ብሎ በታላቅ ድምጽ አላዛር ሆይ ወደ ውጭ ና ብሎ ጮሀ የሞተውም አላዛር እጆቹንና እግሮቹን

በመግነዝ እንደተገነዙ ወጣ ፊቱም በጨርቅ እንደ ተጠመጠመ ነበር፡ ኢየሱስም ፊቱን ፍቱትና ይሂድ አለ፡፡

**አረብ፡-**ኢየሱስ ወደ ሰማይ ማየቱ ለምን አስፈለገ? አምላክ ከሆነ ራሱ አያስነሳውም?ያስነሳውም በአምላኩ ፍቃድ እንደሆነ ለሁሉም ግልጽ ነው፡፡ ፀሎቱም ተቀባይነት እንዳገኘለት ባየ ጊዜ አባት ሆይ ስለሰማሃኝ አመሰግናለሁ፣ አለ፡ አብ ፀሎቱን ባይሰማ ኖሮ እየሱስ ምን ይሆን ነበር?ቁርአን 3÷49 እንዲህ ይነበባል "ወደ እስራኤልም ልጆች መልእክተኛ ያደርገዋል (ይለዋል) እኔ ከጌታዬ ዘንድ በተዓምር መጣኋችሁ፡ እኔ ለናንተ ከጭቃ እንደ ወፍ ቅርጽ እፈጥራለሁ በእርሱም እተነፍስበታለሁ <u>በአላህም ፍቃድ</u> ወፍ ይሆናል፡ በአላህም <u>ፍቃድ</u> እውር ሆኖ የተወለደን ለምፀኛንም አድናለሁ ሙታንንም አስነሳለሁ፡ የምትበሉትንና በቤታችሁ የምታደልቡትንም ሁሉ እነግራችኋለሁ፡ የምታምኑ እንደሆናችሁ ለእናንተ በዚህ ውስጥ በእርግጥ ተዓምር አለበት፡፡" ታድያ እዝህ ውስጥ ኢየሱስ ሙታንን ያስነሳው በራሱፍቃድ ነው የሚል የት አለ?

**አለማየሁ፡-** ዝም!

**አረብ፡-**ሙታንን የማስነሳት ተዓምር በኢየሱስ አልተጀመረም; በሱረቱል በቀራህ 2÷260 ኢብራሂምም ጌታዬ ሆይ ሙታንን እንዴት ሕያው እንደምታደርግ አሳየኝ ባለ ጊዜ (አስታውስ አላህ)አላመንክምን? አለው፡ አይደለም (አምኛለሁ)ግን ልቤ እንዲረጋጋ ነው አለ፤(አላህም) ከበራሪዎች (ከወፎች) አራትን ያዝ ወደ አንተም ሰብስባቸው (ቆራርጣቸውም)፤ ከዚያም በየኮረብታው ሁሉ ላይ ከነርሱ ቁርጥራጭን አድርግ፤ ከዚያም ጥራቸው፤ <u>ፈጥነው ይመጡሃልና፤</u> አላህም አሸናፊ ጥበበኛ መሆኑን እወቅ አለው፡፡ ወንድሞቼ የአላህ ችሎታ ሰፊ ነው፤ አላህ ለአንድ ሰው ተዓምርን ቢሰጥ እኛ ማድነቅ ያለብን አላህን ነው እንጂ በአላህ ፍቃድ ተዓምር ሰሪውን አይደለም፡፡ አላህ በሱረቱል ረዓድ 13÷38 … ለማንኛውም መልእክተኛ <u>**በአላህ ፍቃድ ቢሆን እንጂ**</u> ተዓምር ሊያመጣ አይገባውም፤ ለጊዜው ሁሉ ጽሁፍ አለው፡ ወደ መጽኃፍ ቅዱስ እንመለስና ከኢየሱስ ውጪ ሙታንን ያስነሱ ብዙ ናቸው፡ መጽኃፈ ነገስተ ካልእ 4÷32 አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡-**የሆነ ቀጠሮ ስላለብኝ መሄዴ ነው፡፡

**ኢብራሂም፡-**ይህ ለመሸሽ የምታደርጉት ፈጠራ ነው; ከዚህ የበለጠ ቀጠሮ አይኖርህም! እውነትም ቀጠሮ ቢኖርህ ኖሮ ውይይቱን ከመጀመርህ በፊት በተናገርክ ነበር፡ ወይም ቅድም ስትሄድ ባልተመለስክ ነበር፡፡

አንድ ሰው፡-ተነሳና አንተነህ እባላለሁ አንተ እስከ አሁን ስትናገር የነበርከው ሃቅ ነው! ሃቅ ስለ መሆኑን አልጠራጠርም ጥቅሶቹንም በሙሉ ይገኛሉ አላማዬ ሃቁን ይገኙ መሞት ስለሆነ እነርሱ ፈርተው ቢሄዱ እንኳ አንተ ትምህርቱን ቀጥልልን፡፡

**ብሩክ፡-** ፈርተን እንኳን አይደለም ብንፈራ ኖሮ ቅድም ባልተመለስን ነበር፡፡

**አረብ፡-** ብትሄዱ እንኳ እኔ ንግግሬን እቀጥላለሁ; ከህዝብ ውስጥ አንድ አንባቢ እፈልጋለሁ ቅድሚያ ግን ለክርስቲያኖች እድል እሰጣለሁ፡፡

**አንተነህ**፡-ተነሳና ወደ መድረክ ወጣ በመጽኃፈ ነገስት ካለዕ 4÷32 ኤልሳእም ወደ ቤት በገባ ጊዜ እነሆ ህፃኑ ሞቶ በአልጋ ላይ ተጋድሞ ነበር፤ ገብቶም በሩን ከሁለቱ በኋላ ዘጋ ወደ እግዚአብሔርም ፀለየ መጥቶም በህፃኑ ላይ ተኛ አፍንጫውንም በአፍንጫው፤አይኑንም በአይኑ ፤እጁን በእጁ ላይ አድርጎ ተጋደመበት የህፃኑምገላ ሞቀ፡ ተመልሶም በቤት ውሰጥ አንድ ጊዜ ወዲህ እና ወዲ ተመላለሰ ደግሞም ወጥቶ ሰባት ጊዜ በህፃኑ ላይ ተጋደመ <u>ህፃኑም አይኖቹን ከፈተ…</u>

**አረብ፡-**መጽኃፈ ነገስተ ካልእ 8÷5 አንብብ

**አንተነህ**፡-እርሱም የሞተውን እንዳስነሳ ለንጉሱ ሲናገር እነሆ <u>ልጇን ያስነሳላት</u> ሴት ስለቤትና ስለመሬቷ ወደ ንጉስ ጮሀች <u>ጌታዬ ንጉስ</u> ሆይ ሴቲቱ ይህች ናት <u>ኤልሳዕም ያስነሳላት</u> ልጅዋ ይህ ነው አለ፡፡

**አረብ፡-**ተከቢር!

**ሙስሊሞች፡-**አላሁ አክበር!

**አረብ፡-**ክርስቲያን ወንድሞቼ እውነት ሃቅ ፈላጊ ከሆናችሁ አትሂዱ፡ 1ኛ መጽኃፈነገስት 17÷20 አንብብ፡፡

**አንተነህ፡-**…እንዲህም ደግሞ አስጨነቀሃትን ብሎ ጮሀ በብላቴና ላይ ሶስት ጊዜ ተዘረጋበት ወደ እግዚአብሔርም አቤቱ አምላኬ ሆይ የዝህ ብላቴና ነፍስ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ እለምነሃለሁ ብሎ ጮሀ እግዚአብሔርም የኤሊያስን ቃል ሰማ የብላቴና <u>ነፍስ ወደ እርሱ ተመለሰች</u>፡፡

**አረብ፡-**የሐዋሪያ ስራ 9÷40 አንብብ፡፡

**አንተነህ፡-**ጴጥሮስም ሁሉንም ወደ ውጭ አስወጥቶ ተንበርክኮም ፀለየ ወደ ሬሳውም ዞር ብሎ ጣቢታ ሆይ ተነሺ አላት እርስዋም አይኖችዋን ከፈተች ጴጥሮስንም ባየች ጊዜ ተቀመጠች፡ እጁንም ለእርስዋ ሰጥቶ አስነሳት፡ ቅዱሳንንና መበለቶችንም ጠራ **ሕያውንም ሆና በፊቱ አቆማት**፡፡

**አረብ፡-**ሐዋሪያ ሥራ 20÷9-11 አንብብ፡፡

**አንተነህ፡-**አውጤኪስ የሚሉትም አንድ ጎበዝ በመስኮት ተቀምጦ ታላቅ እንቅልፍ አንቀላፍቶ ነበር፡ ጳውሎስም ነገሩን ባስረዘመ ጊዜ እንቅልፍ ከብዶት ከ 3 ኛው ድርብ ወደ ታች ወድቆ **ሞቶም አስነሳው**፡፡

**አረብ፡-** እነዚህ አሁን ያየናቸው በሙሉ ሙታንን አስነስቷል፡፡ አብረሃም፣እየሱስ፣ኤልሳእ፣ኤሊያስ፣ጴጥሮስ፣ጳውሎስ ሁሉም አማልክት ናቸው ማለት ነውን?

**አንተነህ፡-**እነዚህ ሁሉማ እንዴት አማልክት ይሆናሉ?

**አረብ፡-** በሱረቱል ኢምራን 3÷73 "... መምሪያው የአላህ መምሪያ ብቻ ነው በላቸው፤ ችሎታውም በአላህ እጅ ነው ለምሻው ይሰጠዋል፤ አላህም ችሮታው ሰፊ አዋቂ ነው በላቸው"፡፡ በሱረቱል ሀዲድ 57÷29 (ይህን) የመጽኃፉ ሰዎች (አይሁዶችና ክርስቲያኖች) ከአላህ ችሮታ በምንም ላይ የማይችሉ መሆናቸውን ችሮታም በአላህ እጅ ነው፤ ለሚሻው ሰው ይሰጠዋል ማለትን እንዲያውቁ ነው፤ አላህም የታላቅ ችሎታ ባለቤት ነው፡፡ የመሪዎቻችን ትምህርት እንጂ የመጽኃፍ ቅዱስንና የቁርዓንን ትምህርት አንቀበልም የምትሉ ከሆነ መብታችሁ ነው፡ መጨረሻችሁ ግን በሱረቱል አህዛብ 33÷66-68 ፊቶች በእሳት ውስጥ በሚገላበጡበት ቀን ዋ ምኞታችን! አላህን በታዘዝን፤ መልእክተኛውንም በታዘዝን ኖሮ እያሉ ይፀፀታሉ፡፡ ይላሉም ጌታችን ሆይ እኛ ጌቶቻችንና ታላላቆቻችን ታዘዝን መንገዱንም አሳሳቱን፡፡ ጌታችን ሆይ ከቅጣቱ (እኛን ከምትቀጣን) እጥፍን ስጣቸው ታላቅን እርግማንንም እርገማቸው፡፡ ያ ቀን ከመምጣቱ በፊት ዛሬውኑ ሃቁን ፈልጉ፡ ትንቢተ ኢሳያስ 3÷12 አንብብ፡፡

**መስፍን፡-ወደ መድረክ ተመልሶ** እኔ አነባለሁ፡፡

**አረብ፡-** እሺ አንብብ፡፡

**መስፍን፡-**ህዝቤ ሆይ! የመሩአችሁ ያስቷችኋል የምትሄዱበትንም መንገድ ያጠፉሉ፡፡

**አረብ፡-**ይህ ጥቅስ በ 1980 ትርጉም... ህዝቤ ሆይ መሪዎቻችሁ

የሥቷችኋል የምትሄዱበትንም ያጣምማሉ፡ ስለዚህ
የያዛችሁት መንገድ ተጣሟል፡፡ ያልተጣመመውን ከኛ
ጋር እስልምናን ተከተሉ ብለን ጥሪ እናደርጋለን፡፡

## እውን ገነትና ገሃነም የሉምን?

**ገረመው፡-**እጁን አወጣና እኔ ገረመው እባላላሁ፡ ድሮ ክርስቲያን ነበርኩ አሁን ግን የኦሾ ተከታይ ነኝ; ገነትም ገሃነምም የሉም፡ ለምን አልኖሩም ካልክ፡ ክርስቶስ በዮሃንስ ወንጌል 11÷25 በእግዚኣብሔር ያመነ ቢሞት እንኳ ወደ ህይወት ተሸጋገረ እንጂ አይሞትም ይላል፡ ያ መለት በፈጣሪ ያመነ ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ህይወት ወይም ገነት ገባ ማለት ነው; ክርስቶስ አላዛርን ከሞት ሲያስነሳው በዮሃንስ 11÷38-43 አላዛር ለ 4 ቀናት መቃብር ውስጥ ነበር፡ ለ 4 ቀናት ሙሉ ነፍሱ የት እንደነበረች ገነት ገባሁ ወይም ገሃነም ገባሁ ብሎ ለህዝቡ ምንም የተናገረ ነገር የለም፡ ገነትና ገሃነም ቢኖሩ ኖሮ እርሱ ሞትን ያየ በተናገረ ነበር፡ ስለሌሉ ነው እንጂ ቢኖሩ ኖሮ በተናገረ ነበር፡ ዝምብላችሁ ትለፋላችሁ እንጂ ገነትና ገሃነም አሉ የሚል በእኔ ዘንድ ተቀባይነት የለውም፡፡

**አረብ፡-**ትልቁ የአንተ ማስረጃ ይህ ነው?

**ገረመው፡**-አዎ! ከዝህ በላይ ምን ትፈልጋለህ?

**አረብ፡**- መጀመሪያ አላዛርን በሞትክ ጊዜ ነፍስህ የት ነበረች ብሎ ማን ጠየቀው? ተጠይቆ እውነትም ገነትም ገሃነምም የሉም ቢል ኖሮ በተጠራጠርክ ነበር፡ነገር ግን አልተጠየቀም፡ ተጠይቋል የሚል ማስረጃ ካለህ አምጣ!

**ገረመው፡**-ሙሉ መጽኃፉን አንብቤያለሁ በእርግጥ ተጠይቋል የምል አላየሁም፡፡

**አረብ፡**-ታዲያ እርሱ አልተናገረም ብለህ ገነትም፡ገሃነምም፡ የሉምብለህ መከራከር አትችልም፡**2 ኛ** አንተ ክርስቶስ በአላህ ፍቃድሙታንን እንዳስነሳ ታምናለህ አይደል?

**ገረመው፡**-አዎ አምናለሁ፡፡

**አረብ፡**-ኢየሱስ በአላህ ፍቃድ ሙታንን ማስነሳቱን ካመንክ አላህ መኖሩንም እያመንክ መሆንህንም እወቅ! ታድያ አላህ መኖሩን ካመንክ

ገነትና ገሃነምም በፈጣሪ ዘንድ ትንንሽ ነገሮች ናቸው፤ አላህ ይሰራቸዋል፡፡

**ኢብራሂም፡**-ተክቢር!

**ሙስሊሞች፡**-አላሁ አክበር!

**አረብ፡-** እኔ ሃይማኖት ከሌላቸው ሰዎች ጋር ብዙን ጊዜ እወያያለሁ፤ ከሞትን በኋላ አንቀሰቀስም እያሉ ከኔ ጋር ይከራከራሉ ገነትንና ከሃነምም የሉም ይላሉ፡ ገነትና ሀሃነምም የሉም ብሎ የሚከራከር ሰው የትንሳኤ ቀን መቀስቀሱን የማያምን ሰው ነው፡ አንድ ሰው ከሞትኩ በኋላ አልቀሰቀስም የሚል ከሆነ መጀመሪ ከየት መጣህ; ማን ፈጠረህ? ..... ታድያ ፍጡርን ከእምንት ያስገኘውን ጌታ ነገ አጥንቶቻቸውን መቀስቀስ ምን ይከብደዋል? በሱረቱል መሪየም 19÷66-67 ሰውም በሞትኩ ጊዜ ህያው ሆኜ (ከመቃብር) እወጣለሁን? ይላል፡፡ ሰው ከአሁን በፊት ምንም ነገር ያልነበረ ሲሆን እኛ የፈጠርነው መሆኑን አያስታውስምን? ታድያ ያልነበርን የፈጠረንን ጌታ ነገ በቂያማ(በትንሳዔ) ቀን እኛን መቀስቀስ ምንም አይከብደውም፡፡ በሱረቱል ኢብራም 14÷20 <u>"ይህ በአላህ አስቸጋሪ አይደለም፡፡"</u> ታድያ ለአላህ ምን ይሳነዋል?

**ሙስሊሞች ፡**- ምንም አይሳነውም!!

**አረብ፡**-በሱረቱል ሉቅማን 31÷28 እናንተን መፍጠርና እናንተን <u>መቀስቀስ እንደ አንዲት ነፍስ እንጂ ሌላ አይደለም</u> አላህ ሰሚ ተመልካች ነውና፡ ገነት መኖሩን ያለመንከበት ምክንያት መቀስቀስህን ስለማታምን ነው፡ የአሾ (ራጅኒሽ) አቋሙ ይህ ነበር፡ አሁንስ ምን ትላለህ?

**ገረመው፡**-እስከ አሁን ምን ነው ዝም አለችሁን? ስምንት ዓመት ሙሉ መልስ ያላገኘሁለት ጥያቄ ገና ዛሬ ተመለሰልኝ፡ ማስረጃችሁም ሎጂካችሁም በሙሉ አሳማኝ ናቸው; ጊዜ ስጡኝና ከሰሞኑ ፈጣሪ ካለ እስልምናን እቀበላለሁ፡፡

**ኢብራሂም፡**-አላሁ አክበር! ማስረጃችን አሳማኝ የሆነበት ትልቁ ምክንያት የአላህን ገመድ <u>የማይበጠሰውን</u> ስለ ያዝን ብቻ ነው፡ አላህም የምያውቃት ኃይማኖት በሱረቱል ኢምራን 3÷19 <u>እስልምና ብቻ ነው</u>፡፡

**አረብ፡**-ሃቅ ፈላጊ ማለት ለጥያቄው መልስ ሲሰጥ ወደ ኋላ የማይመለስ ነው፡ እስላምን ለመግባት ሁለት ቃላቶች ብቻ ናቸው የሚያስፈልጉህ፡ እነርሱም ከአላህ በቀር ሌላ በእውነት የሚገዙት አለመኖሩን እና

ነቢዩ ሙሐመድ (ኢ.ሰ) የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን መመስከር ብቻ ነው፡፡

**ገረመው፡**-ታድያ ይህ ብቻማ ከሆነ ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ ነቢዩ ሙሐመድም እውነተኛ የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን አምናለሁ፡ እውነተኛ ነብይ ባይሆኑ ኖሮ ዛሬ ሙስሊሞች የያዛችሁት ማስረጃ ቁርዓን ውሸት በሆነ ነበር፡ እኔ ቁርዓንንም ትንሽ አንብቤ ነበር ባነበብኩት ውስጥ አንድ ውሸት እንኳን ላገኝ አልቻልኩም፡ ፕሮቴስታንቶች በየመንገዱ እየቆሙ ለሰው ስለሀይማኖታቸዉ እንደሚያስተምሩ ሁሉ እናንተ ሙስሊሞችም ቁርዓንን ለህዝቡ እንድታስተምሩ እላለሁ፡፡

**አረብ፡**- ሃቅ ላይም በተገኘች ጊዜ መንጠልጠል ነው፡ ወደ ኢስላም ኡንኳን በሰላም መጣህ መስፍን አንተስ?

**መስፍን፡**-ገረመውንም አሳስተሃዋል እናንተ ሙስሊሞች አሳሳቾች ናችሁ!

**አረብ፡**-አላማችሁ ሙስልምን ማጥፋት ነው እንጂ ሃቁን ለማወቅ አይደለም፡ ምክንያቱም ገረመው ከመስለሙ በፊት የኦሾ ተከታይ እንደሆነ ተናገረ፡ የዛኔ ከፊትህ ጥሩ ገጽታ ይታየኝ ነበር; ነገር ግን እርሱ ኢስላምን ስለተቀበለ ፊትህን ቀየርከው ከኢስላም የጠላችሁት ነገር ምንድን ነው?

**መስፍን፡**-ዝም

**አረብ፡-**ስለ ኢስላም የናንተ መሪዎች ጥሩ አመለካከት እንዳይኖራችሁ የሚያደርጉት እንደሆነ እናውቃለን፡ የነሱስ ችግር ምንድን ነው?

## <u>አርባ ቀንና ለሊት ብፆምስ?</u>

**አለማየሁ፡-** በማቴዎስ ወንጌል 4÷4 እየሱስ <u>አርባ ቀንና ለሊት መፆሙ</u> ራሱ አምላክ ያደርገዋል፡

**አረብ፡-**ያንተስ ነገር በጣም ይገርማል አንዴ ትመጣለህ አንዴ ትሄዳለህ፡ አሁንም የቀረ ነገረ አለህ? **<u>አርባ ቀንና አርባ ለሊት ከፆመ</u>** በኋላ ተራበ አይደል? ለመሆኑ አምላክን ይርበዋል?

**አለማየሁ፡**-ዝም

**አረብ፡**-የሙስሊሞቹ ጥያቄ መፆሙ ጋር ሳይሆን <u>መራቡ ጋር ነው</u>፡፡ አርባ ቀን የፆሙማ ብዙ ናቸው፡ በሱረቱል አእራፍ

7÷142 ሙሳንም <u>ሰላሳን ለሊት (ልፆምና</u> ልናነጋግረው ቀጠርነው) በአስርም ለሊት (አርባ ቀናት) ሞላናት የጌታውም ቀጠሮ አርባ ለሊት ሲሆን ተፈፀመ… እንዲሁም በሱረቱል በቀራህ 2÷51 ያለውን ማንበብ ትችላላችሁ፡ 1ኛ መጽኃፈ ነገስት 19÷7 እንኩ አንዳችሁ አንብቡ፡፡

**ብሩክ፡**-… የእግዝአብሔር መልአክ ደግሞ ሁለተኛ ጊዜ ዳሰሰውና የሚትሄድበት መንገድ ሩቅ ነውና ተነስተህ ብላ አለው፡ ተነስቶም በላ ጠጣ በዚያ ምግብ ኃይል እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ ድረስ **<u>አርባ ቀንና አርባ ለሊት</u>** ሄደ፡፡

**አረብ፡**- አንድ ቀን በበላ ምግብ አርባ ቀንና አርባ ለሊት የተጓዘ ሰው ነው ወይስ፡ አንድ ቦታ ተቀምጦ የፆመ ሰው ነው ይበልጥ የሚደከመው? ይህንን እናንተው ፍረዱት፡

ሙሴም በኦሪት ዘፀዓት 34÷28 <u>አርባ ቀንና አርባ ለሊት</u> እንደፆመ ተጽፏል፡ ታድያ ክርስቶስ አርባ ቀንና አርባ ለሊት መፆሙ ምን ይገርማችኋል?

**ብሩክ፡-** ኢየሱስ እኮ በልቶ ጠጥቶ ይህን ሁሉ ማድረጉ እኛን ለማስተማር ነው፡፡

**አረብ፡**-ከኢየሱስ በፊት ሰዎች መብላትንና መጠጣትን አያውቁም ነበር ማለትህ ነውን?’’ ታዲያ እየበላና እየጠጣ ካልበላ ወደ የሚርበው አምላክ ሙስሊሞችን ስትጠሩ ትንሽ እንኳን አታፍሩም? በሱረቱል አንዓም 6÷14 "ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ ከሆነው አላህ እርሱ የሚመግብ ሲሆን (ለራሱ) <u>የማይመገብ</u> ሲሆን ሌላን አምላክ እይዛለሁን…**?**" ማንም ሙስሊም አይሰማችሁም ማህበራችሁ ሁሌ ስለ እርሱ የምታወሩት ከቁርዓን የሚያስተምሩትን ነገር አሁን ህዝብ ፊት ለፊት ለምን አታወጡትም? ማህበራችሁስ ስያስተምር ሙስሊም ክርስትያን ውይይት ብሎ ሙስሊሞችንም ጠርቶ ህዝብ በተሰበሰበበት ከሙስሊሞች ጋር ለምን አይወያዩም? ሁሌ በቤተክርስቲያን ውስጥ ጉባዔ እያሉ እያዘጋጁ ክርስቲያኖች ስለ ኢስላም መጥፎ አመለካከት እንዲኖራቸው ማስተማራቸው በመላ ኢትዮጵያውያን ውስጥ መርዝ መርጨት ነው፡ እንደ ሀገራችን ህገ-መንግስት ግን መብት ኣለቸው፡ አሁን ደግሞ እኔ አዲስ ርእስ ልክፈት ፍቃደኛ ናችሁ?

**እነ ብሩክ፡-**አዎ!

## <u>እነዚህ የአምላክ ባህሪያት ናቸውን?</u>

**አረብ፡**-አምላክ ያንቀላፋል"?

**ብሩክ፡**-አምላክ አንያቀላፋም"? ኢየሱስ እኮ እኛን ለማስተማር ብሎ ነው ያንቀላፋው እንጂ አምላክ እማ አያንቀላፋም ፡፡

**አረብ፡**-ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት ሰዎች መተኛትንም ሆነ ማንቀላፋት አያውቁምን?

**ሙስሊሞች፡**- አላሁ አክበር!-

**አለማየሁ**:-መዝሙረ ዳዊት 120(121)÷ 1-4 ፡፡

አይኖቼን ወደ ተራሮች አነሳሁ ረዳት ከወዴት ይመጣል? ረዳቴ ሰማይና ምድርን ከሰራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፡፡ አባርህን ለመናወጥ አይሰጠውም የሚጠብቅህ **<u>አይተኛም</u>** እነሆ እስራኤልን የሚጠብቅ **<u>አይተኛም አያንቀላፋም፡፡</u>**

**አረብ**:-ኢየሱስ በማርቆስ ወንጌል 3÷38 <u>ተኝቶ</u> ነበር፡ ታዲያ አምላክ <u>አይተኛም</u> የተባለው ነዉ; ወይስ <u>የተ**ኛዉ ኢያሱስ ነዉ**</u>? ቅዱስ ቁራን 2÷255 አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም ህያው ራሱን ቻይ ነው፤ <u>ማንገላጀትም እንቅልፍም</u> አይዘውም በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የእርሱ(ፍጡር) ብቻ ነው…፡፡ በየታከሲውና በየግርግዳው ላይ ድንግል ፈጣሪዋን ወለደች እያሉ ይፅፋሉ ለመሆኑ አምላክ እናት አለው?

**አለማየሁ**:-ድንግል ፈጣሪዋን ወለደች የሚል ሉቃስ ወንጌል 1÷31-35 ላይ ተጽፏል፡፡

**አረብ** :- እስቲ ሙሉ ቃሉን አንብበው፡፡

**አለማየሁ**:-እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅን ትወልጃለሽ <u>ስሙንም ኢየሱስ</u> ትይዋለሽ…

**አረብ**:-ታድያ ድንግል <u>ፈጣሪዋን ወለደች የሚል ቃል የ</u>ት አለ?

**አለማየሁ**: በመንፈስ ካልሆነ አይገባህም፡፡

**አረብ**:-አማርኛው ግልጽ አማርኛ ነው፡ ለናንተ ከገባችሁ አስረዱን፡ ለመሆኑ አምላክ በ1ኛ መጽኃፈ ነገስት 8÷27 ሰማያት እንኳ የማይበቃውን አምላክ የትኛው <u>ማህፀን ነው እርሱን የሚሸከመው</u>? መጽኃፍ ቅዱስ እንኳ በናንተ ላይ እየመሰከረ ነዉ።

**አለማየሁ**:-ከትንሽ ዝምታ በኋላ ቁርዓናችሁ እንደሚለው ከሆነ በሱረቱል ማኢዳ 5÷116 ክርስቲያኖች ኢየሱስንና ማሪያምንም አማልክት አድርገው እንደያዙት አድርጎ ያስተምራል፡ እኛ እየሱስን እንጂ ማሪያምን አምላክ አድርገን አልያዝናትም;ታድያ ቁርዓን እዛ ጋር አልተሳሳተም?

**አረብ**:-እናንተ ማርያምንም ጭምር ባትሉ እንኳ የምሉ ቡድኖች አሉ፡፡ ዘ ኒው ኢንሳይክሎፒዲያ ቢሪታኒካ (1988) ጥራዝ 16 ገጽ 326 እና 327 "ለአምላክ እናት አምልኮ አካል ክብር በመስጠት ይበልጥ የተስፋፋው … አረማዊ አምልኮ ይከተሉ የነበሩ ሰዎች ወደ ቤተክስቲያን በጎረፉበት ወቅት ነው፡፡… (ወደ ክርስትና የተለወጡት አረማውያን እንዲህ ያለውን) የአምልኮ ቅንዓትንና ሃይማኖተኝነትን ያዳበሩት ለሺህ ዓመታት‘ታላቋ እናት’ የተባለችውን <u>ሴት አምላክ አድርገው ያመልኩ በነበረበት ወቅት</u> ነው፡፡" ስለዚህ እናንተ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሶች አምላክ ናት ባትሉ እንኳ ሌሎች የሚሉ ስላሉ ነው; አሁን ራሱ ብዙ የሀገራችን ኦርቶዶክሶች በትንቢተ ኢሳያስ 60÷14 <u>የናቁሽ ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ፡</u> የሚለውን የመጽኃፍ ቅዱስ አንቀጽ ይወስዱና ብዙን ጊዜ ይህ የተባለው ለድንግል ማርያም ነው ይላሉ፡ ታዲያ ስግደት የሚገባው በማቴዎስ ወንጌል 4÷9 ለፈጣሪ ብቻ እንደሆነ ተገልጿል፡ ለማርያምም ይሰገዳል ከተባለ ስለዚህ እርሷም አምላክ ናት ማለት ነው፤ እንጂ ቁርዓን አልተሳሳተም፡፡ የኦርቶዶክስ ማህበረ ቅዱሳን ቁርዓን ዋሽቷል ብለው ብዙ መጽኃፍቶችን ጽፈዋል; በመጀመሪያ ስንት የክርስትና ኃይማኖት ድርጅቶች አሉ? ማህበራችሁ ኦርቶዶክሶችን እንጂ መላው የዓለም ክርስቲያን ድርጅቶችን ወክሎ መናገር አይችልም፡፡ እኛ ሙስሊሞችን የአንቀጹ ትርጉሙ ምን እንደሆነ ለመጠየቅም

አልደፈሩም; ቢጠይቁን ኖሮ መልስ ባገኙ ነበር፡፡ ነገር ግን ሆን ብለው ክርስቲያኖች (ኦርቶዶክሶች) እስልምናን እንዲጠሉ ለማድረግ እየጣሩ ነው; ማሪያምም ኢየሱስም ሁለቱም በሰው ማህፀን ውስጥ ተቀምጠው ተወልደው; <u>በተዓምር አማልክት ሊሆኑ አይችሉም</u>፡፡

**አለማየሁ**:-እኛ እኮ ማሪያምን አናመልክም!

**አረብ** :-እያልኩኝ ያለሁትም ይህ ነው; እናንተ ባታመልኩ እንኳ የሚያመልኩ ወገኖች ስላሉ ነው፡፡ አሁን የጠቀስኩትን ኢንሳይክሎፒዲያን አንብቡ; ማህበራችሁ ሆን ብሎ የተሳሳተ መረጃ ጽፎ መበተኑ በጣም ያስጠላል።

**አለማየሁ**:-በሱረቱል ኢምራን 3÷42 ላይ ማርያም ተመርጣለች ስለዝህ <u>ታማልዳለች</u> ኣታማልድም የምትል ከሆንክ ፤ ታዲያ ለምን ተመረጠች?

**አረብ**:-በዚሁ ምእራፍ 3÷3 አላህ አደም፤ኑህ፤የኢብራሂም ቤተሰብ፤የኢምራን፤ቤተሰብም በኣለማት ላይ<u>መርጠ</u>፡፡ በሱረቱ ጣሃ 20÷41 <u>ሙሳም ተመረጦዋል እ</u>ነዚህም ያማልዳሉ ማለትህ ነው? <u>ታማልዳለች የሚል ቃል የታለ?</u>

**እንዲሁም በሁዲስ ሰሂህ ቡኻሪ ቅጽ 4 መእራፍ 178 ቁጥር 290 ነቢያችን (ሰ.ኢ.ወ) መረየም ና ከዲጃም(ረ.አ) ተመርጧ በለዋል… ሲላዚህ እነሱም ያማልዳሉ ማለትህ ነዉን? ሰሂህ ቡኻሪ ቅጽ 4 መእራፍ 4 ቁጥር 642 … መሪየም የተመረጠችዉ በዘመኗ ነበር፣ ኸዲጃም የተመረጠችዉ በጊዜዋ ነበር … ። ታዲያ እነዝህስ ለምን ተመረጡ?**

**አለማየሁ**:-ዝም!

**ሙስሊሞች** :-አላሁ አክበር!

**አረብ**:-ገና በአላህ ፍቃድ ሁሉም ወደ ኢስላም ኢብረሂም ና እነዚህን ሸሃዳ አስይዛቸዉ፡ **አለማየሁ** ሉቃስ ወንጌል 18÷18 አንብብ

**አለማየሁ፡**-ከአለቆችም አንዱ ቸር መምህር ሆይ የዛላለምን ህይወት እንድወርስ ምን ላድርግ? ብሎ ጠየቀው

ኢየሱስም <u>ስለምን ቸር ትለኛለህ ?</u> ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር <u>ቸር ማንም የለም፡፡</u>

**አረብ** ፡- ኢየሱስ ቸር ካልሆነ አምላክነቱ ምኑ ጋር ነው?

**አለማየሁ**፡-ኢየሱስ እኮ ራሱን ዝቅ ለማድረግ ነው እንጂ እሱ ቸር ነው፡፡

**አረብ**፡-እንደዚያ የሚል የት አለ? አምላክ ራሱን ዝቅ ካደረገ ራሱን ከፍ የሚያደርግ ማን ነው? ይህ ሁሉ የምታደርጉት ሃቋን ላለመቀበል ነው ብትለፉም ሃቋ ትወጣለች፡፡

**አለማየሁ**፡-ዝም

**አረብ**፡-ሉቃስ ወንጌል 2÷21 አንብብ፡፡

**አለማየሁ**፡-አቃታለሁ፡፡

**አረብ**፡-አንብብ አልኩህ እንጂ እንደምታውቅ አልጠየቅኩህም፡፡

**አለማየሁ**፡-<u>ሊገርዙትም</u> ስምንት ቀን በሞላ ጊዜ በማህፀን <u>ሳይገረዝ</u> በመልዓኩ እንደተባለ ስሙም እየሱስ ተብሎ ተጠራ…

**አረብ**፡-ሰዎች ለመሆኑ አምላክ ይገረዛል እንዴ?

**ሙስሊሞች**፡-አምላክእማ እንዴት ይገረዛል?

**አረብ**፡-እዛ ጋ! አትረብሹን መወያየት የሚፈልግ ሰው ካለ መድረኩ ክፍት ነው; ወደ አንተ ልመለስና ለመሆኑ አምላክ ይደክማል እንዴ?

**አለማየሁ**;-በትንቢተ ኢሳያስ 40÷28 እግዚአብሔር የዘለዓለም አምላክ የምድር ዳርቻ ፈጣሪ ነው፤ <u>አይደክምም</u> ፡፡

**አረብ፡-**ዮሃንስ ወንጌል 4÷6 አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡-**ኢየሱስም መንገድ **<u>ከመሄድ ደክሞ</u>** በጉድጓድ አጠገብ እንዲህ ተቀመጠ ጊዜው ስድስት ሰዓት ያህል ነበር፡፡

**አረብ፡-**ታድያ አምላክ እየሱስ ነው ወይስ እግዚአብሔር ነው? ይህን እንኳን ሳትለዩ ሙስሊሞችን ለማሳሳት የምታደርጉት ሩጫችሁ በጣም ይገርማል!

**ብሩክ፡-**ኢየሱስ የደከመው ሥጋ ለባሽ ስለሆነ ነው፡፡

**አረብ፡-**አንድ ሰው ለምሳሌ አይበላም ብለን የበላው ግን ስለራበው

ነው ብንል ምንኛ ንግግር ነው? *ሥጋ* ለባሽ ስለሆነ ሳይሆን
የደከመው <u>ሰው ስለሆነ</u> ነው።

**ኢብራሂም:-**ተከቢር!

**ሙስሊሞች:-**አላሁ አክበር!

**ብሩክ:-**ኢየሱስ እኮ ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ ነው።

**አረብ** :-እርሱ የጳውሎስ ትምህርት ነው እንጂ የነቢያትም ሆነ የኢየሱስ ትምህርት አይደለም! የጳውሎስ ትምህርት ከመጽኃፍ ቅዱስ ትምህርትና ከነቢያቶች ትምህርት ጋር ይቃረናል; እርሱንም በሌላ ርእስ <u>እግዚአብሔርን በውሸት ማምለክ</u> በምለው እንመጣበታለን፡ እስቲ እንበልና አንድ ሰው ከሰው ሁሉ ውስጥ ጥቁር ነው ብለን ተመልሰን ከሰው ሁሉ እርሱ ነጭ ነው ብንል ይህ ነገር አይቃረንም? እነዝነህ እንኳ ይህን ያህል የሚቃረኑ ከሆኑ፡ መቶ እጅ ፈጣሪ መቶ እጅ ደግሞ ፍጡር ምን ማለት ነው? <u>አሲድ *(ACID)*</u> ና <u>ቤዝ *(BASE)*</u> ተቃራኒ ናቸው አሲድንና ቤዝን አንድ ላይ ብንጨምራቸው (NEURTAL) ኒዉትራል ይሆናሉ ስለዚህ 100% ፈጣሪ + 100% ፍጡር አንድ ላይ ብንደምራቸው እየሱስ ፍጡርም ፈጣሪም አይደለም እንደ ማለት ነው፡ ታድያ ኢየሱስ ፍጡርም ፈጣሪም ካልሆነ ምን ሊሆን ነው?

**ብሩክ፡-**ዝም

**አለማየሁ፡-**በዮሃንስ ወንጌል 1፥1-3 በመጀመሪያ ቃል ነበር ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ቃልም እግዚአብሔር ነበር፡ ስለዚህ ቃሉ ኢየሱስ ነውና እየሱስ አምላክ ነው።

**አረብ፡-**ይህ ጥቅስ ለአንተም አልገባህም ቢገባህ ኖሮ ባልጠቀስከው ነበር።

1. በመጀመሪያ ቃል ነበር ስትል <u>ከሁሉም ነገር በፊት ቃል ይቀድማል</u> ማለት ነው። ተመልሶ እዛው ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ይላል፤ <u>ቃል ይቀድማል ወይስ እግዚአብሔር ይቀድማል?</u>
2. በአንደኛ ቆሮንጦስ 3፥23 … ሁሉ የናንተ ነው እናንተም የክርስቶስ ናችሁ <u>ክርስቶስም የእግዚአብሔር</u> ነው። ቃል የተባለው ኢየሱስ ነው፡ እየሱስ ደግሞ አሁን ባነበብነው ጥቅስ ላይ የእግዚአብሔር ተብሏል፡ስለዚህ በዮሃንስ ወንጌል

1÷1-3 ቃልም እግዚኣብሔር ነበር ሳይሆን ቃልም <u>የእግዚኣብሔር</u> ነበር የሚሆነው፡ ስለዚህ የ የምትል ፊደል ከዚያ ቀርታለች፡ የ የምትል ፊደል ካስገባን ቃሉም <u>የእግዚኣብሔር</u> ነበር የሚል ይሰጠናል፡ የእግዚኣብሔር ቃል ደግሞ እግዚኣብሔር ሊሆን አይችልም፡ አይደለም የእግዚኣብሔር ቃል እግዚኣብሔርን ሊሆን ቀርቶ፤ የአንተ ቃልም አንተን ሊሆን አይችልም፡፡

ሁለቱም፡-ዝም

አረብ፡-በሱረቱ አል በቀራህ 2÷117 ሰማያትንና ምድርን ያለ
ብጤ ፈጣሪ ነው፤ነገርንም (ማስገኘት) ባሻ ጊዜ ለእርሱ
የሚለው <u>ሁን ነው</u> ወዲውም ይሆናል፡፡ እናንተ እግዚኣብሔር ነው
ያላችሁት ቃል የፈጣሪ <u>ሁን</u> የሚል ቃሉ ነው፡ ፈጣሪ ብዙ
ቃላቶችን ተናግሯል ታድያ ቃላቶቹ በሙሉ አማልክት ናቸው
ማለትህ ነውን?

አለማየሁ፡-ፈጣሪ ካልገለፀላችሁ አይገባችሁም፡፡

አረብ፡-ለናንተም ስላልገባችሁ ነዉ እንጂ ይህ ሰውን ለማሳመን ይበቃል ብላችሁ ባላቀረባችሁ ነበር፡ በዮሃንስ ወንጌል 1÷18 አንብብ

አለማየሁ፡-መቼም ቢሆን <u>እግዚኣብሔርን ያየ አንድ ሰው እንኳን የለም፡፡</u>

አረብ፡-አሁንም በዮሃንስ ወንጌል 5÷37 ያለውን አንብብ፡፡

አለማየሁ፡-የላከኝ አብን እርሱ ስለ እኔ መስክሯል፡፡
ድምጹንም <u>ከቶ አልሰማችሁም መልኩንም አላያችሁም…</u>፡፡

አረብ፡-ኢየሱስ እንግዲህ፤ታይቷል፤ተወልዷል፤ተርቧል፤
ተወግሯል፤ተተፍቶበታል፤ተሰቅሏልም ጭምር
ተብሏል፡ ይህን ሁሉ የጠቀስኩት መታየቱንና አምላክ
አለመሆኑን ለመጠቆም ነው፡ <u>የማይታይ ፈጣሪ ጌታችን</u>
<u>አላህ ነው፡</u> በሱረቱል አንዓም 6÷103 አይኖች
<u>አያገኙትም(አያዩትም)</u> እርሱ (አላህ) አይኖችን
(ሁሉ)ያያል፤ እርሱም ርህራሄው ረቂቁ ውስጠ አዋቂ ነው፡፡

ከህዝብ፡-ውስጥ አንዱ ተነሳና መጽኃፍ ቅዱስ የማያውቁትን
ክርስቲያኖች ትጠሩና ታሳስታላችሁ፡ እንደዚህ ከምታደርጉ
አዋቂዎችን ለምን አታመጡም?

አረብ፡-እኔን በዚህ ውይይት ላይ ክርስቲያኖች በሙሉ እንደተጋበዙ ነው

የተነገረኝ፤ ነገር ግን፡ የመጡት እነዚህ ብቻ ናቸው፡ ዉይይቱ
አላህ ካለ ነገም ይቀጥላል፡ ያውቃሉ ብለህ የምታዉቃቸውን ይዘህ
መምጣት ትችላለህ፡ ለመሆኑ እርሶ የምን ሃይማኖት ተከታይ ኖት?

ሰውየው፡-እኔ ፕሮቴስታንት ነኝ፡ እናንተ የእየሱስን አምላክነት ባታምኑ እንኳ ነገ እንደሚመጣ ታምናላችሁ አይደል?

አረብ፡-አዎ! የሚመጡት ግን ሁለት መሲሆች ናቸው፡ አንዱ
ሃሰተኛው መሲህ(መሲሁደጃል) <u>አምላክ ነኝ ባይ ነው፡-</u>
ሁለተኛው <u>የአላህ መልእክተኛ</u> የሆኑት ኢሳ (ዐ.ሠ) ናቸው፡፡

ሰውየው፡-ሃሰተኛ ነው የምትሉት አምላክ ነኝ ባዩ ባታምኑም ያመሲህ(መሲሁደጃል) አምላክነቱን ባትቀበሉም የኛ አምላክ ነው ሀሌሉያ!!

ሙስሊሞች፡-በሙሉ ይስቃሉ፡፡

አረብ፡-እባካችሁ አትሳቁ፤ ሰው የመሰለውን መናገር ይችላል፡ ማስረዳት ግን የእኛ ግዴታ ነው፡ ደጃል ኃሰተኛው መሲህን በተመለከተ ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) የመሲሁደጃል ራስ የተቆጣጠረ (ከርዳዳ) ነው፡፡ (አህመድ ዘግቦታል) አሁንም በሌላ ሀዲስ ፤አዋጅ ደጃል አንድ አይኑ የጠፋ ነዉ:ጌታችሁ ደግሞ አንድ አይኑ የጠፋ አይደለም: በአይኖቹ መካከል <u>ك ف ر</u>(ካፊር) የሚል ጽሁፍ ተከትቦበታል: ሁሉም ሙእሚን ያነበዋል፡፡" (ቡኻሪና ሙስሊም) ›

ሰውየው፡-የፀጉሩን ከርዳዳነት አልቀበልህም አንድ አይኑ የጠፋችው <u>ግን በመከራ ጊዜ ሰዎች በመስቀል ላይ ሲወግሩት ነው፡፡</u>

አረብ፡-እንደዚያ የሚል የት አለ? እዚሁ ቆመዉ ለምን ይፈላሰፋሉ? ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) "በኔና በኢሳ መካከል አንድም ነብይ የለም! (ኢሳ ከሰማይ) ይመጣል ስታዩት ትለዩታላችሁ፡ ትከሻው ሰፊ ነው፡ <u>ወደ ቀይና ነጭነት የጋደለ የፊት ገጽታ አለው</u>፡ ቀይም ቀለም የተቀለሙ ሁለት ምሰሶዎች መካከል ይወርዳል፡ እርጥበት ባይኖረውም ፀጉራቸው (ፈሳሽ) የሚያንጠባጥብ ይመስላል፡ ስለዚህ <u>ራስ ከርዳዳው ሃሰተኛዉ መሲህ ነው</u>፡ የሚገደለውም በእውነተኛ የአላህ መልእክተኛ በሆኑት በኢሳ (በእየሱስ) (ዐ.ሰ) ነው፡" <u>ለመሆኑ አምላክ በነብይ ይገደላል?</u>

ሰውየው፡-ከትንሽ ዝምታ በኋላ፤ ገዳዩስ እሱን ከገደለ በኋላ ምን ይሆናል?

አረብ፡- ገዳዩም ነቢያቸን (ሰ.ዐ.ወ) እንዳሉት ይሞታል፡ አላህም በቁርዓን በሱረቱል ኢምራን 3÷185 ነፍስ ሁሉ ሞትን ቀማሽ ናት… ፡፡

አለማየሁ፡-ይህማ አዲስ ነገር ነው፡ የእኛ እየሱስ በኋላ ቢመጣ እንኳ አይሞትም!

አረብ፡-የምትቀበል ከሆንክ አስረደሃለው፡ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ያረገው ከነስጋዉ መሆኑን ታምናለህ አይደል?

አለማየሁ፡-አዎ! ያረገው ከነስጋው ነው፤ የሚመጣውም ከነሥጋው ነው፡፡

አረብ፡-ትክክል ነህ! ነገር ግን አንተ እየሱስ አይሞትም ብለሃል፡ 1ኛ ቆሮንጦስ 15÷50 ላይ እንደተጻፈው ከሆነ ሥጋ መንግስተ ሰማያትን አይወርስም ይላል፡ ክርስቶስ ግን ከአመኑት ጋር ነገ መንግስተ ሰማያትን እንደሚወርስ በዮሃንስ ወንጌል 14÷23 ተገልጿል፡ ክርስቶስ ገነት ለመግባት መጽሃፍ ቅዱስ እንደሚለው ከሆነ የግድ ከሥጋ መለየት አለበት፡ ታድያ የሥጋና የነፍስ መለየት ምን ተብሎ ይጠራል?

አለማየሁ፡-ዝም

አረብ፡-ሰዎች የሥጋ ና ነፍስ መለየት ምን ተብሎ ይጠራል?

ሁሉም፡-"ሞት" አሉ

አረብ፡-ታዲያ ኢሳ ድጋሜ ሲመጣ ይሞታል ብንል የሙስሊሞች ስህተት ምኑ ጋር ነው? ይህን ሁሉ የምትለፉት እየሱስን አምላክ ለማድረግ ነው፡ ነገር ግን አምላክ ራሱ አምላክ ነዉ እንጂ ሰው አምላክ ሊያደርገው አይችልም፡ እንደዚያማ ከሆነ አምላክ ራሱ ፍጡር ነው ማለት ነው፡ በእዮብ 15÷14 እንከ ብሩክ አንተ አንብብ፡፡

ብሩክ፡-ንፁህ ይሆን ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ፃዲቅም ይሆን ዘንድ ከሴት የተወለደ ምንድር ነው? እነሆ በቁድሳን እንኳ አይታመንም ሰማያትን በፊቱ ንፁሃን አይደሉም ይልቁንስ አስፀያፊና የረከሰ ሃጢአትንም እንደ ውኃ የጠጣ ሰው ምንኛ ያንስ…

አረብ፡- ኢየሱስ የተወለደው ከሴት ነው፡ ከሴት የተወለደ ሁሉ ሃጊአተኛ ተብሏል፡ ታድያ እየሱስ ከሴት ተወልዶ እንዴት ቅዱስ አምላክ ሊሆን ይችላል?

መስፍን፡-መጽኃፍ ቅዱስ እኮ ቃል በቃል አይተረጎምም፡፡

አረብ፡- ሁሉም የክርስቲያን ድርጅቶች ትርጉም እያሉ ወደ እሚመቻቸው እየተረጎሙ በሰው ነፍስ ይጫወታሉ፡

(ፕሮቴስታንቶች፣ኦርቶዶክሶች፣ ካቶሊኮች፣የይሖዋን ምስክሮች፣ … ) ሁሉም የእኔ ትርጉም ትክክለኛኛ ነው ይላል፡ ታድያ ለምሳሌ እኔ ክርስትናን ለመቀበል ብፈልግ እንኳ የማንን ትርጉም ልከተል? ይህማ በራሳችሁ ላይ ማሾፍ ነው፡፡

ሁሉም፡-ዝም

አረብ፡- እዮብ 25÷4 አንብብ፡፡

ብሩክ፡-ሰውስ በእግዚአብሔር ፊት ፃዲቅ ይሆን ዘንድ ከሴት የተወለደ ንፁህ ይሆን ዘንድ እንዴት ይችላል?

አረብ፡- ሺህ ጊዜ ብታካብዱ እንኳ ከሴት የተወለደ ፃዲቅ ሊሆን በፍጹም አይችልም፡፡ በተጨማሪም መጽኃፍተ መክብብ 7÷20 አንብብ፡፡

መስፍን፡-ጣልቃ ገባና፤ ታድያ ፃድቅ ሰው ከሌለ በሉቃስ ወንጌል 23÷50 እነሆ በጎና ፃዲቅ ሰው የሸንጎ አማካሪ የሆነ ዮሴፍ የሚባል ሰው ነበር፡፡

አረብ፡-ፃዲቅ ሰው የለም ሲል የነበረውም መጽሃፍ ቁድስ ነው፡ አለ የሚለውም እርሱ ራሱ ነው፡ ይህ አይቃረንም ወይ?

አለማየሁ፡-መጽኃፍ ቅዱስማ አይቃረንም፡፡

አረብ፡- ታዲያ እነዚህን ጥቅሶች አስማማቸው፡፡

ሁሉም፡-ዝም

ኢብራሂም፡-ተክቢር!

ሙስሊሞች፡-አላሁ አክበር!

አረብ፡-መክብብ 7÷20 አንዳችሁ አንብቡት

ብሩክ፡-በምድር ላይ መልካምን የሚሰራ ኃጢአትንም የማያደርግ ፃዲቅ አይገኝምና…

አረብ፡-በሱረቱል ሀሽር 59÷23 እርሱ አላህ ነው ያ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ ንጉሱ ከጉድለት ሁሉ የጠራው የሰላም ባለቤቱ ፀጥታን ሰጪ ባሮቹን ጠባቂ አሸናፊው ሀያሉ ኩሩው ነው አላህ ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ፡፡ታዲያ መመለክ ያለበት ከጉድለት ሁሉ የጠራ አላህ ነውና አላህን እንገዛ፡፡

## ኢየሱስ ነብይ ነው

አረብ፡- አምላካችን የምትሉት ኢየሱስ እኮ የአላህ መልእክተኛ ወይም ነብይ ነው፡፡ በቁርዓን ውስጥ ብዙ ጊዜ ነብይ ተብሏል፡ በሱረቱል መርየም 19÷30 (ህፃኑም) ኢሳም አለ፤ እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ መጽኃፍም ሰጥቶኛል፤ ነብይም አድርጎኛል፡፡ አልኢምራን 3÷49 ፤ አልበቀራህ 2÷87 ፤ አልኢምራን 3÷59፤ ኒሳእ 4÷156-159 ፤ኒሳእ 4÷163 ፤ ኒሳእ 4÷171፤ ማኢዳ 5÷17፣46፣72፣75፤78 እና 110-118፤ አልመርየም 19÷19-37፤ ሙእሚኑን 23÷50 ዙክሩፍ 43÷57-64፤ አልሀዲድ 57÷27 ፤አልሷፍ 61÷6 እና 14 ላይ በግልጽ ነብይ መሆኑን የመርየም ልጅ በተዓምር የተወለደ መሆኑን አላህ ያስተምረናል፡ የናንተ ክርስቲኖች እየሱስ በቁርዓን እንኳን ሳይቀር አምላክ ተብሏል እያሉ ያስተምራሉ፡ ነገር ግን በተጠቀሱት ጥቅሶች ላይ ኢሳ(አ.ሰ) የአላህ መልእክተኛ ብቻ ናቸው፡ የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን የሚጠራጠር አንድም ሙስሊም የለም፡ ታዲያ ሌላ ጊዜ ነብይ አይደለም ሙስሊሞች ይዋሻሉ እያላችሁ የምትበትኑት መስረጃችሁን አሁን አምጡ!

አለማየሁ፡-ርእሱ ይቀየር በመሰቀሉ ዙሪያ እንወያይ!

ኢብራሂም፡-ተከቢር!

ሙስሊሞች፡-አላሁ አክበር!

አረብ፡-እንደ ቅድሙ መድረኩን ለቃችሁ ትሄዳላችሁ እንጂ እኔ ርእሱን አልቀይርም፡፡

ብሩክ፡-ታዲያ ኢሳ ነብይ ነው የሚል መጽኃፍ ቅዱሳችን ውስጥ የት አለ?

አረብ፡-በዮሃንስ ወንጌል 4÷19 አንብብ፡፡

ብሩክ፡-ሴቲቱም ጌታ ሆይ አንተ ነብይ እንደሆንክ ኣያለሁ…

አረብ፡-በዮሃንስ ወንጌል 17÷1-3 አንብብ፡፡

ብሩክ፡-ኢየሱስም ይህን ተናግሮ ወደ ሰማይ አይኖቹን አነሳና እንዲህ አለ፤ አባት ሆይ ሰዓቱ ደርሷል ልጅህ ያከብርህ ዘንድ በሥጋ ሁሉ ላይ ስልጣን እንደ ሰጠሀው ለሰጠሀው ሁሉ የዘለዓለምን ህይወት እንዲሰጣቸው ልጅህን አከብረው እውነተኛ አምላክ አንተ ብቻ የሆንሕ እና አንተ **የላከዉንም ኢየሱስ ክርስቶስን** ያውቁ ዘንድ ይህቺ የዘለዓለም ህይወት ናት፡፡

አረብ፡- 1ኛ አምላክ አንድ አብ ብቻ ነው፡

**2** ኛ እየሱስ የእርሱ መልእክተኛ ነው፡ አሁንም በዮሃንስ ወንጌል 5÷30 ያለውን አንብብ፡፡

ብሩክ፡-እኔ ከራሴ አንዳችን ላደርግ አይቻለኝም እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው <u>የላከኝን</u> ፍቃድ እንጂ…

አረብ፡- 1. ኢየሱስ ከራሱ ምንም ማድረግ ካልቻለ የእርሱ አምላክነት ምኑ ላይነዉ?

**2.** ኢየሱስ መልእክተኛ ነው፡ እርሱ ፈጣሪ ቢሆን ኖሮ እንዴት <u>ይላካል</u>? በመጽኃፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታ ላይ መልእክተኛ ተብሏል፡ በዮሃንስ ወንጌል 6÷14 ፤ በማቴዎስ ወንጌል 21÷10፤ …

**ሰውየው፡**-ኢየሱስ <u>አምላክም ነብይም</u> ነው፡፡

**አረብ፡-እርሶ** ለውይይት ፍቃደኛ ከሆኑ ለምን ወደ መድረክ አይወጡም? ሌላ ጊዜ ቤት ለቤት እያንኳኳችሁ ሙስሊሞቹን የሚታስቸግሩትስ አሁን ወደ መድረክ ለምን አትወጡም? እርስዎ ራሱ ወደ መድረክ ይውጡ፡፡

**ሰውየው፡**-እኔ አልፈልግም! መንፈስ ቅዱስ ከልክሎኛል፡፡

**ኢብራሂም፡**-ቅድምም መስፍን መሸነፉን ሲያይ መንፈስ ቅዱስ ከለከለኝ ሲል ነበር፡ አንተም ጀመርክ? አሁን ከሙስሊሞች ጥያቄ ማምለጥ ያልቻላችሁ ነገ ከፈጣሪ ጥያቄ እንዴት ልታመልጡ ነው? በሱረቱል ቀሰስ 28÷56 አንተ የወደድከውን ሰው ፈጽሞ አታቀናም ግን አላህ የሚሻውን ሰው ያቀናል፡እርሱም ቅኖችን አዋቂ ነው፡፡ ስለዚህ አረብ ምንም ሊያደርግላችሁ አይችልም፡ እባካችሁ በራሳችሁ ላይ አታሹፉ፡፡

**አንዱ ሰዉ፡ እጁን** አወጣ እኔ ክርስቲያን ነኝ ኢየሱስ ነብይ ስለመሆኑ እርግጠኛ ነኝ፡፡

**አረብ፡-** ከክርስቲያን የትኛው ቡድን ነህ?

**ሰውየው፡**-የይሖዋ(YHWA) ምስክር ነኝ፡፡

**አረብ፡**-አዎ እናንተ የኢየሱስን ነብይነት ታምናላችሁ፡ በአላህ ፍቃድ የነቢዩ ሙሐመድንም(ሰ.ዐ.ወ) ነብይነት እንድትቀበሉ ተስፋ እናደርጋለን፡ በክርስቶስ ዙሪያ እናንተ ክርስቲያኖች እንኳ በአንድ ነገር ልትስማሙበት ያልቻላችሁትን እኛን ስትጠሩን ትንሽ እንኳ ለምን አታፍሩም? መጀመሪያ እናንተ ተስማሙ፡፡

**ኢብራሂም፡**-ወንድሜ ለመወያየት ፍቃደኛ ከሆንክ ወደ መድረክ ውጣ፡፡

**አረብ፡**-ተወዉ መብቱ ነው፡ ከፈለገ መጥቶ ይወያይ፡ ካልፈለገ ቆሞ ያዳምጥ፡ ባይገርማችሁ እየሱስ ሙስሊም ነው፡፡

<u>ኢየሱስ ሙስሊም ነው!</u>

**አለማየሁ፡-**አሁንስ አበዛችሁ፡ የቁርዓኑ ኢሳ ሙስሊም ቢሆንም የመጽኃፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ግን ሙስሊም አይደለም፡፡

**አረብ፡-**መጀመሪያ ሙስሊም ማለት ትርጉሙን ታውቃለህ?

**አለማየሁ፡-**ሙሰሊም ማላት ቱርጉሙ ምንድንነዉ?

**አረብ፡-**ሙስሊም ማለት ቃሉ አረብኛ ሲሆን ለፈጣሪ ፍፁም ታዛዥ መሆን ማለት ነው፡በሱረቱል በቀራህ 2÷133 ላይ ተገልጿል፡ ኢየሱስም ለፈጣሪ ፍፁም ታዛዥ እንደ ነበር በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፏል፡ ሙስሊም የሚል ቃል በቁርዓን ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጽፏል፡ ሙስሊም ማለት ፍጹም ታዛዥ እንደሆነ የአረብኛውን መዝገበ ቃላት ከፍታችሁ ማየት ትችላላችሁ፡ በሱረቱል ኢምራን 3÷64፣67፣84፣እና 102 አንዓም 6÷163፤ ሁድ 11÷14፤ ሂጅር 15÷2፤ ነህል 16÷89፤ አንቢያእ 21÷108፤ ሀጅ 22÷78፤ ነምል 27÷81 እና 91 ቀሰስ 28÷52-3፤ አህዛብ 33÷35 ፤ ዙመር 39÷11-12 ፤ ፉሲለት 41÷33፤ ዙክሩፍ 43÷68-69፤ አህቃፍ 46÷15፤ ቀለም 68÷35 ፤ አልጅን 72÷14 ላይ ተጠቅሷል፡ ከመጽኃፍ ቅዱስ ኢብራዊ 5÷7 ትን አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡-**እርሱም (ኢየሱስ) በስጋ ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩሀትና ከእንባ ጋር ፀሎትና ምልጃንም አቀረበ <u>እግዚአብሔርንም ስለመፍራቱ</u> ተሰማለት፡፡

**አረብ፡-**ይህቺኑ ጥቅስ በ1980 ቀለል ባለ አማርኛ መጽኃፍ ቅዱስ ትርጉም አነባታለሁ፡፡ ኢየሱስ ሰው ሆኖ በዚህ ምድር በኖረበት ጊዜ ከሞት ሊያድነው ወደምችል አምላክ በታላቅ ጩሀትና በብዙ እንባ ጸሎትንና ልመናን አቀረበ **<u>በትህትና በመታዘዙ</u>** እግዚአብሔር ጸሎቱን ሰማው፡ እየሱስ በትህትና መታዘዙ ማለት ፍፁም ሆኖ መታዘዝ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ እንደሱ ካልገባችሁ በሌላ መንገድ ላስረዳችሁ፡፡

## <u>1.ዘካ</u>

**አረብ፡-**ኢሳ ዘካ ሲሰጥ እንደ ነበር፡ማንም ሙስሊም አይጠራጠርም ምክንያቱም በሱረቱል መርየም 19÷31 በየትም ስፍራ ቢሆን ብሩህ አድርጎኛል፤ በህይወት እስካለሁ ሰላትን በመስገድ፣ **<u>ዘካንም</u>** በመስጠት አዞኛል፡ በመጽኃፍ ቅዱስ እየሱስ <u>ዘካ *(አስራት)*</u> ሲያዝ እንደነበር ማቴዎስ 23÷23 አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡-**እናንተ ግብዞች ፃፉች ፈሪሳውያን ከአዝሙድና ከእንስላል ከከሙንም <u>አስራት</u> ስለምታወጡ ፍርድንና ምህረትን ታማኝነትንም በህግ ያለውን ዋና ነገርስለምትተው ወዮላችሁ፡፡ <u>ሌላውን ባትተው ይህችን ልታደርጉ ይገባችሁ ነበር፡፡</u>

**አረብ፡-** በ1980 የተተረጓመው እንድህ ይላል፡ እናንተ ግብዞች የሙሴ ህግ መምህራንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ ከአዝሙድ ከእንስላል ከከሙን <u>አስራት ትሰጣላችሁ</u>፡፡ ነገር ግን በህግ ውስጥ የሚገኙትን ዋና ነገሮች ትተዋላችሁ፡፡ እነርሱም ፍርድ፣ምህረትና ታማኝነት ናቸው፡ <u>ያንን ሳትተው</u> ይህንንም ማድረግ ይገባችሁ ነበር፡፡ በብሉ ኪዳን አስራት አወጣጡ ኦሪት ዘ ሌዋውያን 27÷28-30 አሰጣጡ ኢስላም ከሚሰጠው ጋር ተመሳሳይ ነው፡ ዘካ በቁርዓን ውስጥ አላህ አዞናል፡፡ በሱረቱል በቀራህ 2÷43 ሰላትንም ደንቡን ጠብቃችሁ ስገዱ፤ <u>ዘካንም *(ግዴታ ምጽዋትንም)*</u> ስጡ (ለጌታችሁ) ከአገንባሾች ጋር አጎንብሱ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አልበቀራህ 2÷83 እና 110 ፤ ማኢዳ 5÷12 ፤ አእራፍ 7÷156 ፤ ተውባ 9÷11፤60 እና 103 ሀጅ 22÷78 ፣ አልሙእሚኑን 23÷4 ፤ ኑር 24÷56፤ ሩም 30÷39 ፤ ሙዘሚል 73÷20 ፤ አልበይነህ 98÷5 ላይ እኛ ሙስሊሞች ታዘናል፡፡

## <u>2.ፆም</u>

**አረብ፡-** ኢየሱስ በማቴዎስ ወነንጌል 4÷4 ላይ ሲፆም እንደነበር ተጠቅሷል፡ ሁሉም ነቢያቶች በአላህ ያምኑ ነበር፡ እነርሱ የኛ ናቸው እኛም የእነርሱ ነን፡ በሱረቱል በቀራህ 2÷285 በአንድም ነብይ አንነጣጠልም፡ በአልበቀራህ 2÷183-185፣187፣196፤

አልኒሳእ 4÷92፤ ማኢዳ 5÷89፤ አህዛብ 33÷35 ላይ ታዘናል፡፡ እኛ <u>የምንፆመው ለፈጣሪ ብቻ</u> ነው፡፡

**አለማየሁ፡-**መድረኩን የራስህ ብቻ አድርገህ በኛ ላይ ጫና እየፈጠርክብን ነዉ፡ ቦታዉም መስጊድ አከባቢ ስለሆነ እኛ የፈለግነዉን ለመናገር መብት የለንም…

**አረብ፡-** እባክህ ለምን ትዋሻለህ? የፈለከዉን እማ እየተናገርህ ነው፤ርእሶችን ም እየመረጣችሁ ያላችሁት እናንተው ናችሁ፡ ምን ጊዜ ነው ታድያ እኔ ጫና የፈጠርኩባችሁ እነ ገረመውም የሰለሙት በራሳቸው ፍላጎት ነው፡ ማንምያስገደዳቸው ሰው የለም፡፡

**አለማየሁ፡-**እንደዚያ ማለቴ አይደለም፡ ነገር ግን አንድን ርእስ አንተው ትደመድማለህ፡ እኛ ለምን አንደመድምም? እየሱስ ስለ ፆመ ሙስሊም ነው ብለሃል፡ እኛ ኦርቶዶክሶችም እንፆማለን፡ <u>ታድያ እኛም ሙስሊሞች ነን ማለትህ</u> ነውን”?

**አረብ፡-** እናንተ የምትፆሙት ለኢየሱስ ነው፤ ኢየሱስ ደግሞ ሲፆም የነበረው ለፈጣሪው ነው፡ ለፈጣሪ የፆመ እየሱስና ለፈጣሪ የሚፆሙ ሙስሊሞች ናቸው በኃይማኖት የሚመሳሰሉት ወይስ እየሱስ ለፈጣሪዉ ፆሞ እናንተ ለእየሱስ መፆም?

**አለማየሁ፡-**ዝም!

**አረብ፡-**አምልኮ ሁሉ ለአንድ ፈጣሪ ብቻ ነው፡ በሱረቱል አንዓም 6÷162 ስግደቴ መገዛቴም ህይወቴም ሞቴም ለአለማት ጌታ ለአላህ ብቻ ነው በል፡ ስለዚህ ያንን የሚያደርጉት ሙስሊሞች ብቻ ናቸው፡ እየሱስ ሙስሊም ነው፡፡

## <u>3 ኡድሂያ (መስዋእት) ማቅረብ</u>

**አረብ፡-** እኛ ሙስሊሞች ለአላህ ብለን ሚስኪኑን ለማብላት በኢድ አል አድሃ አላህ በኛ ላይ የፃፈውን በሱረቱል ከውሰር 108÷2 ስለዚህ ለጌታህ ስገድ (በስሙ) <u>መስዋእት</u> አድርግ፡፡

**አለማየሁ፡-**በእኛም በብሉይ ኪዳን ሰዎች ከኃጢአት ለመዳን ለፈጣሪ ደምን በማፍሰስ በግ እና ፊየልን ያርዱ ነበር፡ አሁንም በእኛ በኦርቶዶክስ ኃይማኖት አለ፡፡

**ወንድወሰን፡-**ከህዝብ ዉስጥ እጁን አወጣና እኔ ፕሮቴስታንት ነኝ ሲል የነበረው ወደ መድረክ ወጣ፡ እኔ ወንድወሰን እባላለሁ፡ አሁን እነ

አለማየሁ በተናገሩት ተሳስተዋል፡፡ መስዋእት ማቅረብ አሮጌ ህግ ስለሆነ ተሽሯል፡ ምክንያቱም ክርስቶስ በኢብራዊ 7÷17 ላይ አንተ እንደ መልከህ ፄዴቅ ሹመት ለዘለአለም ካህን ነህ ብሎ ይመሰክራልና ህጉ ምንም ፍፁም አለደረገምና ስለዚህ የምትደክም የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትእዛዝ **ተሽራለች**… ስለዚህ መስዋእት ማቅረብ ተሽሯል፡፡

**አለማየሁ፡-** ተሽሯል?

**ወንድወሰን፡-**አዎ! ተሽሯል

**አረብ፡-**ተክቢር!

**ሙስሊሞች፡-**አላሁ አክበር!

**አለማየሁ፡-**በማቴዎስ ወንጌል 5÷17 እኔ ህግና ነብያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፡ ልፈፅም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም፡ እውነት እላችኋሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከህግ አንዲት ያውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም… ስለዚህ ዋሽተሃል፡፡

**ወንድወሰን፡-**እኔም ያነበብኩት ከመፅኃፍ ቅዱስ ነው፡፡

**ሙስሊሞች፡-**ተገረሙ

**አረብ፡-**ታዲያ ትክክለኛው የቱ ነው? ወይስ መጽኃፍ ቅዱስ ተቃረነ?

**ሁለቱም፡-**መጽኃፍ ቅዱስ አይቃረንም፡፡

**አረብ፡-**ይህ እራሱን የቻለ ርእስ ስለሆነ አሁን አልገባበትም፡ ታዲያ የሁለታችሁም ትክክል ነው ማለት ነውን?

**አለማየሁ፡-**የኛ ትክክል ነው፡ የነርሱ ትክክል አይደለም ከውስጡም ቀንሰውታል፡፡

**ወንድወሰን፡-**ሃሌሉያ፤እግዚአብሄር ኃይልነው!ደግሞ ተጨማሪ የቅኖና መጽኃፍት እያላችሁ በመጽኃፍ ቅዱስ ላይ አለም የማያውቀውን ትምህርት ጨምራችሁ ፕሮቴስታንቶች ትክክል አይደሉም ትላላችሁ?

**አረብ፡-**በሱረቱል ዩኑስ 10÷66 ንቁ በሰማያት ያሉት እና በምድርም ያሉት ሁሉ በእርግጥ የአላህ ናቸው፤ እነዚያ ከአላህ ሌላ ታጋሪዎችን የሚጠሩ ምንን ይከተላሉ? ጥርጣሬን እንጂ ሌላን አይከተሉም፤እነርሱ የሚዋሹ እንጂ አይደሉም፡፡ የምትናገሩት ሃቅ ቢሆን ኖሮ እናነንተን ባስማማችሁ ነበር፡ እናንተ ራሳችሁ ባልተስማማችሁበትን እንዴት ሙስሞችን ትሰብካላችሁ?

**ብሩክ፡-**እኔ እስልምናን መግባት እፈልጋለሁ፡ ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ምክንያቱም ኃይማኖት የግል ነው፡ እዚህ ከመጣሁ ጊኤ ጀምሮ

አእምሮዬ ሊረጋጋ አልቻለም ስለዚህ ለአእምሮዬ ሰላም መስጠት እፈልጋለሁ፡፡

**ኢብራም፡**-አላህ የሚፈልገው እንዲህ አይነቱን ነው …!

**አረብ፡**- አላህ ካለ ውይይታችን ሰው ሁሉ መምጣት በሚችልበት ቦታ እናዘጋጃለን፡፡ ሁሉም ሙስሊም ይህንን ማወቅ አለበት፡ ለሁሉም ጥሪ አልደረሰም እንጂ ጥሪ ቢደርሰው ኖሮ ሁሉም በሰለመ ነበር፡ ከዚህ በኋላ ስቴዲየም ና አደባባይ ቢሆን ይመረጣል፡ ወንድወሰን ማርቆስ 1÷41 አንብብ፡፡

**ወንድወሰን፡**-ኢየሱስም አዘነለት፤ እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና እወድሃለሁና ንፃ አለው በተናገረው ጊዜ ለምፁ ወዲው ለቀቀውና ነፃ፤በብርቱም ተናግሮ ወዲያው አነፃው ለማንም አንዳችን እንዳትናገር ተጠንቀቅ ነገር ግን ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ ለእነርሱም ምስክር እንዲሆን ስለመንፃትህ <u>ሙሴ ያዘዘውን አቅርብ</u>፡፡ ታዲያ መስዋዕት የሚል እዚህ ውስጥ የት አለ?

**አረብ፡**-በ 1980 የተተረጎመው ግልጽ አድረገው ተርጉመውታል፡

ማርቆስ 1÷41-43 አንብብ

**ወንድወሰን፡**-… ይህንን ነገር ለማንም እንዳትናገር ተጠንቀቅ ነገር ግን ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ ለህዝቡም ምስክር እንዲሆን ስለመዳንህ ሙሴ ያዘዘውን <u>**መስዋእት**</u> አቅርብ፡፡

**አረብ፡**-በተጨማሪም ማቴዎስ 8÷1-4 እና ሉቃስ 5÷12-17 ላይ ታዛችኋል ይህ እንግዲህ በአዲስ ኪዳን ነዉ አሁንስ ምን ትላለህ?

**ወንድወሰን፡**-መሪዎቼን ጠይቄ መልስ እፈልግልሃለሁ እንጂ ብሞት አልሰልምም!

**አረብ፡**-ስለም ያለህ ሰው የለም፡ ብሩክ እና ገረመው የሰለሙት በራሳቸው ፍላጎት ነው ማንም አያስገድድህም፡ ከሞትክማ ምኑን ትሰልማለህ? ስለመስዋእት የማትከራከሩት ኢስላምን ስትቀበሉ ብቻ ነው፡፡

**ወንድወሰን፡**-እግዚአብሔር ሃቁን ይግለፅልህ ብሎ ጥሎን ሄደ

## <u>*4 ኢየሱስ ይሰግድ ነበር*</u>

**አረብ፡-**በሱረቱል መርየም 19÷**31** በየትም ስፍራ ብሆን ብሩህ አድርጎኛል፤ <u>**ሰላትን በመስገድ**</u> ዘካንም በመስጠት አዞኛል፡ ኢየሱስ ይሰግድ ነበር፡፡

**አለማየሁ፡-**ኢየሱስ ይሰገድለታል እንጂ እንዴት ይሰግዳል? ይሰግዳል የሚል በመጽኃፍ ቅዱስ ውስጥ የለም፡ ቢኖርም እኛን ለማስተማር ነው፡፡

**አንተነህ፡-**ኢየሱስ ይሰግዳል የሚልእማ አለ፡፡

**አረብ፡-**ቡሃንስ 4÷19 አንብብ

**አለማየሁ፡-**አላነብም፡፡

**አረብ፡-** ለምንድን ነው የማታነበው?

**አለማየሁ፡-**በቃ አላነብም ብያለው አላነብም፡፡

**አንተነህ፡-**እኔ አነባለሁ፡ ሴቲቱ ጌታ ሆይ! አንተ ነብይ እንደሆንህ አያለሁ አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ እናንተ ሰው ሊሰግድበት የሚገባው ስፍራ በእየሩስአሌም ነው ትላላችሁ አለችው፤ እየሱስም አንቺህ ሴት እመኚኝ በዚህ ተራራ ወይም በእየሩስአሌም ለአብ የማትሰግዱበት ቀን ይመጣል፡ እናንተስ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ፤ እኛ መዳን ከአይሁድ ነውና <u>**ለምናውቀው እንሰግዳለን**</u>፡፡

**አረብ፡-**እስቲ ይህቺን ጥቅስ እናስተንትናት እየሱስ ለምናውቀው እንሰግዳለን ሲል

1. ሲሰግድ እንደነበር ግልጽ ነው፡፡
2. ለምናውቀው እንሰግዳለን ሲል ስግደቱ ለፈጣሪ ብቻ እንደሆነ ያሳያል በማቴዎስ 4÷10 ላይም ተጽፏል፤ ታዲያ እየሱስ ለፈጣሪ እየሰገደ እናንተ ለእየሱስ መስገዳችሁ ምንድር ነው?

**ሁሉም፡-**ዝም

**አረብ፡-**ሴቲቱ ኢየሱስን ሰው ሊሰግድበት የሚገባው ስፍራ በእየሩስኣሌም ነው ትላላችሁ አለችው…

1. ስግደትም አቅጣጫ እንዳለው እየተናገረች ነው፡፡
2. በዚህ ተራራ ወይም በየሩስአሌም ስትል በእየሩስአሌም ያለው ምንድንር ነው?

**አንተነህ፡-**<u>ቤተመቅደስ</u> ነው፡፡

**አረብ፡-** አላሁ አክበር! ትክክል ነህ፤እኛ ሙስሊሞች ድሮ ስንሰግድ የነበርነው ወደ ቤተመቅደስ ነበር፡ በሱረቱል በቀራህ 2÷144 የፊትህን ወደ ሰማይ መገላበጥ በእርግጥ እናያለን ወደ እምትወዳትም ቂብላ እናዞረሃለን፤ ስለዚህ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጅድ <u>(ወደ ከእባ)</u> አቅጣጫ አዙር የትም ስፍራ ብትሆኑም (ስትሰግዱ) ፊቶቻችሁን ወደ እርሱ አቅጣጫ አዙሩ፤ እነዚያም መጽኃፍን የተሰጡት እርሱ ከጌታችሁ ሲሆን እውነት

መሆኑን ያውቃሉ፤ አላህም ከምትሰሩት ስራ ዘነንጊ አይደለም፡፡ ነቢያችን(ሰ.ዐ.ወ) ሲሰግዱ የነበሩት ወደ ቤተመቅደስ ነበር ነገር ግን አላህ ከሰጣቸው ተዓምር ዉስጥ አንዱ ወደ ከእባ ዞሮ መስገድ ነው፡፡

**አንተነህ፡-** ቁርዓን እነዚያ መጽኃፍ የተሰጡት ያውቃሉ ሲል ምን ማለቱ ነው?

**አረብ፡-**አሁን በዮሃንስ 4÷19-24 ያለውን በትክክል ብታነብ በደንብ ይገበሃል፡ አንዳንድ ክርስቲያኖች ወደ ከእባ ዞረን ስንሰግድ ከእባን እንደ ጣኦት አድርገው እኛ ለካእባ የምንሰግድ ይመስላቸዋል፡ ነገር ግን የነቢያችን ባልደረቦች በነቢያችን ጊዜ <u>በከእባ ድንጋይ ላይ ቆመው አዛን የደርጉ ነበር</u> እውነትም የከእባ ድንጋይ ጣኦት ቢሆን ኖሮ የትኛው ጣኦት አምላኪ ነው በሚያመልከው ጣኦት ላይ ወጥቶ በእግሩ የሚቆመው? በዮሃንስ ወንጌል 4÷23 <u>በዚህ ተራራ ወይም በእየሩስአሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል</u>፡ ያማለቱ ወደ ሌላ አቅጣጫ ትዞራላችሁ ማለቱ ነው፡ እንጂ ስግደት ይቀራል ማለቱ አይደለም፡ታዲያ ያ ጊዜ መቸ ነው?

**ብሩክ፡**- ይህማ ግልጽ ነው አሁን ነው፡ እባካችሁ ስለሙ!

**አለማየሁ፡**-አሁኑኑ ሰልመህ ተነሳህብን?

**አንተነህ፡**-እርሱን ተወውና ቀጥልልን፡ ታዲያ ስግደት አያልቅም እንዴ?

**አረብ፡**-እባካችሁ ፀጥታ ሰው የፈለገውን መጠየቅ ይችላል፡ በሙስሊሞች ላይ ያለብን ግዴታ ግን ሀቁን ማሳወቅ ነው፡ **ወንድሜ** በሱረቱል ሂጅር 15÷99 እውነቱም (ሞት) እስኪመጣህ ድረስ ጌታህን ተገዛ፡ ስለዚህ ስግደት አያልቅም፡ ስግደት የሚያልቀው ስትሞት ብቻ ነው፡፡

**አለማየሁ፡**-ስግደት በመጽኃፍ ቅዱስም አያልቅም፡ በ1ኛ ዜና መዋእል 16÷11 የእርሱን እርዳታ ለማግኘት እግዚኣብሔርን ፈልጉ <u>ባለማቋረጥ ለእርሱ ስገዱ</u>፡፡

**ወንድወሰን፡-**ህዝብ ውስጥ ቆሞ፤ታዲያ እናንተ ኦርቶዶክሶች አሁንም የምትሰግዱ ከሆናችሁ፡ የክርስቶስ ለእናንተ ፤ብሎ መሰቀል ትርጉሙ ምንድን ነው?

**አረብ፡-**ወደ መድረክ ለምን አትወጣም?

**ወንድወሰን፡-**አልፈልግም፡፡

**አረብ፡-** ለኃጽኣታችሁ መሰረያ ይሆን ዘንድ የስግደት ልክ የሚገመተው በአባቶች (በቄሶች) ነው፡፡

**አለማየሁ፡-**ስግደት በእርግጥ አንተ እንዳልከው አርብ አርብ ልክ የስቅለት ቀን ሁሉም ይሰግዳል፡ የስግደት ልክም የሚገመተው(በቄሶች) ነው ፡፡

**አረብ፡-**ፕሮቴስታንቶች በመጽኃፍ ቅዱስ አምነው ስግደት አልቋል ይላሉ፡ እናንተ ደግሞ ላይ አላለቀም ትላላችሁ፤ሌላም ቢመጣ ሌላ ነገር ማለቱ አይቀርም፡ ስለዚህ ወደ እስልምና ብትመጡ ከዚህ ሁሉ ክርክር ነፃ ትወጣላችሁ፡ ባይገርማችሁ ኢየሱስ ሲያስተምር የነበረው በመስጊድ ነው፡፡

## 5.ሙክራብ በ(1949 መ.ቅዱስ ትርጉም) መስጊድ ነው፡፡

**አለማየሁ፡-**በመስጊድ!

**አንተነህ፡-**እንዴት ሆኖ ነው በመስጊድ ያስተማረዉ?

**አረብ፡-**ይህ የምታዩት በ 1949 የተተረጎመ መጽኃፍ ቅዱስ ነው፡፡

**አንተነህ፡-**እኔ በእርግጥ ይህንን መጽኃፍ ቅዱስ ከዚህ በፊት አላየሁም፡፡

**አለማየሁ፡-**አይ በአባቴ እጅም አለ፤ በቤተክርስቲያን ውስጥም በአባቶች(በቄሶች) እጅም አለ፡፡

**ሰዎች፡-** እየተገረሙ ተራ በተራ ወደ መድረክ እየወጡ ይህንን መጽኃፍ ቅዱስ ማየት ጀመሩ፡፡

**አረብ፡-** የሰጠኝ ሳዲቅ ወንድማችን ነው፡ ሳዲቅ የምንኮራበት ታላቅ ዳኢያችን ነው፡ሳዲቅን አላውቅም የሚል ሰው እዚህ ውስጥ ይኖራል ብዬም አልገምትም፡፡

**አለማየሁ፡-**ኢየሱስ በመስጅድ አስተማረ የሚል የት አለ?

**አረብ፡-** ዮሃንስ ወንጌል 6÷58 አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡-** ይህንን እንጀራ የበላ ለዘለአለም ይኖራል፤ ይህንን አለ <u>**በመስጊድ ሲያስተምር**</u> በፍቅርናሆም፡፡

**አረብ፡-** ምነው ፊትህ ተቀየረ?

**አለማየሁ፡-**ነገሩ አዲስ ሆኖብኝ ነው፡ በ 1954 የተተረጓመ እኮ ምኩራብ ይላል፡፡

**አረብ፡-**እጃችሁ መች ያርፋል! በ 1954 እና በ 1980 የተተረጎሙትን አሁን በእጃችን የሚገኙትን

እንኳን በትንቢተ ኢሳያስ 7÷21 አንብብ

**አለማየሁ፡-በ 1954**

- በዚያን ቀን እንዲህ ይሆናል ሰው አንድ <u>*ጊደር ና ሁላት በጎችን*</u> ያስድጋል

በትንቢተ ኢሳያስ 7÷21 **በ 1980** ትርጉም
ያም ዘመን በደረሰ ጊዜ አንድ ገበሬ አንድ ጊደርና ሁለት
***ፊየሎችን*** እንኳ ለማትረፍ ቢችል እድለኛ ነው፡፡

**አንተነህ፡**-ታዲያ ለምን ተለያዩ?

**አረብ፡**-እሱ የኔ ጥያቄ ነው፡ በጎችን በፍየሎች የቀየሩት መስጊድን በምኩራብ መቀየር ምን ይከብዳቸዋል? ለመሆኑ ፍየሎችና በጎች አንድ ናቸው?

**አንተነህ፡**-አንድ አይደሉም፡፡

**አለማየሁ፡**-ዝም!

**አረብ፡**-በሱረቱል ጅን 72÷18 እነሆ መስጅዶችም የአላህ ብቻ ናቸው (በውስጣቸው) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ (ማለትም) መስጅድ የአላህ ቤት ብቻ ነው፡፡ እውነትም እናንተ እንደምትሉት ኢስላም የመጣው በነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከሆነ። ታዲያ መስጊድ ምን ሊሰራ ነው በመጽኃፍ ቅዱስ ውስጥ የገባው? ሁሉም ነቢያት ሙስሊሞች ነበሩ፡፡

**ሁለቱም፡**-ዝም!

**አረብ፡**-በማቴዎስ 13÷54 አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡**-**በመስጊዳቸውም** አስተማረ፡፡

**አረብ፡**- ማርቆስ 5÷38 አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡**-ወደ **መስጊድ** አለቃቤትም መጣ ሁከትም አየ ሰዎች ሲያለቅሱ ወይም ሲሉ…

**አረብ፡**- በዮሃንስ ወንጌል 6÷2 አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡**-ቅዳሜም በሆነ **በመስጊድ** ያስተምር ጀመረ፡፡

**አረብ፡**- በማቴዎስ 10÷17 **በመስጊዳቸውም** ይገርፉቸዋል፡፡ በዮሃንስ 12÷42 አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡**-ነገር ግን ስለፈሪሳውያን ይህንን አልገለጡም ወደ **መስጊድ** ከመግባት እንዳይከልክሉ…

**አረብ፡**- ዛሬ ሰው ወደ መስጇድ እንዳይገባ ትልቅ ጥረት እንደምታደርጉ ግልጽ ነው፡ ነገር ግን እየሱስ አትከልክሉ ስል ነበር፡ አይደለም ቃሉን ልትሰሙት፡ መስጅድ የሚለውንም ቃል ሙሉ ለሙሉ ከአሁኑ መጽኃፍቅዱስ አስወግዳችሁታል፡ ይህን ሁሉ የሚታደርጉት ሃቅን ላለመቀበል ነው፡ እኛ መስጊድ የሚገባውን ሰው አንከለክልም በሱረቱል በቀራህ 2÷114 የአላህም መስጊዶች በውስጣቸው ስሙ እንዳይወሳ ከከለከለና እሷንም በማበላሸት

ከሮጠ ሰው ይበልጥ በዳይ ማን ነው?…፡፡ ታድያ በዳዮች እነማን ናቸው? ዛሬ መስጊድ የሚለውን ቃል በሙሉ ሙክራብ በሚለው ቃል ቀይረዉታል፡ ሙክራብስ ምንድን ነው?

## 6 ሙክራብ ሚህራብ ነው፡፡

**አረብ፡-** የአማርኛው ቅዱስ ቁርዓን አባታችን ሃጅ ሙሐመድ ሳኒ ሀቢብ ረሂመሁላህ (አላህ ይዘንላቸውና) በተረጎሙት በቁርዓኑ መቅድም ላይ ሙክራብ ሚህራብ እንደሆነ ገልጸውታል፡ እኔ አስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፤ ሙክራብ የሚባል የትኛው የቤተክርስቲያን ክፍል ነው?

**አለማየሁ፡**-ቤተክርስቲያን ውስጥ ሙክራብ የሚባል ክፍል የለም አባቶች ሲያስተምሩን ግን ሙክራብ <u>የአይሁዶች የፀሎት</u> ቦታ ነው፡፡

**አረብ፡**-እንደዚያ ካልከማ መጽኃፍ ቅዱስ የክርስቲያኖች ሳይሆን የአይሁዶች መሆኑ ነው፡ አይሁዶች በኢየሱስ አያምኑም የሚያምኑት በእዝራእ ነው፡ ሙክራብ ኢማሞቻችን (የሙስሊም አሰጋጅ) ቆመዉ የሚያሰግድበት ቦታ ነው፡ እየሱስ በአይሁድ የፀሎት ቦታ ሰገደ ካልንማ እየሱስ የአይሁድ ሃይማኖት ተከታይ ነበር ማለት ነው። ሙክራብንም ወደ አይሁዶ የፀሎት ቦታ የቀየራችሁት እስልምናን ስለምትጠሉት ብቻ ነው፡ በኬንያ ውስጥ ያሉት በኪሱዋህለኛ ቋንቋ የተተረጎሙት mattayo(Matthews 13;54, 10;17) Yohana(John 6;58) Maark(Mark 5;38 <u>*SINAGOGI (MISKITINI) (mosque)*</u> <u>መስጊድ</u> ይላሉ እስከ አሁን መስጅድ የሚለውን ቃል አልቀየሩትም፤ በአማርኛው ውስጥ በስህተት ገባ ብንል እንኳ በኪሱዋህለኛ ና በሌሎች ውስጥ እንዴት ሊገባ ቻለ? ስለዚህ አላህ አልበቀራህ 2÷79 ለእነዚያ መጽኃፉን በእጆቻቸው ለሚጽፉና ከዚያም ጥቂትን ዋጋ ሊገዙበት ይህ ከአላህ ዘንድ ነው ለሚሉ ወዮላቸው፤ለነርሱም ከዚያ እጆቻቸው ከጻፉት ወዮላቸው፤ ለእነርሱም ከዚያም ከሚፈሩት (ኃጢአት) ወዮላቸው፡ አላህ ተውራት(ኦሪት) እና ወንጌል (ኢንጂል) የወረዱት ከኔ ዘንድ ነው ስለዚህ አበላሹት የሚለውም ለዚህ ነው፡፡

**አለማየሁ፡**-በሱረቱል አንዓም 6÷34 የአላህ ቃላት ለዋጭ የለም ይላል እንዴት ይቀየራል?

**አረብ፡**-በሱረቱል ማኢዳ 5÷44 እኛ ተውራትን በውስጥዋ መምሪያና ብርሃን ያለበት ሲሆን አወረድን፤ እነዚያ ትእዛዝን የተቀበሉ ነቢያት በነዚያ ይሁዳውያን በሆኑት ላይ በርሷ ይፈርዳሉ፤ **<u>ሊቃውንትና አዋቂዎቹም ከአላህ መጽኃፍ እንዲጠብቁ</u>** በተደረጉትና በርሱም ላይ መስካሪዎች በሆኑት (ይፈርዳሉ) ሰዎችንም አትፍሩ ፍሩኝም በአንቀጾቼም አነስተኛ ዋጋ አትለውጡ አላህም ባወረደው ነገር ያልፈረደ ሰው እነዚያ ከሃዲዎች አነርሱ ናቸው፡፡ አላህ የተውራትንና የእንጂልን ጥበቃ ያስቀመጠው በሰዎች ላይ ነበር፡ አንተ ከቁርዓን የጠቀስከው ደግሞ ያለው ቁርዓንን ነው፡፡ አላህ የቁርዓን ጥበቃ በሱረቱል ሂጅር 15÷9 ቁርዓንን እኛ አወረድነው እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን፡፡ አሁን አንተ የጠቀስከው የቁርዓን አንቀጽ ቃሌን ለዋጭ የለም ያለው ቁርዓንን ነው እንጂ መጽኃፍ ቅዱስን አይደለም፡ አንዳንድ ክርስቲያኖች ቁርዓን የአላህን ቃላት ለዋጭ የለም ይላል እና መጽኃፍ ቅዱስ አልተቀየረም ይላሉ፡ ከ 66 ቱ፤ ከ 81 ንዱ፤ ከ 73 ቱ ትክክለኛዉ የቱ ነው የሚል ጥያቄ ብናቀርብላቸው፡ ኦርቶዶክሶች 81 ንዱ ነው ይላሉ፡፡ ካቶሊኮች 73 ቱ ነው ይላሉ፡ ፕሮቴስታንቶቹ 66 ቱ ነው ይላሉ፡ ታዲያ የቁርዓኑ አንቀጽ ለመጽኃፍ ቅዱስ እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡ ሁሉም ለጥቅማቸው ብለው ለውጠውታል፡ አሁን እዚህ መድረክ ላይ ያሉ ራሳቸው አይመሳሰሉም፡ ስለዚህ አይቀየርም የተባለው ቁርዓን ብቻ ነው፡፡

**አለማየሁ፡**-አንተ ብትልም እኔ ግን አልቀበልህም፡፡

**አንተነህ፡**-ሙስሊሞች ፂማቸውን ያሳድጋሉ ይህንንስ ታዛችኋል?

## <u>7 ፂም ማሳደግ</u>

**አረብ፡-**ፂም ማሳደግ የነቢያቶች ፈለክ ነው፡ በሱረቱል ጣሃ 20÷94 የናቴ ልጅ ሆይ **<u>ፂሜንም</u>** ራሴንም አትያዝ እኔ በእስራኤል ልጆች መካከል

ሰያየህ ቃሌንም አልጠበክም ማለትህን ፈራሁ አለው፡፡ እዚህ አንቀጽ ላይ ሙሳ(ዐሰ) ሃሩንን(ዐሰ) ፂሙን ይዞት ነበር፡ ሃሩን ነብይ ነው፤ ነብያቶች ከሚታወቁበት መስፈርቶች ውስጥ አንዱ ፂም ማሳደግ ነው፡ ነቢያችንም(ሰ.ዐ.ወ) በሰሂህ ቡኻሪ ቅጽ 7 አንቀጽ 64 ሀዲስ ቁጥር 780 እና 781 ላይ አዞናል፡፡ ብዙን ጊዜ እናንተ ክርስቲያኖች ፂም አሳድጎ የሚሄደውን ሙስሊም <u>አሸባሪ</u> የሚል ስም ትሰጡታላችሁ፡፡ ነገር ግን መጽኃፋችሁም <u>ፂማችሁን እንድታሳድጉ ያዛችኋል</u>፡፡ አሪት ዘሌላውያን 19÷26 በ1980 ትርጉም አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡**-ደም ያለበትን ስጋ አትብሉ፤ የአስማትንም ነገር አትከተሉ፤የራስ ፀጉራችሁንም ዙሪያውን አትከርክሙት፤**<u>ፂማችሁን አሳጥራችሁ አትቁረጡ</u>...**

**አረብ፡**-አላህ ካለ ገና ብዙ ነገሮችን ታያላችሁ፡ አሁንስ ከእስልምና የጠላችሁት ነገር ምንድን ነው;

**አለማየሁ፡**-ቁርዓናችሁ ከአንድ በላይ ጋብቻን ያዛል ስለዝህ የሴቶችን መብተ ይነካል፡፡

## <u>8 ከአንድ በላይ ማግባት</u>

**አረብ፡**-ቁርዓን ከአንድ በላይ ማግባትን <u>ይፈቅዳል እንጂ አያዝም፡</u> በሱረቱል ኒሳእ 4÷3 በየቲሞች (ማግባት) አለማስተካከላችሁን ብትፈሩ (ዝሙትንና ከተወሰነላችሁ በላይ ማግባትን ፍሩ) ከሴቶች ለእናንተ የተዋበላችሁን <u>ሁለት ሁለት፣</u> <u>ሶስት ሶስትም፣</u> <u>አራት አራትም አግቡ፡፡</u> አለማስተካከልንም ብትፈሩ አንዲትን ብቻ ወይም እጆቻችሁ ንብረት ያደረጉትን (ሀብታችሁ የሆኑትን እቁባት) ያዙ፤ ይህ ወደ አለመበደል በጣም የቀረበ ነው፡፡ በዚህ አንቀጽ ላይ አላህ ፈቀደ እንጂ አንተ እንደምትለው ትእዛዝ ወይም ግዴታ አይደለም፡ ከአንድ በላይ መስተዳደርን የቻለ ሰው ብቻ ነው የሚያገባው፡ መጽኃፍ ቅዱስ ከአንድ በላይ ማግባትን በተመለከተ ምን ይላል?

**አለማየሁ፡**-መጽኃፍ ቅዱሳችን ከአንድ በላይ ያገባ ሁሉ አመነዘረ ይላል፡፡

**አረብ፡**-መጽኃፈ ነገስተ ቀዳማዊ 11÷3 ጠቢቡ ሰለሞን *<u>700 ሚስቶችን</u>* ና 300 <u>እቁባቶች ነበሩት፡፡</u>ከፈለግክ እንካ አንብብ፡፡

**አንተነህ፡**-አንድ ሺህ ሚስቶች?

**አረብ፡-** አዎ! እና እሱ አመነዘረ ማለትህ ነውን?

**አለማየሁ፡**-አዎ አመንዝሯል፡፡

**አንተነህ፡**-የእግዝአብሔር ነብይ እንዴት ያመነዝራል? የተሰጠው ህግ ይኖራል እንጂ፤ እኔ ደፍሬ እንደሱ አልናገርም፤ እርሱ ለተናገረውም እግዚአብሔር ይቅር ይበለው፡፡

**አረብ፡**-ታዲያ ዝሙተኛ ከሆነ ነብይነቱ ምኑ ጋር ነው? እባክህ ከመናገርህ በፊት አስብ!

**አለማየሁ፡**-ዝም!

**አረብ፡-** የአብረሃም ሚስቶች ስንት ነበሩ?

**አለማየሁ፡**-አብረሃም በህግ ያገባት ሳራን ብቻ ነበር ከአጋር የተወለደው ልጅ በዝሙት (ዲቃላ) ነው፡፡

**ኢብሂም፡**-እባካችሁ ካለወቃችሁ አናውቅም በሉ እንጂ ነብያቶችን አትስደቡ፡ ክርስትና እንደዚህ ነብያትን የሚሰድብ ከሆነ ታዲያ የፈጣሪ ኃይማኖት የሆነው ምኑ ላይ ነዉ?

**አረብ፡**-ተው ከሆዳቸው ያላቸውን ነገር በሙሉ ይነናገሩ፡

ኦሪት ዘ ፍጥረት 16÷3 አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡-...** የአብረሃም ሚስት ሳራ ግብፃዊት ባሪያዋን አጋርን ወስዳ ለአብረሃም **ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠችው** ፡፡

**አረብ፡**-እና ሚስት ማለት ምን ማለት ነው? ለመሆኑ አብረሃም ሳራንና አጋርን ብቻ ነው እንዴ ያገባው? በኦሪት ዘ ፍጥረት 25÷1 አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡**-አብረሃምን ደግሞ ስሟ ኬጡራ የምትባል አገባ...

**አረብ፡**-በዚህ ዙሪያ ከአንድ በላይ ያገቡትን ብዙ ማምጣት ይቻላል፡፡ ክርስትና ከአንድ በላይ ማግባትን የማይፈቅድ ከሆነ እንዚህ ከአንድ በላይ ስያገቡ የነበሩት የትኛው ኃይማኖት ተከታይ ነበሩ? ክርስቲያን ናቸው የምትል ከሆንክ ክርስትና ከአንድ በላይ ጋቻን አይፈቅድም፤ ሙስሊሞች ነበሩ የምትል ከሆንክ ደግሞ መከተል አለብህ።

**አለማየሁ፡**-ዝም!

**አንተነህ፡**-እስልምና እስከ አራት ብቻ ማግባትን ነው የሚፈቅደው፡ እነዚህ ደግሞ ከአራት በላይ አግብቷል፤ እንዴት ሙስሊም ይሆናሉ? እኔ አልቀበልህም!

**አረብ፡**-ነቢያችን(ሰ.ዐ.ወ) ከ 9-11 እንዳገቡ በሀዲስና በታሪካቸውም ተገልጿል፡ ታዲያ ነቢዩ ሙሐመድም (ኢ.ሰ.ወ) ከአራት በላይ ስላገቡ ሙስሊም አይደሉም ማለትህ ነዋ? ለነብያቶች የተፈቀዱና ለእኛ

የተፈቀዱ አንድ አይደለም ነቢያቶች ከእኛ በላይ ማስተካከልን ስለሚችሉ አላህ ፈቅዶላቸዋል፡ ለእነርሱ ከአራት በላይ ተፈቅዶ ለእኛ ለምንድን ነው የማይፈቀደው የምትሉ ከሆናችሁ ደግሞ፡ የእናንተ ጥያቄ አይኖቻችን ለምን ሁለት ሆነው የእጆቻችን ጣቶች ደግሞ ለምን አምስት ሆኑ እንደማለት ነው፡ በአለማችን ላይ የሴቶችን ብዛት ብናየው ከወንዱ በጣም ይበልጣል፡ በኒውዮርክ 1,000,000፤ በሩስያ 7,000,000፤ በእንግሊዝ 4,000,000፤ በህንድ 7,000,000፤ በሀገራችን ውስጥ ራሱ የማእከላዊ እስታቲክስ ባለስልጣን መጽሄት በ 1997 / ገጽ 24 ስናየው የሴቶች ብዛት ከወንዶች በጣም ይበልጣል፡፡ እያንዳንዱ ወንድ ከአንድ በላይ እንዳያገባ የሚል ህግ ቢወጣ ኖሮ የቀሩት እህቶቻችን የት ይሄዳሉ?

**አለማየሁ፡-** ዝም!

**አረብ፡-**ሶስት ምርጫ ብቻ አላቸዉ፡ እነርሱም……

1. አላህ ለሙስሊሞች እንደ ፈቀደልን ቀደም ብሎ ካገባዉ ወንድ ጋር ትዳር መመስረት፡
2. በአሜሪካ ና አዉሮፓ ውስጥ እንደተጀመረው ሴት ለሴት መጋባት፡
3. ለዝሙት መጋለጥ

ከነዚህ ከሶስቱ የትኛው የተሻለ ነው ?

**አለማየሁ፡-**የወንዱ ቁጥር ቢበዛስ?

**አረብ፡-** መች በዛ?

**አለማየሁ፡-**ወንዶች ከአንድ በላይ እንደሚያገቡት ሁሉ ሴቶችስ ከአንድ በላይ ማግባት አይችሉምን?

**አረብ፡-**ይህንን አላህ ሳያውቅ ቀርቶ አይደለም፡ ነገር ግን ታግባ ብለን ብንፈቅድና ብዙ ከአንድ ባል በላይ ቢኖራት፡ የሚወለደው ልጅ ለማን ነው የሚሆነው? ለአንደኛ ባሏ ነው ወይስ ለሌሎቹ?

**አንተነህ፡-**ኧረ! በጣም ይከብዳል፡፡

**ኢብራሂም፡-**ተክቢር!

**ሙስሊሞች፡-**አላሁ አክበር!

## 9 በዘመድ መጋባት

**አንተነህ፡-**እስልምና በዘመድ መጋባትን ያስገድዳል!!

**አረብ፡**-አያስገድድም! አንዷት ወጣት ሴት ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) ጋር መጣችና አንተ የአላህ መልእክተኛ ሆይ! አባቴ ደረጃውን ከፍ ለማድረግ ሲል ለወንድሙ ልጅ (ለአጎቴ ልጅ) ዳረኝ፤ ስትል ነቢያችን(ሰ.ዐ.ወ) ሁለት አማራጮችን ሰጧት፤ ከፈለግሽ አግቢ ካልፈግሽ አታግቢ በማለት፤ እኔ የአባቴን ምርጫ ተቀብያለሁ ተጋብተናል ነገር ግን ወላጆች በልጆቻቸው ላይ የማስገደድ መብት እንደሌላቸው እንድያውቁ ፈልጌ ነው፡፡ (ከአቡዳውድ ውጪ አራቱ ዘግበውታል)፡፡ በኢስላም የአጎትን ልጅ ማግባት የተፈቀደ ነው እንጂ በጣም የተወደደም አይደለም፡፡ መጽኃፍ ቅዱሳችሁን ብታውቁ ኖሮ እንዲህ አይነት ጥያቄ በኢስላም ላይ አታነሱም ነበር፡፡

**አለማየሁ፡**-እኛ ክርስቲያኖች እስከ 7 እስከ 10 ቤት በመቁጠር እንገባለን እንጂ እንደናንተ የአጎታችንን ልጅ አናገባም፡፡

**አረብ፡**-በክርስትና ኃይማኖት ውስጥ እንደሌለ አውቃለሁ፡ በመጽኃፍ ቅዱስ ውስጥ ግን አለ፡፡

**አለማየሁ፡**-ደነገጠ! ክርስትናንና መጽኃፍ ቅዱስን ለምን ትለያለህ?

**አረብ፡**- ምን አስደነገጠህ ከታዘዝክ ማድረግ ብቻ ነው፡፡

**አለማየሁ፡**-መጽኃፍ ቅዱስ ሺህ ጊዜ ቢያዘኝ እንኳ አላደርግም!

**አረብ፡**-በኦሪት ዘሁልቅ 36÷10-11 ያለውን አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡**-እኔ አለነብም አንተ ድግምተኛ ነህ፡፡

**አንተነህ፡**-እርሱ የሚለውን ተውና እኔ አነባለሁ፡፡ ስለዚህም የፀሎፍሃድ

ሴቶች ልጆች ማህላ፣ቲርፃ፣ሆግላ፤ሚልካና ኖኣ እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት **ከአባታቸው ወንድሞች ልጆች** (ከአጎታቸው ልጆች) ጋር ተጋቡ፡፡

**አረብ፡**- ሙሴ የአጎቱን ልጅ እንዲያገባ ታዟል፡ እናንተ ክርስቲያኖችም ታዛችኋል ማለት ነው፡ የሙሴ ተከታዮች የአጎታቸውን ልጆች ሲያገቡ ነበሩ፡ እነርሱስ የትኛው ኃይማኖት ተከታይ ነበሩ? ኃይማኖታችን በዘመድ መጋባትን አይፈቅድም ትላላችሁ፡ የአዳም ልጆች እንዲሁም ሰው ዘመድ ለዘመድ ተጋብተው ተባዝተዉ እዚህ ደረሱ፡ የዛኔ ሀይማኖታችሁ እንዳል ነበረ ያሳያል፡ ምክንያቱም ኃይማኖታችሁ ዘመድ ለዘመድ መጋባትን ስለማይፈቅድ ነው፡ ኢስላም በዚያን ጊዜም የነበረ ነዉ፤ኃይማኖታችሁ የመጣው ራሱ ሰው ዝምድናንከተላቀቀ በኋላ ነው ማለት ነው፡፡ መጽሀፍ ቅዱስ የወንድምህን ሚስት

እርሱ አግብቶ ልጅ ሳይወልድ ከሞተ ሚስቱን፡እንድትወረስ ያስገድደሃል!

## 10 የወንድምህን ሚስት እርሱ ከሞተ ማግባት

**አንተነህ፡-**የወንድምህን ሚስት እርሱ ከሞተ ማግባት በኢስልም ብቻ ነዉ በክርስቲያን የለም።

**ዮሃንስ፡-**እኔ ዮሃንስ እባላለሁ፡ የመጣሁትም ከአዋሳ ነው፡እናንተ የምትወያዩበትን ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ፈልጌ ነው፡ ከዚህ በፊትም ከኢስላም የጠለሁት ይህን ብቻ ነበር፤ አንተ እንደምትለው መጽኃፍ ቅዱስ የሚያዝ ከሆነ እኔ እዝህ ህዝብ ፊትለፊት ቆሜ እስልምናን እቀበላለሁ፡ ሙስሊሞቹም እንዲያውቁኝ እፈልጋሁ፡፡

**አለማየሁ፡-**ሊኖር ይችላል ተው እንደዚያ አትበል፡፡

**ዮሃንስ፡-**ሊኖር ይችላል? ታዲያ ካለ ለምን አንተገብርም የእግዚአብሔር ትእዛዝ አይደል?

**አለማየሁ፡-**ቢሆንም ተሽሯል፡፡

**ኢብራሂም፡-**ቅድም ከወንደወሰን ስትነጋገሩ መጽሃፍ ቅዱስ አይሻርም ብለህ ነበር፡ አሁን ደግሞ ራስህ ተሽሯል ትላለህ? እነዚህ ሰዎች አውቀው የከፈሩ ናቸው ወንድሜ **አረብ** ውይይቱን ብታቆም ይሻላል፡፡

**አረብ፡-** ሳያዉቁ የከፈሩም ይኖራሉ፡ ስለዚህ እነርሱን ማስተማር አለብን አዉቀዉ  የጠመሙትን ለመመለስ ችሎታው በአላህ እጅ ብቻ ነው፡ አሪት ዘ ዳግም 25÷5  አንብብ

**ዮሃንስ፡-** ወንድማማቾች በአንድነት ቢቀመጡ አንዱ ልጅ ሳይኖረው ቢሞት፡ የሞተው ሰው ሚስት ሌላ ሰው ታገባ ዘንድ ወደ ውጭ አትሂድ፤ ነገር ግን የባሏ ወንድም ወደ እርሷ ገብቶ እርሷን ያግባ፤ ከእርሷም ጋር ይኑር፡፡

**አረብ፡-** በ1980 የተተረጎመው ለማግባት ግዴታ አለበት ይላል፡፡

**አንተነህ፡-** እየሱስስ ስለዚህ የተናገረ ነገር አለ?

**አረብ፡-**በሚገባ በአዲስ ኪዳንም ይህ ህግ ነበር፡

በማቴዎስ 22÷23 አንብብ፡፡

**አንተነህ፡-**በዚያን ቀን ትንሳኤ ሙታን የለም የሚሉ ሳዱቃውያን ወደ እርሱ ቀረቡ እንዲህም ብለው ጠየቁት መምህር ሆይ! ሙሴ አንድ ሰው ልጅ ሳይወልድ ቢሞት ወንድሙ ሚስቱን አግብቶ ለወንድሙ

ዘር ይታካለት አለ፡፡ ሰባት ወንድማማቾች በእኛ ዘንድ ነበሩ ፊተኛው ሚስት አግብቶ ሞተ ዘር ስለሌለው ሚስቱን ለወንድሙ ተወለት፤ እንዲሁም ደግሞ ሁለተኛውም ሶስተኛውም እስከ ሰባተኛው ድረስ፡፡ ከሁሉም በኋላ ሴቲቱም ሞተች፤ ሁሉም አግበቷታልና በትንሳኤ ቀንስ ከሰባቱ ለማናቸው ሚስት ትሆናለች?

**ዮሃንስ፡**-ለሰባት አንዷን ሴት! ይህቺ እማ ገፊ ናት፡፡

**አረብ፡**-1. እናንተ ክርስትያኖች ሰው ኢስላምን እንዲጠላ ብቻ በኢስላም ላይ ያለውን ትንሽ ነገር ሁሉ ታወራላችሁ፡ አንደ ሙስሊም ሚስት አግብቶ ከሞተ ሁለተኛው ወንድሙ ሚስቱን በራሷ ፍቃድ ማግባቱ ነው ወይስ አሁን በመጽኃፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳገኘነው ለሰባት አንዷን ሴት ያለፍቃዷ በግድ ማግባት ነው ይበልጥ የሚገርመው?

**2.** ያተከለከለ ቢሆን ኖሮ እርሱ (ክሮስቶስ) በከለከለ ነበር፤ እርሱ ያልከለከለውን ማን ሊከለክል ይችላል?

3. አሁን በእኛ ዘንድ ብለው ነው ጥያቄውን የጠየቁት፡ ያ ማለታቸው ደግሞ በአዲስ ኪዳን ማላታቸው ነው፡ ነቢያችንም (ሰ.ዐ.ወ) አዲስ ህግ አላመጡም የኢስላም ኃይማኖትም መጤ አይደለም፡ ታዲያ ኢስላምን የምትነቅፉት በምናችሁ ነው? በማርቆስ 12÷17 እና በሉቃስ 20÷28 ላይም ተጽፏል፡፡ አሁንስ ምን ትላላችሁ?

**ዮሃንስ፡**-ያው እኔ እስልምናን መቀበሌ ነው፡

**አረብ፡**- እናንተስ?

**አለማየሁ፡**-እኔ ብሞት አልሰልምም፡፡

**አረብ፡**- መብትህ ነው፤ እስቲ አሁን ያላችሁ ክርስቲያኖች

-ከአንድ በላይ ብታገቡ

-የወንድማችሁን ሚስት እርሱ አግብቶ ልጅ ሳይ ወልድ ከሞተ ብትወርሱ

- የአጎታችሁን ልጅ ብታገቡ
- ለፈጣሪ ብቻ ብትሰግዱ
- ለፈጣሪ ብቻ ብትፆሙ
- ለፈጣሪ ብቻ ዘካ(አስራት) ብታወጡ
- ፂማችሁን ብታሳድጉ

- መስዋእት (ኡድሂያን) ብታርዱ፡፡ እነዚህን ብቻ እንኳ ብትተገብሩ ቀጥታ የምትመጡት ወደ የትኛው ኃይማኖት ነው?

**ኢብራሂም፡**-ተክቢር!
**ሙስሊሞች**፡-አላሁ አክበር!
**አንተነህ**፡-ይህማ ግልጽ ነው፡ ታዲያ መሪዎቻችን የደበቁን ለምንድን ነው?
**አለማየሁ**፡-መድረኩን ለቆ ሄደ፡፡

## <u>እግዚአብሔርን በውሸት ማምለክ</u>

**አረብ፡**-መሪዎቻችሁንም ገደል የከተታቸው ጳውሎስ ነው፤ በሮሜ 3÷8 በ1954 ትርጉም አንብብ

**አንተነህ፡**-…ነገር ግን አመፃችን የእግዚአብሔርን ጽድቅ የሚያስረዳ ከሆነ ምን እንላለን? ቁጣን የሚያመጣ እግዚአብሔር አመፀኛ ነውን? እንደሰው ልማድ እላለሁ እንድህ አይሁን እንዲህ ቢሆን እግዚአብሔር በዓለም እንዴት ይፈርዳል; **<u>በኔ ውሸት ግን የእግዚአብሔር እውነት ለክብሩ ከላቀ</u>** ስለምን በእኔ ደግሞ እንደ ኃጢአተኛ ገና ይፈርዱብኛል?

**አረብ፡**- እንዴት እግዚአብሔር በውሸት ክብሩ የላቀ ይሆናል?

**አንተነህ፡**-ወሸቶቹስ ዬቶቹ ናቸው?

**አረብ፡**- እነዚህን ጥቅሶች አንብብ በ1980 ቀለል ባለ አማርኛ ትርጉም አንብብ፡፡

**አንተነህ፡**- እሺ

| | |
|---|---|
| ማቴዎስ 5÷17 ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ የሙሴን<br>ህግና የነቢያትን ትምህርት ለመሻር የመጣሁ<br>አይምሰላችሁ፤ እኔ ፍፁም እንዲሆን ለደርጋቸው<br>መጣሁ | ኢብራዊ 7÷18 የቀድሞ ትእዛዝ፤ደካማና የማይጠቅም ስለሆነ <u>ተሸሯል</u> |

| | |
|---|---|
| እንጂ፡ልሽራቸው አልመጣሁም። | |
| ማቴዎስ 19÷17 ኢየሱስም ስለ መልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ; መልካም የሆነ... ...አንድ አምላክ ብቻ ነው ወደ ህይወት ለመግባት ብትፈልግ ግን **ትእዛዛትን ጠ ብቅ**። | ገላቲያ 3÷10 **ህግን በመፈፀም እንፀድቃለን የሚሉ ሁሉ የተረገሙ**.. ናቸው፡፡ |
| ማርቆስ፡ወንጌል 12÷29... ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት ከሁሉ ፊተኛይቱ ትእዛዝ እስራኤል ሆይ ስማ እግዚአብሔር አምላካችን አንድ አምላክ ነው፡፡ | ኤፌሶን 6÷2 ... እናትህንና አባትህን አክብር የሚለው ትእዛዝ የተስፋ ቃል ያለበት የመጀመሪያ ትእዛዝ ነው |

**አረብ፡-** ታዲያ ትክክለኛው የጳውሎስ ነው ወይስ የኢየሱስ ትምህርት ነው?

**አንተነህ፡-** እኔ ያየሁት ገና ዛሬ ነው ይህንን ለመለየት በጣም ይከብዳል፡፡

**አረብ፡-**በማቴዎስ 10÷1-4 ማርቆስ 3÷ 13-19 እና ሉቃስ 6÷12-16 ባለው ላይ የእየሱስ ሀዋሪቶች 12 ነበሩ፡ ጳውሎስ ከየት መጥቶ በሀዋሪያቶች ውስጥ እንደገባ ራሱ አናውቅም ትንቢትም የለውም፤ አለው የምትል ከሆንክ አምጣ፡፡

**አንተነህ፡-**ትንቢት የለውም ልክ ነህ፡፡

**አረብ፡-**ገና ብዙ ነገር ታያላችሁ፡ ይህን ሁሉ ጣጣ ውስጥ የገባችሁት ነቢዩ ሙሐመድን (ኢ.ሰ.ወ) ላለመቀበል ነው፡፡

## ነቢዩ ሙሐመድ(ዐ.ሰ.ወ) በቁርዓንና በመጽኃፍ ቅዱስ

**አንተነህ፡-**ነቢዩ ሙሀመድ በመጽሀፍ ቅዱስ ትንቢት የላቸዉም ።

**አረብ፡-**ትንቢት እማ አላቸው! አላህ እንደሚለን ከሆነ ከነስማቸው በመጽኃፍ ቅዱስ ውስጥ ተፅፏል፡፡

**አንተነህ፡-**አሁንም አለ ማለትህ ነው?

**አረብ፡-**እጃችሁ መች ያርፋል?በትንቢተ ኢሳያስ 7÷21 በ1954 የተፃፈውን በግ በ1980 ላይ በፊየል የቀየራችሁት፡ እንዲሁም በኦሪት ዘፍጥረት 11÷12 የቃይናን ታሪክ በ1954 ላይ ነበር፤ነገር ግን በ1980 በተተረጎመው የቃይናን ታሪክ ሙሉ ለሙሉ ከመጽኃፍ ቅዱስ አስወግደዉታል፡ ብዙ ነገር ማለት ይቻላል፡ ታዲያ እነዚህን ሁሉ መቀየርና ማጥፋት ያልከበዳቸውን ሰዎች፡ የነቢዩ ሙሐመድንም (ሰ.ዐ.ወ) ስም ከመጽኃፍ ቅዱስ ማስወገድ ምን ይከብዳቸዋል?

**አንተነህ፡-**ዝም!

**አረብ፡-** ውይይታችን በ1980 ቀለል ባለ አማርኛ መጽኃፍ ቅዱስ ትርጉም ይሁን፤ በዮሃንስ ወነንጌል 1÷19 አንብብ

**አንተነህ፡-**አይሁዳውያን ባለስልጣኖች ከእየሩስዓሌም ካህናትንና ሌዋውያን ወደ ዩሃንስ ልከው "አንተ ማንነህ?" ብለው ባስጠየቁት ጊዜ ዮሃንስ "እኔ መሲህ አይደለሁም" ሲል መሰከረ እንጂ አልካደም፡ እነርሱም "ታዲያ አንተ ማንነህ; ኤልያስ ነህን?" ሲሉ ጠየቁት፡ እርሱም "አይደለሁም" ሲል መለሰላቸው፡ እነርሱም "ይመጣል የተባለው ነብይ ነህን?" አሉት፡፡

**አረብ፡-**እዚህ ጋር ዮሃንስ ሶስት ጥያቄዎችን ነው የተጠየቀው፡፡

1. መሲህ ኢየሱስ ነው፡
2. ኤልያስ ዮሃንስ ነው፡
3. ይመጣል የተባለዉ ነብይስ ማንነው?

**አለማየሁ፡-**ከህዝብ ውስጥ ወንድሜ ልጄን እያሳሳትክ ነው፡ ኤልያስ እና አጥማቂው ዮሃንስ አንድ አይደሉም፡

**አረብ፡-**እባክህ ና ና! ወደ መድረክ ውጣ፡ እኔም ማስረጃ ስላለኝ ነው እንጂ ከራሴ አልተናገርኩም፡፡

**አለማየሁ፡-**ተመልሶ ወደ መድረክ ወጣ፡ በሁለተኛ መጽኃፈ ነገስተ 2÷11 ኤልያስ ማለት ወደ ሰማይ የወጣ ነው፡ ስለዚህ አንድ አይደሉም፡፡

**አረብ፡-**ድጋሜ እንደሚመጣ በትንቢተ ሚልኪያስ 4÷5 እንካ አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡-**ነገር ግን ታላቅ እና አስፈሪ የሆነው የጌታ ቀን ከመምጣቱ በፊት ነቢዩ ኤልያስን ወደ እናንተ እልክላችኋለሁ፡፡

**አረብ፡-**ትንቢተ ሚልኪያስ ከብሉይ ኪዳን የመጨረሻ መጽኃፍ ነው፡ ከርሱ ቀጥሎ ያለው የማቴዎስ ወንጌል ነው፡ ታዲያ ትንቢቱ የሚፈፀመው መች ይመስለሃል?

**አለማየሁ፡-**እኔ ይህንን አልቀበልህም፡ ሌላ ማስረጃ ካለ አምጣ፡፡

**አረብ፡**-እሺ ማቴዎስ ወንጌል 11÷13 አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡**-መላው የነቢያት ትምህርትና የሙሴ ህግ እስከ አጥማቂው ዮሃንስ ሲነገሩ ቆይተዋል፤ እንግዲህ እነርሱ የተናገሩትን ነገር ለመቀበል ከፈቀዳችሁ ያ <u>ይመጣል የተባለው ኤልያስ እነሆ ይህ ዮሓንስ ነው</u>፡ እንግዲህ ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ፡፡

**አረብ፡**-ኢየሱስ በአፉ ኤልያስ ማለት አጥማቂው ዮሓንስ እንደሆነ እየመሰከረ ነው፡ አሁንም በማቴዎስ 17÷11-13 አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡**-ኢየሱስ እንዲህ ሲል መለሰላቸው "እርግጥ ነው ኤልያስ አስቀድሞ ይመጣል፤ እርሱ ሁሉንም ያስተካክላል፤ ነገር ግን ኤልያስ ገና ድሮ መጥቶኣል እልችኋለሁ፡፡ ግን አላወቁም፤ ስለዚህ የፈለጉትን ሁሉ አደረጉበት፤ እንዲህም ደግሞ የሰው ልጅ ክርስቶስ በእነርሱ እጅ መከራ መቀበል አለበት፡" በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ የተናገረው <u>ስለ አጥማቂው ዩሓንስ መሆኑ ገባቸው</u>፡፡

**አረብ፡**-ኤልያስ ማለት ዮሓንስ እንደሆነ ለደቀ መዛሙርቱ ከገባቸው፤ ለእናንተ የማይገባበት ምክንያት ምንድር ነው? መሲህ ኢየሱስ ነው፡ ዮሓንስም ኤልያስ ነው፡ ታዲያ ያ ይመጣል የተባለው ሶስተኛው ነብይ ማን ነው?

**ኢብራሂም፡**-ተክቢር!

**ሙስሊሞች፡**-አላሁ አክበር!

**አለማየሁ፡**-እኔ ይህንን ገና ዛሬ ነው ያየሁት።

**አረብ፡**-በሱረቱል ሷፍ 61÷6 የመርየም ልጅ ኢሳም የኢስራኤል ልጆች ሆይ እኔ ከተውራት ከበፊቴ ያለውን የማረጋግጥ እና ከኔ በኋላ የሚመጣውን መልእክተኛ <u>ስሙ አህመድ</u> በሆነው የማበስር ስሆን ወደ እናንተ (የተላከኩ) የአላህ መልእተኛ ነኝ ባለ ጊዜ (አስታውስ)፤ በግልጽ ተዓምራቶችም በመጣቸው ጊዜ ይህ ግልጽ ድግምት ነው አሉ፡፡ አህመድ ማለት ትርጉሙ ምስጉን ሙሐመድ ማለት ደግሞ አመስጋኝ ማለት ነው፡ ሁለቱም የነቢያችን ስሞች ናቸው፡ ነቢያችን በብዙ ስሞች ሲጠሩ ነበር ለምሳሌ በቁርዓን ውስጥ ሱረቱል ጧሃ 20÷1 ***(<u>ጧሃ</u>)*** ተብሏል፡፡ በሱረቱል ያሲን 36÷1 ***(<u>ያሲን</u>)*** ተብሏል፡ እንዲሁም በሀዲስም **<u>ሙስጠፋ</u>** ተብሏል፡፡ ስለዚህ አንዳንድ ሰዎች ነቢዩ ሙሐመድን(ሰ.ዐ.ወ) ላለ መቀበል የተለያዩ ነገሮችን ያቀርባሉ፡ ነገር ግን እነርሱ የሚያቀርቡት ነገር አሳማኝ አይደለም፡ በትንቢተ ኢሳያስ 42÷1 አንብብ፡፡

**አለማየሁ፡**-የእግዚአብሔር አገልጋይ እኔ የምደግፈው የመረጥሁትና በእርሱ ደስ የሚለኝ <u>አገልጋዬ ይህ ነው</u>፡ መንፈሴ በእርሱ እንድያድርበት አደርጋለሁ፡ እርሱ ለህዝቦች ሁሉ ትክክለኛ ፍትህን ያስገኛል፡፡ ይህ የተባለው እኮ ለእየሱስ ነው!

**አረብ፡**-በተዓምር ሊሆን አይችልም፡ የእየሱስን ነብይነት ብትቀበሉማ እናንተ እኮ ሙስሊሞች እየሆናችሁ ነው፡ መንፈሴ በእርሱ እንዲያድርበት አደርጋለሁ ሲል በሱረቱል ነጅም 53÷4 እርሱ (ንግግሩ) የሚወርድ ርእይ (መንፈስ) እንጂ ሌላ አይደለም፡ ትንቢቱ እርሱ ለአለም ሁሉ ትክክለኛ ፍትህን ያስገኛል ይላል፡ ያ ማለት የተላከዉ ለዓለም ሁሉ እንደሆነ ይገልጻል፡ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል 15÷24 ላይ የተላከው <u>ለእስራኤል ብቻ ነው</u>፡፡ ታዲያ ለዓለም ሁሉ ፍትህን የሚያስገኘው ማን ነው?

**አለማየሁ፡**-ማንንም ቢሆን ከክርስቶስ ውጪ እኔ አልቀበለውም፡፡

**አረብ፡**-ማስተካከል በእጄ የለችም እንጂ እንድትቀበል አደርግህ ነበር፤ እንኳን እኔ አንተን ማስተካከል ይቅርና ነቢያችን እንኳ አጎታቸውን ወደ ቀጥተኛ መንገድ መምራት አልቻሉም፡ በሱረቱል ቀሰስ 28÷56 አንተ የወደድከውን ሰው ፈጽሞ <u>ኢታቀናም</u> ግን አላህ የሚሻውን ሰው ያቀናል፤ እርሱም ቅኖቹን አዋቂ ነው፡ አንተ ባትቀበልም በአላህ ፍቃድ የሚቀበሉ አሉ፡፡

**አንተነህ፡**-ትንቢትማ ካለ እኔ ራሴ እቀበላለሁ፡ እስከ አሁን ከኣንተ የሰማሁትን ከዛሬ በፊት ሰምቼ አላውቅም ቀጥልልን፡፡

**አረብ፡**-በሱረቱል አንቢያእ 21÷107 (ሙሐመድ ሆይ) ለአለማት እዝነት አድርገን እንጂ አልላክንህም፡ ስለዚህ ትንቢቱ የሚሆነው ለነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ነው፡፡ በሱረቱል አህዛብ 33÷46 ላይም … ለህዝብም ሁሉ ብርሃን አደርገሃለሁ፡፡ በሱረቱል ኑር 24÷40 ወይም (መጥፎ ስራዎቻቸውን) ከበላዩ ማእበል ከበላዩ ዳመና ያለበት ማእበል በሚሸፍነው ጥልቅ ባህር ውስጥ እንዳሉ ጨለማዎች ነው(እነዚያ) ከፊላቸው ከከፊሉ በላይ ድርብርብ የሆኑ ጨለማዎች ናቸው፡፡ (በዚህች የተሞከረ ሰው) እጁን ባወጣ ጊዜ ሊያያት አይቀርብም፡፡ <u>አላህም ለእርሱ ብርሃንን ያለደረገለት ሰው ለእርሱ ምንም ብርሃን የለውም</u>፡ በአላህ ያለመኑ ጭለማ ውስጥ ናቸው፤ አላህ እንዳለው በሱረቱል በቀራህ 2÷18 በአላህ ያለመነ ሰው እውር ነው፡፡ ትንቢቱ እንደሚያሳየው የእውሮችንም አይን ታበራለህ በጨለማ ስፍራ በግዛት የተቀመጡት ነፃ ታወጣለህ፡ ያ ማለት በአላህ ያላመኑትን

ወደ አላህ መንገድ ትጠራለህ፤ እንድሁም ነቢዩ ሙሐመድ(ዐሰወ) ብዙ በ ግዛት የተቀመጡትን ቢላል(ረዐ) ንም ጭምር ነፃ አዉጥቷል ፤ በትንቢተ ኢሳያስ 42 ተራ ቁጥር 11 ላይ በረሃና በበረሃ የሚገኙ ከተሞች እግዚአብሔርን ያመስግኑ **<u>የቄዳር</u>** ህዝቦች ያመስግኑት ይላል፤ ቄዳር በኦሪት ዘፍጥረት 25÷12 የእስማኤል ልጅ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ የእስማኤል ዝርያዎች ደግሞ አረቦች ናቸው፤ በትንቢተ እንምባቆም 3÷3 አንብብ

**አለማየሁ፡**-እግዚአብሔር <u>ከቴማን</u> ቅዱስም <u>ከፋራን</u> ተራራ ይመጣል፡፡

**አረብ፡**-በመጽኃፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር በሰው መካከል ተገለጸ የሚለውን ጥቅስ ብዙን ጊዜ ለእየሱስ አድርጋችሁ ትተረጉማላችሁ አይደል?

**አለማየሁ፡**-አዎዋ! እግዚአብሔር በሰው መካከል ተገለጸ የተባለውእማ ኢየሱስ ነው፡፡

**አረብ፡**- ያ ለኢየሱስ ከተተረጎመ፡ ከቴማን ይመጣል የተባለው እግዚአብሔርስ ማን ነው? ቴማን ደግሞ በኦሪት ዘፍጥረት 25÷12 የእስማኤል ልጅ ነው፡ የእስማኤል ዝርያዎች ደግሞ አረቦች ናቸው ታዲያ ከአረብ ይመጣል የተባለው እግዚአብሔር ማን ነው? ፋራን ተራራም የሚገኘው በሰኡዲ አረቢያ ውስጥ ነው፡ ስለዚህ ይመጣል የተባለው እግዚአብሔር፡ <u>ነብይ ነው እንጂ</u> አምላክ ራሱ አይደለም፡፡

**አለማየሁ፡**-ሌላ ጊዜ ጠይቄ መልስልሃለሁ፤ እንጂ እኔ እስልምናን አልቀበልም፡፡

**አረብ፡**-ይህንን ቃል ደጋገምከ ምንነው? ተቀበል ያለህ ሰው አለ? ብትቀበል እንኳ ከዚህ እንደወጣህ ሙስሊሞች አስገደዱኝ የምትል ትመስላለህ፡ ከቅድም ጀምሮ የሰለሙትንም እኛ ስለሙ አላልናቸውም፡፡

**አለማየሁ፡**-ለመጨረሻ ጊዜ መድረኩን ለቆ ሄደ፡፡

**አንተነህ፡**-እኔ እቀበላለሁ፡ የቀረ ነገር ካለ በኋላ ጥያቄ እንዳይሆንብኝ እባክህ ጨርስልን፡፡

**አረብ፡**-በሱረቱል አእራፍ 7÷157 ለነዚያ ያንን እነርሱ ዘንድ በተውራት (በኦሪት) እና በእንጂል (ወንጌል) ተጽፎ የሚያገኙትን <u>የማይጽፍና የማያነብ ነብይ</u> የሆነውን መልእክተኛን የሚከተሉ የሆኑት ...፡፡ በትንቢተ ኢሳያስ 29÷12 አንብብ፡፡

**አንተነህ፡**-ማንበብ ወደ እማይችል ሰው ወስዳችሁ <u>አንብብ ብትሉት እንኳ እኔ ችዬ አላነብም ይላችኋል…</u>

**አረብ፡**-በሙሉ መጽኃፍ ቅዱስ ውስጥ መጽኃፍ ተሰጥቶት አንብብ ተብሎ <u>እኔ ችዬ አላነብም ያለ ነብይ</u> አንድም የለም፡ ነገር ግን ነቢያችን

በሱረቱል አለቅ 96÷1 ጅብሪል ወደ ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) መጥቶ አንብብ ባላቸው ጊዜ ነቢያችን የመለሱት <u>እኔ ችዬ አላነብም ነበር</u> ያሉት፡፡እንዲሁም በኦሪት ዘዳግም 18÷17 በ1954 ትርጉም አንብብ፡፡

**አንተነህ፡-**እግዚአብሔር አለኝ የተናገሩት መልካም ነው <u>ከወንድሞቻቸው</u> መካከል <u>እንደ አንተ ያለ ነብይ አስነሳላቸዋለሁ፤ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፡፡</u> ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፤በስሜም የሚናገረውን ቃልን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ፡፡

**አረብ፡-**እግዚአብሔር ከወንድሞቻቸው ሲል፡ የኢስራኤል ወንድሞች አረቦች እንደሆኑ በኦሪት ዘፍጥረት ምእራፍ 15፤16፤17 እና 18 ላይ ተገልጿል፡ ታዲያ ከኢስራኤል ወንድሞች ውስጥ የመጣ ነብይ ማን ነው? አንድ የክርስቲያን ጸኃፊ ከበደ ሞላ መጽኃፍ ቅዱስ ስለ እስልምናና ስለ ሙሐመድ ምን ይላል? 2008 እ.ኤ.አ Alem printing press ባሳተመው ላይ አባታችን አህመድ ዲዳት(አላህ ይዘንለትና) "ተሳስተዋል ሙሳና እየሱስ ናቸው እንጂ ሙሳና ሙሐመድ አይመሳሰሉም" ብሎ አንድ ሙሉ መጽኃፍ ጽፏል፡ ከበደ ሞላ ለፃፈው በ1980 ቀለል ባለ አማርኛ መጽኃ ቅዱስ ትርጉም በኦሪት ዘዳግም 18÷20 ላይ ያለው ብቻ ለመልስ በቂ ነው፡ ጥቅሱ የሚለው፤ነገር ግን ሌላ ነብይ እኔ ሳላዘው በስሜ ትንቢትን ለመናገር ቢደፍር <u>በሞት ይቀጣል (ይገደላል)</u> እንዲሁም በበእዴን አማልክት ስም ትንቢት ለመናገር የሚሞክር ማናቸውም ነብይ እንዲሁ <u>በሞት ይቀጣሉ</u>፡፡ ሁላችንም እንደምናውቀው ክርስቲያኖች ኢየሱስ በሰው ተገድሏል ብላችሁ ታምናላችሁ፤ ጥቅሱ እንደሚለው ከሆነ ኢየሱስ ራሱ ሀሰተኛ ነብይ ነው፤ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር የተላከ ከሆነ አይገደልም ተብሏልና፡ ኣይ ኢየሱስ ሀሰተኛ አይደለም የምሉ ከሆነ ደግሞ ኢየሱስ አልተገደለም ማለት ነው፡ ስለዚህ ጸኃፊው ለጻፈው መጽህፍ መልስ ለመስጠት፡ ይህ ብቻ በቂ ነው፡ ኢየሱስ አምላክ ነው ተብሏል፤ ታዲያ አምላክ እንዴት ሆኖ ነው ከነብይ ጋር የሚመሳሰለው?

**አንተነህ፡-**ኧረ! በጣም ይገርማል! መጽኃፍ ቅዱስ ዛሬ አዲስ ሆነብኝ፡፡

**አረብ፡-**አይዞህ! በጣም ከሚገርምህ ነገር ነብይነት ከኢስራኤሎች ላይ ተወስዳ ለሌላ ህዝብ እንደምትሰጥ ፡ ማቴዎስ 21÷43 አንብብ፡፡

**አንተነህ፡-**ስለዚህ <u>የእግዚአብሔርመንግስት ከናንተ</u> ትወሳደለች ፍሬዋንም ለሚያደርግ ህዝብ ትሰጣለች፡፡

**አረብ፡**-ስለዚህም ከኢስራኤል ተወስዳ ለአረቦች ተሰጥታለች ማለት ነው፡፡

**ኢብራሂም፡**-ተክቢር!

**ሙስሊሞች፡**-አላሁ አክበር!

**አረብ፡**-ይህችን ጥቅስ አንዳንድ ክርስቲያኖች ነብይነትን አትገልጽም ይላሉ፡ ታዲያ ነብይነት ካልሆነ ከኢስራኤል ተወስዶ ለሌላ ህዝብ የተሰጠ ነገር ምንድር ነው?

**አንተነህ፡**-ዝም!

**አረብ፡**-በሱረቱል ኢምራን 3÷19 በአላህ ዘንድ (የተወደደ) ኃይማኖት <u>ኢስላም ብቻ</u> ነው፤ እነዚያ መጽኃፉን የተሰጡት ሰዎች በመካከላቸው ላለው ምቀኝነት እዉቀቱ ከመጣላቸው በኋላ እንጂ አልተለያዩም፤ በአላህም አንቀጾች የሚክድ አላህ ምርመራው ፈጣን ነው፡ ኢስራኤሎች መህላቸው ላለው ምቀኝነት ነው እንጂ የካዱት ለሌላ አይደለም፡ አላህ ደግሞ በቁርዓን ውስጥ ብዙ ቦታ ስለ ኢስራኤል ልጆች ሲናገር ከሰዎች ሁሉ በላይ አደረግናችሁ ሲል አሁን ስላለው ትውልድ አይደለም፡ እዚህ ላይ እንዳት ሳሳቱ፡ ስለ ቀደምት ነቢያቶችና የቀደምት ነቢያቶችንም ስለ ተቀበሉ፡ ነው እንጂ ልክ ብዙ ነቢያቶችን ገድለዉ፡ እነ ዮሃንስም ጨምረዉ፤ እየሱስንም ለመግደል እንሞከሩት አይደለም፡ ነብያቶች ከየትም ጎሳ ቢመጡ የአላህን ቃል ያስተምሩ እንጂ በጎሳ ነቢያቶችን ማነጣጠል አይቻልም እኛ ሙስሊሞች አላህ በሱረቱል በቀራህ 2÷285 ላይ እንዳዘዘን ፡በነቢያት አንነጣጠልም፡፡

**አንተነህ፡**-ታዲያ የኛ ሰዎች እስከ አሁን ያላወቁት ለምንድር ነው?

**አረብ፡**-በሱረቱል በቀራህ 2÷146 እነዚያ መጽኃፍን የሰጠናቸው ልጆቻቸውን እንደሚያውቁ (ሙሐመድን) ያውቁታል (በመጽኃፋቸው ምልክቱ ተነግሯልና) ከእነርሱ የተለዩ ክፍሎች እነርሱን የሚያውቁ ሲሆኑ <u>እውነቱን በእርግጥ ይደብቃሉ</u>፡፡

**አንተነህ፡**-በጣም ያስቸግራል፡፡

**አረብ፡**-አላህ በሱረቱል ሰጅዳህ 41÷53 እርሱም (ቁርዓን) እውነት መሆኑ ለእነርሱ እስከሚገለጽላቸው ድረስ በአጽናፎቹ(በምድርና በሰማይ ቀበሌዎች) ውስጥ እና በነፍሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን ተዓምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን፤ ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ አዋቂ መሆኑ አያበቃቸውምን"? መኀበራችሁ በኢስላም ላይ የማይሆን ነገር ለመፃፍ ገና አሁን እየባነኑ ነው፡፡ ምእራባውያን ከዚህ በፊት ከ 60 ሺህ ያላነሱ መጽኃፍቶችን

በእስልምና ላይ ጽፈዋል፡ ሁሉም ይጽፋል እንጂ በጻፈው ነገር እርግጠኛ ሆኖ ከሙስሊሙ ጋር በአደባባይ የሚወያይ የለም፡ ታዲያ ሰው በጻፈው ነገር የሚፈራ ከሆነ ያ የጻፈው ነገር ውሸት (ትክክል ያልሆነ ነገር) እንደሆነ ያሳያል፡ በሱረቱል ሷፍ 61÷8 የአላህንም ብርሃን በአፎቻቸው ለማጥፋት ይሻሉ አላህም ከሃዲዎች ቢጠሉ እንኳ ብርሃኑን ገላጭ ነው፡፡

በሱረቱል አህዛብ 33÷40 ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም ግን የአላህ መልእክተኛ የነቢያቶችም መደምደሚያ ነው፤ አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ አዋቂ ነው፡፡

**አንተነህ፡**-በቃኝ! ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እና ሙሐመድም የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ፡፡

**አረብ፡**-ሌላ ለውይይት ፍቃደኛ ነኝ የሚል ሰው ካለ ወደ መድረክ ይውጣ!

**ለአምስት ደቂቃ ያህል ማንም አልነበረም የአንድ ቀን ውይይቱ በዚሁ ተጠናቀቀ፡፡** ወቢላሂ አተውፊቅ ወሰላሙ አሌይኩም ወረህመቱላሂ ወበረካቱህ፡፡

የሁለተኛዉን **ቀን** ዉይይት አሏህ ካለ በሁለተኛ መጽሃፌ ላይ ይጠብቁ!